***የመልካም አስተዳደር መንግሥት እና የገበያ ኢኮኖሚ ግንባታ በኢትዮጵያ፣*** በፕሮፌሰር ተሾመ ሙላት

ይኸን መጽሐፍ በኢትዮጵያ ለማሳተም ሞክሬ ስላልተሳካልኝ (ምዕራፍ 20.6ን ተመልከት) በሚከተለው አኳኋን ታትሟል

Teshome Mulat (2015). ***Yemelkam Astedader Mengist Ena Yegebeya Economy Ginbata*** (Amharic Edition) (Amharic) paperback. USA: Self-publishing. www.amazon.com (ISBN-13: 978-1519729972; ISBN-10: 151-972-9972)

1

በዓለማችን የሚገኙትን መንግሥታት ሁለት ከፈሎ ማየት ይቻላል፤ (ሀ) ***የመልካም አስተዳደር መንግሥት (መአመ)*** [Good Governance Government (G-3)] እና (ለ) ***አምባገነን መንግሥት (አመ)*** [Non-Good Governance Government (NG3)]፡፡ መአመ የሰው ለጅ ሰብአዊ መብቶችን (የንብረት መብቶችን ጨምሮ) እንዲያከብርና እንዲያስከብርለት፣ የገበያ እቃዎችን እና አገልግሎቶችን ለማምረት እንዲያስችለው፣ በሰዎች መካከል የሚፈጠሩ (የመብት ነክ) ችግሮችን እንዲፈታለት እና የገበያ ኢኮኖሚ ግንባታዎችን በቀጣይነት ለማካሄድ ያስችለው ዘንድ የፈጠረው ነው፡፡

ይኸን ሠፊ የመብት ጥበቃ ጉዳይ ተፈጻሚ እንዲያደርግ ከተፈለገ የመአመ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት በተለየ መልክ መዘርጋትና መዋቀር አለበት፡፡ ***እውነተኛ ተቃዋሚ ፓርቲዎች (እተፓ)***[1] በ3ቱም የመአመ ክፍላተ መንግሥቱ (ማለትም በሕግ አውጪው፣ ሕግ አስፈፃሚው እና ሕግ ተርጓሚው የመአመ ክፍሎች) በነጻነት እና በመተባበር ከገዢ ፓርቲው ጋር ይሠራሉ፡፡ መንግሥቱ እና የገበያ ኢኮኖሚ ግንባታው እንዲጠናከር እና ቀጣይነት ሊኖረው የሚችለው በእተፓዎች ነው፡፡ ከእተፓዎች መካከል የእውነቱ እውቀት ባለው ሕዝብ ሕዝበ-ውሳኔ የተመረጠው እተፓ መአመ ይሆናል፡፡[2]

መሠረታዊ የኢኮኖሚ እና ማኅበራዊ ችግሮችን መፍታት የሚቻለው **የገበያ እቃዎችንና አገልግሎቶችን** በብዛት፣ አይነት እና ጥራት በማምረት እና በማከፋፈል ሲሆን፣ ይኸም ተፈጻሚ የሚሆነው ***በመልካም አስተዳደር መንግሥት (መአመ)*** እና ***በገበያ ኢኮኖሚ*** ሥርዓት ብቻ ነው፡፡ መአመ ***የመንግሥት ማሻሻያዎችን*** (Government Reform) እና ***የገበያ ማሻሻያዎችን*** (Market Reform) ለማካሄድ የሚያስችለውን ሕገ-መንግሥታዊ እና ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት የዘረጋ መንግሥት ነው፡፡ በአምባገነን መንግሥት (አመ) ሥርዓት ውስጥ የገበያ ኢኮኖሚ እቃዎች እና አገልግሎቶች ዘላቂነት ባለው መንገድ አይመረቱም፤ በሕጋዊ፣ፍትሐዊ፣እና ሥነ-ልቡናዊ ተቀባይነት ባለው መንገድ አይከፋፈሉም፡፡

በፈርኦኑ ዘመንም ሆነ በሶቪየቶቹ ***የስብስብ ኢኮኖሚ*** ሥርዓት ***የኢኮኖሚ እቃዎችና አገልግሎቶች*** ይመረታሉ፣ ***የጥፋት እቃዎችና አገልግሎቶችም*** እንዲሁ፡፡ በሁለቱም ሁኔታዎች ውስጥ ተመራቾች ያልነበሩት ***"የገበያ እቃዎች እና አገልግሎቶች"*** ናቸው፡፡[3] በመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት የሚመረቱት የገበያ እቃዎችና አገልግሎቶች ሲሆኑ እነሱም ***ድህረ-መብት ንብረቶች*** (የመብት ጥበቃ ያላቸው እቃዎችና አገልግሎቶች) ናቸው፡፡ በፈርኦን ሥርአት፣ በሶቪየት ኅብረት፣ በደርግ የስብስብ ኢኮኖሚ፣ በሩሲያ ኦሊጋርኪ እና በወያኔ/ኢሕአዴግ (የብሔር) አፓርታይድ መንግሥት እና የማፊያ ኢኮናሚ ሥርዓት የሚመረቱ እቃዎችና አገልግሎቶች ***ቅድመ-መብት*** (መብት ያልተከበረላቸው) ንብረቶች ናቸው፡፡ በ ***አምባገነን መንግሥት (አመ)*** ሥርዓቶች ተመራች የሚሆኑት ***ቅድመ-መብት ንብረቶች*** (የኢኮኖሚ እና የጥፋት እቃዎችና አገልግሎቶች) ሲሆኑ፣ ድህረ-መብት ንብረቶች (የገበያ አቃዎችና አገልግሎቶች) ደግሞ የሚመረቱት በመአመ እና በገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት ብቻ ነው፡፡[4]

---

[1] ባጭሩ እተፓ ማለት ስለ መአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት እንዲሁም ስለ መአዓመ አብዮት (11ን ተመልከት) የእውነቱ እውቀት ያለውና ህጋዊ፣ ሙያዊ እና ሥነ-ልቡናዊ ግዴታዎቹን የተረዳ ፓርቲ ነው፡፡ መጽሐፉ እኒህን ጽንሰ-ሀሳቦች ያብራራል፡፡

[2] በእውነቱ እውቀት ሳይሆን በአምባገነን ፓርቲዎች ወይም አምባገነን መንግሥቶች ላይ ባለው እምነት ሕዝበ-ውሳኔውን የሚሰጥ ሕዝብ "ሞብ" ይባላል፡፡ ሞብ እራሱን የሚጐዳ እና አጥፍቶ ጠፊ የሕዝብ ስብስብ ነው፡፡ አመዎችም የሞብ መንጋ ነጂዎች ናቸው፡፡

[3] በ1942-1975 በኢትዮጵያ በመአዓመ ስምምነት የመአመና የገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት በመዘርጋት የገበያ እቃዎችና አገልግሎቶችን ማምረት ተጀምሮ ነበር፡፡ የደርግ፣ የሻቢያ እና የወያኔ መንግሥታት የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓቱን በማፍረስ የኢኮኖሚ እና የጥፋት እቃዎች እና አገልግሎቶች ብቻ እንዲመረቱ አድርገዋል፡፡

[4] መጽሐፉ እነዚህን ጽንሰ-ሀሳቦች እና ጉዳዮች በሠፊው ያስረዳል፡፡

II

ከሁለተኛ የዓለም ጦርነት በኋላ የሰው ልጅ የሰብአዊ መብቶች በዓለም የተከበሩ እንዲሆኑ፣ ***የዓለም የጋራ ንብረቶች[5] መብቶችን*** (rights in global public goods) ለማስጠበቅ እና በመንግሥታት መካከል የሚፈጠሩ አለመግባባቶች እንዲፈቱ ለማድረግ የፈጠረውን የመንግሥታት መንግሥት ***የመልካም አስተዳደር የዓለም መንግሥት (መአዓመ)*** [global good-governance government (G-4)] እንለዋለን።[6]

***የመአዓመ አብዮት*** የምንለው በመአዓመ ስምምነት፣ የመአመን በማቋቋም እና ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱን በመዘርጋት፣ ሰብአዊ መብቶች (ሕገ-አሉታዊ እና ሕገ-አዎንታዊ ሰብአዊ መብቶች) እንዲከበሩ በማድረግ፣ የገበያ እቃዎችንና አገልግሎቶችን እንዲመረቱ እና እንዲከፋፈሉ በማስቻል የገበያ ኢኮናሚ (መብቶች የተከበሩበት ኢኮኖሚ) ግንባታ በቀጣይነት የሚካሄድበትን የሀሳብ መንገድ ነው።

III

አምባገነን መንግሥት (አመ) በመአዓመ ስምምነት አይገዛም፣ የመልካም አስተዳደር መንግሥት (መአመ) አይደለም። አመ ሰብአዊ መብቶችን ገፋፊ፣ ንብረት ዘራፊ፣ የወል ግድያ ፈጻሚ፣ ያለሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት እና ሕገ-መንግሥት ፍርድ የሚሰጥ እና የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ግንባታ ሥርዓት አፍራሽ ነው። የአምባገነን መንግሥት የመልካም አስተዳደር መንግሥት ስላልሆነ እና እውነተኛ ተቃዋሚ ፓርቲዎች የሌሉት በመሆኑ ቀጣይነት አይኖረውም። መንግሥቱ ከመውደቅ ኢኮኖሚውም ከመውደም አይድንም። ሁሌም የመአዓመ አብዮት መንገድን መከተል ካልቻለ የአምባገነን መንግሥቱና የገበያ ኢኮኖሚ ያልሆነው ኢኮኖሚ [ከእጅ-ወደ-አፍ ኢኮኖሚ (subsistence economy)፣ የስብስብ ኢኮኖሚ (collectivist economy)፣ የማፊያ ኢኮኖሚ (mafia economy)፣ የጋራ ንብረት ኢኮኖሚ (common property economy)፣ ወዘተ] መጨረሻው መንግሥቱ ***የወደቀ መንግሥት*** (failed government) እና ኢኮኖሚው ደግሞ ***የወደቀ ኢኮኖሚ*** (failed economy) መሆን ነው።[7]

IV

በ1942-1975 የኢትዮጵያ መንግሥት በመአዓመ ስምምነት መሠረት፣ የመአመ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት በመዘርጋት፣ ሰብአዊ መብቶችን የተከበሩ በማድረግ፣ የገበያ እቃዎችንና አገልግሎቶችን በማምረት እና በማከፋፈል የገበያ ኢኮኖሚ ግንባታዎችን ጀምሯል። ይኸን የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ግንባታ ሥርዓት ለመዘርጋት የኢኮኖሚ እና ማኅበራዊ ቅድመ-ግንባታዎች (infrastructures) (በቅድሚያ) መገንባት ነበረባቸው። ይኸ ሂደት ሁለት የአሥርተ ዓመታት ጊዜንና ሠፊ የመንግሥትን መዋዕለ ንዋይ ወጪዎችን የጠየቀ ነበር። የሰው ሀይል ግንባታው የረጅም ጊዜ ወጪን እና የመአዓመ አብዮት መንግሥታትን ተሳትፎ እና እርዳታ ጠይቋል።

የመጀመሪያዎቹ ዓመታት የቅድመ ግንባታ ጊዜዎች በመሆናቸው የሚደረገው የመንግሥት ማሻሻያ (government reform) እና የገበያ ማሻሻያ (market reform) መርሀ-ግብሮቹ አፈጻጸም አዝጋሚዎች ነበሩ። ከዛ በኋላ ግን በአምስት ዓመት ፕላን እየተመራ የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ግንባታው በተፋጠነ ሁኔታ መካሄድ ጀምሯል። በ1960ዎቹ (በአንደኛ እና ሁለተኛ የአምስት ዓመት ፕላን ዘመን) የገበያ ኢኮኖሚው በአማካኝ የሁለት ዲጂት ዓመታዊ የምርት ዕድገት አሳይቷል።

የ1942-1975 የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት የመአዓመ ድርጅቶች መስራች አባል እና የመአዓመ ስምምነቶችን ፈራሚና ፈጻሚ ነበር። የኢትዮጵያ መንግሥት እንደሶቪየቶቹ የኮሚኒስት መንግሥት ቅኝ አገዛዝን (colonialism) ተዋግቷል። ኢትዮጵያን ብቻ ሳይሆን የአፍሪካን ሕዝብ ከቅኝ አገዛዝ ነጻ ለማውጣት አስተዋጽኦ አድርጓል (የማንዴላን መጽሐፍ፣ የራስ ተፈሪያኖችን

[5] የዓለም የጋራ ንብረት (global public goods) የሚባሉት የዓለም መንግሥታት በጋራ የሚጠቀሙባቸው እንደውቅያኖስ፣ አየር፣ የምድር ዋልታዎች፣ ወዘተ የመሳሰሉትን ነው። በእነሀ የመጠቀም መብት የሚገኘው እና የሚጠበቀው በመንግሥታቱ መንግሥት (መአዓመ) ስምምነቶት ነው።

[6] የተባበሩት መንግሥታት መአዓመ ነው። ለመአዓመ መፈጠር ዋና ምክንያቶቹ እና ስለመአዓመ አሠራር፣ ቀጣይነት እና እየተጠናከረ መሄድ መረጃዎችን መጽሐፉ ይሰጣል።

[7] የትሮይ ፈረስ ጋላቢ መንግሥት የነበረው አምባገነኑ የሶቪየት ኮሚኒስት ፓርቲ በስልጣን ላይ 100 ዓመታት ያህል ሲቆይ፣ የሱ ተጋላቢ የትሮይ ፈረስ የነበረው አምባገነኑ የደርግ/ኢሠፓ የኮሚኒስት መንግሥት ከሶቪየቱ መንግሥት መውደቅ ጋር ተያይዞ በ1991 አብሮ ወድቋል፤ የሶቪየት ኅብረቱ የስብስብ ኢኮኖሚ ሲፈርስ የደርጉ የስብስብ ኢኮኖሚ በእንጥልጥሉ ሳይገነባ ቀርቷል።

ታሪክ እና የፓን አፍሪካን አብዮት መሪዎች ጽሑፎችን፣ የኢትዮጵያውያን እና የውጭ ባለሙያ ጽሑፎችን እንዲሁም የዘውዴ ረታን የጽሑፍ ሥራዎች ተመልከት)።[8]

በሶቪየት ኅብረት እና በኢትዮጵያ መንግሥታት መካከል "ከየት ወዴት?" በሚለው ጥያቄ ላይ የጐላ ልዩነት ነበር። የኢትዮጵያ መንግሥት የእጅ-አዙር-ቅኝ-አገዛዝን (neocolonialism) በሚመለከት ማሸነፍ የሚቻለው በጦርነት ሳይሆን በመአዓመ አብዮት መንገድ ብቻ ነው ብሎ (ማለትም በመአዓመ ስምምነት መሠረት፣ የመአመ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት በመዘርጋት፣ ሰብአዊ መብቶችን የተከበሩ በማድረግ እና የገበያ ኢኮኖሚ በመገንባት መሆኑን) ያምናል። ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት በኋላ በተከሰተው የቀዝቃዛው ጦርነት ዘመን የኢትዮጵያ መንግሥት ይኸን እምነቱን በመአዓመ አብዮት መንገድ ተፈጻሚ አድርጓል። የሶቪየት ኅብረት የኮሚኒስት መንግሥት ደግሞ የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ጦርነቶችን [እንደቅኝ አገዛዝ (colonialism) ጦርነቶች] በቀጥታ ሳይሆን በቀላጤ (proxy) ጦርነት ማሸነፍ እንደሚቻልና ማሸነፍም የሚቻለው በኮሚኒስት ሥርዓተ መንግሥት እና በስብስብ ኢኮኖሚ ግንባታ ነው ብሎ ያምናል።

V

አስከፊው የወሎ ድርቅ በተከሰተበት ዘመን በቦታው የተገኙ ሰዎች በሰሜኑ አካባቢ በረሃብ የተሰቃዩ ሰዎች እህል (ምግብ) የተከማቸበትን ጐተራ ከበው እየሞቱ እንደነበር ነግረውኛል። የተቆለፈበትን ጐተራ ከፍቶ ብሉ የሚል የመንግሥት ባለሥልጣን በአካባቢው አልነበረም። ለምን ጐተራውን ሰብረው እህሉን በመብላት ህይወታቸውን አላዳኑም? ቁም ነገሩ ያለው የዚህ ጥያቄ መልስ ላይ ነው። እነኚህ ሰዎች ለመንግሥት ላላቸው ክብር እና ለአሠርቱ ትእዛዛተ ኦሪት (አትስረቅ፣ አትግደል፣ አታመንዝር፣ ወዘተ) እምነታቸው ከህይወት በላይ ዋጋ ይሰጡታል። የሰው ልጅ መንግሥትን ከፈጠረበት እና መረጃ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ይኸ የሥነ-ልቡናዊ ግዴታ (deontological ethics) መከበር ኢትዮጵያውያን የታወቁበት እና የማንነታቸው መገለጫ ሆኗል።

በሁለተኛው የዓለም ጦርነት የናዚ ጀርመን ጦር የማረካቸውን የፈረንሳይ ጥቁር ወታደሮች በፈረንሳይ ነጭ ወታደሮች ያስጠብቃቸው ነበር። እነኚህ ብዙ ጥቁር ወታደሮች ተሰብስበው በእሥር ቤቱ ግቢ እንዲቆሙ ካደረገ እና በረሃብ ካሰቃያቸው በኋላ አንድ በግ በመሀላቸው እንዲለቀቅ አድርጐ በአጅና በጥርሳቸው ያንን በግ በጣጥሰው ለመብላት ሲራኰቱ ፊልም ቀርጾ ለናዚዎች እና ለዓለም አሳይቶታል። በዚህ ድርጊቱ የራሱን ሰብአዊነት ያጣው የናዚ ጦር የአፍሪካውያኑን አረመኔነት አሳይቶበታል። እነዛ አፍሪካውያን እንደ ኢትዮጵያውያኑ በጉን በመሀላቸው ሣር እንዲግጥ ቢያደርጉት ኖሮ ወይም ጀርመኖቹን ቢላዋ እንዲሰጧቸው ጠይቀው በጉን አርደው ከመሀላቸው ይበልጥ የተጐዱትን እንዲበሉ አድረገው ቢሆን የናዚው ጦር የድርጊቱን ፊልም አይቀርጽም ነበር። ያ ድርጊት እውን ተፈጻሚ ከሆነ በድብቅ ፊልሙን ቀርጾ ያቀረበውም ሰው ስለሰው ልጅ ክብር ማስተማሪያና ትሩፋት ሰጭ ተግባር ፈጽሞ ነበር።

ከ1975 በፊት በኢትዮጵያውያን እና የውጭ ዜጋ ባለሙያዎች ስለኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያውያን በጻፏቸው ጽሁፎች ከላይ የተሰጠውን ድምዳሜ የሚያፋልስ ነገር አላነበብኩም። ከ1975 በኋላ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ምኅዳር በኢትዮጵያ ተጋላቢ የትሮይ ፈረሶች፣ አሸባሪዎች እና አረመኔዎች በመያዙ ስለ እላይ የተገለጡት ኢትዮጵያውያን አረመኔነት መጻፍ ተጀምሯል።[9] አንዱ ይኸንን ጉዳይ አሳዛኝ እና አሳሳቢ የሚያደርገው ይኸ ድርጊት ተፈጻሚ የሆነው የመአዓመ አብዮት መንግሥታት ተጋላቢ የትሮይ ፈረስ፣ አሸባሪ እና አረመኔዎችን በሚዋጉበት ጊዜ መከሰቱ ነው።

የመአዓመ አብዮት መንግሥታት ፍላጐት ከላይ እንደታየው የናዚ ጦር የኢትዮጵያዊውን አረመኔነት ለማሳየት አይደለም። የመአዓመ አብዮት መንግሥታት ዓላማና ፍላጐት ኢትዮጵያውያን አረመኔ ኢትዮጵያውያንን እንዲያውቋቸው ማስቻል መሆኑን መረዳት ይኖርብናል።[10] የመአዓመ አብዮት መንግሥታት እና የማንኛውም ለሰብአዊነት ዋጋ የሚሰጥ ሰው ፍላጐት ኢትዮጵያ የእነዛ ኢትዮጵያዊነትን እና ሰብአዊነትን ከሞት በላይ ዋጋ የሚሰጡ ኢትዮጵያውያን አገር እንድትሆን ነው። የመአዓመ አብዮት መንግሥታት አገራትን የድህረ-መብት ዘመን ዜጐች መኖሪያ እንዳደረጓቸው ሁሉ በኢትዮጵያም

[8] የደርግ እና የወያኔ አምባገነን መንግሥታት በዘመናቸው የተቋቋሙ የመአዓመ ድርጅቶች አባሎች እና መስራቾች አይደሉም። ለምሳሌ የወያኔ እና የሻቢያ መንግሥታት የዓለም ንግድ ድርጅት (ዓንድ፣ WTO) አባላት አይደሉም። የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት የዓንድ አባል ለመሆን አመልክቶ እስከዛሬ ተቀባይነትን አላገኘም።

[9] ተጋላቢ የትሮይ ፈረሶች የውጭ ጋላቢ የትሮይ ፈረስ መንግሥት (ወይም የውጭ የጥፋት ኃይል) ጥይት ካላቀበላቸው፣ ስንቅ ካልሰፈረላቸው እና አመራር ካልሰጣቸው በራሳቸው ምንም መሥራት አይችሉም። ተጋላቢ የትሮይ ፈረሶች ሞቦችን እና የሞራል ዝቅጠት በሽታ ተጠቂዎችን ነጂዎች ናቸው።

[10] የኢትዮጵያ ተጋላቢ የትሮይ ፈረሶች፣ አረመኔዎች እና አሸባሪዎች አላማ በውሸት እና በአሳሳች መረጃ በመጠቀም የኢትዮጵያውያንን አረመኔነት ለማሳየት ነው። በዚህም ድርጊታቸው የራሳቸውን እጅግ የከፋ አረመኔነት ያጋለጡ መሆናቸውን አይገነዘቡም።

የኢትዮጵያን ተጋላቢ የትሮይ ፈረሶችን እና የቅድመ-መብት ዓለም አረመኔዎችን በመአመ እና በገበያ ኢኮኖሚ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት ቁጥጥር ሥር እንዲወድቁ ለማድረግ ዓለም አቀፍ ትግል እየተካሄደ ነው፡፡

እነዛ ሰብአዊነት እና ኢትዮጵያዊነት የገፀ-ባህርያቸው መገለጫ የሆነ ኢትዮጵያውያን ኢትዮጵያን ለአረመኔዎች እና ለተጋላቢ የትሮይ ፈረሶች አስረክበው የሰብአዊ መብት ወደተከበረባቸው የመአዓመ አብዮት መንግሥታት አገሮች መሄዳቸው አሳዛኝ ክስተት ቢሆንም በእነዛው መንግሥታት ለኢትዮጵያውያን አገራቸውን ከአረመኔዎችና ከተጋላቢ የትሮይ ፈረሶች እንዲሁም አሸባሪዎች ነጻ እንዲያደርጉ ድጋፍ መደረጉ ለኢትዮጵያውያን እና ለሰው ልጅ በሙሉ ብሩህ ተስፋን ይሰጣል፡፡ እርግጥ ነው ቁጥረ ብዙ ኢትዮጵያውያን መንገድ ጠፍቶባቸው ከአገራቸው አጥፊዎች ለማምለጥ ሲሉ ወደ አምባገነን የአፍሪካ እና የአረብ አገሮች ተሰደዋል፡፡ በእነህ አገሮች በአረመኔዎቹ እና አምባገነኖቹ በደል ተፈጽሞባቸዋል፣ እዛው ድረስ በመሄድ የኢትዮጵያ ተጋላቢ የትሮይ ፈረሶቹ እና አረመኔዎቹ የኢትዮጵያኑን ኑሮ ከድጡ ወደማጡ እንዲሆን አድርገውታል፡፡ አሁን በግልፅ እየታየ ያለው ሁኔታ ሰብአዊነት እና ኢትዮጵያዊነትን የማንነታቸው መገለጫ ያደረጉ ኢትዮጵያውያን ኢትዮጵያ አገራቸውን ከአረመኔዎች፣ አሸባሪዎች እና ተጋላቢ የትሮይ ፈረሶች ነጻ በማድረግ የ1942-1975 የመአመ እና የገበያ ኢኮናሚ ሥርዓት እንዲጠናከር እና ቀጣይነት እንዲኖረው ለማድረግ የሚዋጉትን ጦርነት መደምደሚያው ምዕራፍ ላይ መድረሳቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የኢትዮጵያ ተጋላቢ የትሮይ ፈረሶች እና አረመኔዎች እነማን እንደሆኑ በመአዓመ አብዮት መንግሥታት እና የእውነቱ እውቀት ያላቸው ኢትዮጵያውያን እየተለዩ መጥተዋል፡፡[11] የኢትዮጵያ ተጋላቢ የትሮይ ፈረሶች እና አረመኔዎች ጥፋተኛ የሆኑ የደርግ/ኢሠፓ፣ የሻቢያ፣ የጀብሃ፣ የወያኔ/መወቢካው መንግሥት እና ተለጣፊው፣ ታብተፓው፣ ተብጦፓው፣ የብሔር እና የሀይማኖት ማርክሲስቱን እንዲሁ በነሱ የሚመራውን (የሚነዳውን) ሞብ እና የሞራል ፀፀት በሽታ ተጠቂዎችን ያጠቃልላል፡፡[12] በመአዓመ አብዮት መንግሥታት አስተባባሪነት በተባበሩት መንግሥታት ጥፋተኛ የኢትዮጵያ ተጋላቢ የትሮይ ፈረሶች እና አረመኔዎች "አሸባሪዎች" ተብለው የሚፈረጁ እና ጦርነት የተከፈተባቸው እና የሚከፈትባቸው ናቸው፡፡

የኢትዮጵያን ተጋላቢ የትሮይ ፈረሶችን እና አረመኔዎችን (ኢተትፈአ) የኢትዮጵያ ሕዝብ ሊያውቃቸው ይገባል፡፡ ኢተትፈአዎች ያለባቸውን የሕግ፣ የዜግነት፣ የሙያ እና የሥነ-ልቡናዊ ግዴታቸውን የሚወጡ አይደሉም፡፡ ሁሉንም መሆን የሚፈልጉ እና "ዘጠኝ የድመት ህይወታቸውን" ነዋሪዎች ናቸው፡፡ አንዱ መለያቸው የሞቦች እና የሞራል ፀፀት በሽታ ተጠቂዎች መሪዎች (ነጂዎች) መሆናቸው ነው፡፡

## VI

ከእጅ-ወደ-አፍ (Subsistence) ኢኮኖሚ ውስጥ ትርፈ-ምርት ስለሌለ ማፊያ አይኖርም፣ የማፊያ ኢኮኖሚም የለም፡፡[13] እንዲሁም በኮሚኒስት (የደርግ) መንግሥት የግለሰብ መብት (በተለይ የግለሰብ የንብረት መብት) እንዲገፈፍ በመደንገጉ ማፊያና የማፊያ ኢኮኖሚ አይከሰትም፡፡ ማፊያ እና የማፊያ ኢኮኖሚ የሚከሰተው በመአመ እና በገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት ውስጥ ሲሆን፣ የመከሰቱም ሁኔታ የሚገለጠው ለመአመና የገበያ ኢኮኖሚው የካንሰር በሽታ በመሆን መአመውን በሙስና የተጨማለቀ በማድረግ እና የገበያ ኢኮኖሚውን በመግደል (በማፍረስ) ነው፡፡[14]

በ1942-1975 ኢትዮጵያ የመአመ ሥርዓት መዘርጋትና የገበያ ኢኮኖሚ መገንባትን ተከትሎ ማፊያውና የማፊያ ኢኮኖሚው ተከስቷል፡፡ ለመከሰቱም ዋና ምክንያቱ በመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት የሚገኘው ትርፈ ምርት ነው፡፡ ነገር ግን የመልካም አስተዳደር መንግሥቱ የመንግሥት ማሻሻያ (Government reform) እና የገበያው ማሻሻያ (market reform) ዳተኛ በመሆኑ፤ ደርግም ባይመጣ ኖሮ በላቲን አሜሪካ ኢኮኖሚዎች እንደታየው ማፊያውና የማፊያ ኢኮኖሚው ተጠናክሮ የኢትዮጵያን መንግሥት ይጥለው ነበር፤ አገሩም የውጭ ጣልቃ ገብነት ከሌለ እንደሶማሊያ ወይም ሱዳን በራሱ ማፊያ ይፈርስ ነበር፡፡

---

[11] "የእውነቱ እውቀት ያላቸው ኢትዮጵያውያን" ያልናቸው ስለ መአዓመ አብዮት እና ስለ 1942-1975 የመአመና የገበያ ኢኮናሚ ግንባታ እውቀት ያላቸው፣ ሥርዓቱን የዘረጉ፣ ለሥርዓቱ መዘርጋት እና የመአዓመ አብዮት በኢትዮጵያ እንዲሰፍን መስዋእት የከፈሉ እና በማንኛውም ጊዜ እና ቦታ ያለባቸውን የሕግ፣ የዜግነት፣ የሙያ እና የሥነ-ልቡና ግዴታቸውን የተገነዘቡ ግለሰቦችን ነው፡፡

[12] የኢትዮጵያን ተጋላቢ የትሮይ ፈረስ እና አረመኔ የሚለው ስብስብ የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥትን የሆብሶን ምርጫ ይጨምራል፡፡ እኒህ የሆብሶን ምርጫዎች ሕዝቡ ከነሱ ይልቅ የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት ይሻለኛል ወይም "የባሰ አታምጣ" የሚላቸው ናቸው፡፡

[13] ማፊያ እና የማፊያ ኢኮኖሚ በመጽሐፉ ተገልጠዋል፡፡

[14] ትርፈ-ምርት የሚገኘው በገበያ ኢኮኖሚ ነው፡፡ ማፊያ እና የማፊያ ኢኮኖሚ ይኽን ትርፈ-ምርት በጥፋት መንገድ (በሕገ-ወጥ መንገድ) ለመዝረፍ ይከሰታል፡፡

የጣሊያን ማፊያ ከግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ በመነሳት አያደገ ሄዶ የመልካም አስተዳደር መንግሥቱን መቆጣጠር እንደቻለ ይነገርለታል፡፡ በመቀጠል ላይ ያለው የ 2008ቱ የዓለም የኢኮኖሚ እና የፋይናንስ ነውጥን ለመከላከል በአውሮፓ ኅብረት የተጀመረው በመንግሥት እና በገበያ ማሻሻያ (government and market reform) የባንክንና የኮርፖሬሽኖችን ከክስረት ለማዳን የሚደረገውን የብድር እና የወገብ አጥብቅ ዘመቻ (bail out and ansterity measures) የጣሊያን ማፊያው ሊያደናቅፍ ይችላል የሚል ፍራቻ አለ፡፡

በአሜሪካ የመንግሥት እና የገበያ ማሻሻያዎችን (government and market reform) በመአመ እና እተፓዎች በጊዜው መወሰድ በመቻሉ የአሜሪካ የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓቱ ሊጠናከር እና ቀጣይነትም ሊኖረው ችሏል፡፡[15] የአሜሪካ መንግሥት የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚው እንዲጠናከር እና ቀጣይነት እንዲኖረው ለማስቻል ያለማቋረጥ የመንግሥት ማሻሻያ (government reform) እና የገበያ ማሻሻያ (market reform) ማካሄድ በመቻሉ ለዓለም ኢኮኖሚ እድገት የፈር ቀዳጁን ሚና መጫወት ችሏል፡፡

የሩሲያን ኦሊጋርኪ እና የወያኔ (የአፓርታይድ) መንግሥት የማፊያ ኢኮኖሚዎች የተለዩ የሚያደርጋቸው የማፊያ ኢኮኖሚው ፈጣሪዎቹ መንግሥቶቹ እራሳቸው መሆናቸው ነው፡፡ የመንግሥቱ ማፊያ የግሉ ኢኮኖሚን ማፊያ የፈጠረ ነው፡፡ የሩሲያ (የመንግሥቱ እና የግሉ ኢኮኖሚ) ማፊያ ወደ መአመ አገሮች (ወደ መአዓመ አብዮት መንግሥታት አገሮች) የኢኮኖሚ እቃዎችንና አገልግሎቶችን ላኪ (exporter) ነው፡፡ ወደ 3ተኛው ዓለም አገሮች ደግሞ የጥፋት እቃዎችንና አገልግሎቶችን በመላክ የኢኮኖሚ እቃዎችን እና አገልግሎቶችን የሚቀበልና ወደ መአመ አገሮች መልሶ የሚያስገባ (re-exporter) ነው፡፡ የሩሲያው ሆነ የኢትዮጵያ የወያኔ መንግሥት እና የግሉ ማፊያ የኢኮኖሚ እቃዎችን እና አገልግሎቶችን እንዲሁም የተዘረፉ የገንዘብ ሀብት ወደ መአዓመ አብዮት መንግሥታት አገራት የሚያስገባው የባለቤትነት መብቱ በአገሩ ያልተከበረ እና በመአዓመ አብዮት መንግሥታት አገሮች ደግሞ የተከበረ በመሆኑ ነው፡፡ ይኽ ሁኔታ ቢቀጥል የሩሲያ ሕዝብ እንደሚጐዳ ግልጽ ነው፡፡ ማፊያው የሩሲያን የኢኮኖሚ እቃዎችንና አገልግሎቶች አሟጦ ወደ መአመ አገሮች በማስገባት የሩሲያን ሕዝብ በብጥብጥ ጦርነት ያጠፋው አገሩንም ያፈረሰው ነበር፡፡[16] የሩሲያ ማፊያ ያገኘውን ንብረት በሕጋዊ፣ ፍትሐዊ እና ሥነ-ልቡናዊ ተቀባይነት ባለው መንገድ ያገኘው ሳይሆን፣ በጥፋት ሥራ (ዝርፊያ፣ ስርቆት፣ በማጭበርበር፣ በሙስና፣ በጦር ኃይል በመጠቀም እና በግድያ) ያገኘው በመሆኑ የንብረት ባለቤትነት መብቱ የሚከበርለት በመአዓመ አብዮት አገሮች በመአመ መንግሥታት በመሆኑ ወደ እነዚህ አገሮች የካፒታል በረራ (capital flight) እንዲፈጸም ያደርጋል፡፡

በድህረ-ቀዝቃዛው ዘመን የሩሲያን ሕዝብ ለመታደግ የመአዓመ አብዮት መንግሥታት የማፊያውን የኢኮኖሚ እቃዎችና አገልግሎቶች በመአዓመ ስምምነቶች መሠረት [ለምሳሌ የዓለም ንግድ ድርጅት (WTO) ሕግ መሰረት] እንዲገቡ በማድረግ ሕጉን የሚጥሱ እቃና አገልግሎቶች ላይ ማእቀብ ጥለውባቸዋል፡፡ በሕጋዊ፣ ፍትሐዊ እና ስነልቦናዊ ተቀባይነት ባለው መንገድ ያላገኘውን ገንዘብ በባንካቸው እንዳያስቀምጥ አግደውታል፡፡ የዚህ ሂደት ጠቀሜታው የሩሲያን ሕዝብ መብት እና ጥቅም ማስከበር ነው፡፡ ኦሊጋርኪው ይኽን ተረድቶ የመአዓመ አብዮት መንግሥታት ለሩሲያ ሕዝብ ተጠቃሚ እንዲሆን ያሳዩትን በጐ ተግባር በመአዓመ ስምምነት በመገዛት በሩሲያ የመአዓመ አብዮትን ተፈጻሚ ካላደረገ መንግሥቱም ይወድቃል የማፊያ ኢኮኖሚውም እንዲሁ፡፡ እንደሚታወቀው በደርግ ዘመን (በ1975-1991) የሶቪየት ኅብረት የትሮይ ፈረስ ጋላቢ የኮሚኒስት አምባገነን መንግሥት ለተጋላቢ የትሮይ ፈረሱ ለደርግ መንግሥት ጥይት (የጥፋት እቃ) በማቀበል እና የማርክሲዝም ሌኒኒዝም ርዕዮተ ዓለም (እምነት) ወደ ኢትዮጵያ በማስገባት በ1942-1975 ኢትዮጵያ በመቀጣጠል ላይ የነበረውን የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት አፍርሶታል፡፡

የቻይና ኮሚኒስት መንግሥት በዴንግ ዚያዎፒንግ የግዛት ዘመን (በ1970ዎቹ መጨረሻ ላይ) በመአዓመ ስምምነት ለመገዛት በመስማማቱ፣ የግል ንብረት መብት (በተለይ የዓለም አቀፍ ኮርፖሬሽኖች የንብረት መብት) እንዲከበር በማድረጉ የውጭ ካፒታል ወደ ቻይና ሊፈስና የቻይናን የገበያ ኢኮናሚ ግንባታ ሊያፋጥነውና ቻይናን የዓለማችን ሁለተኛ ትልቁ ኢኮኖሚ ሊያስብላት በቅቷል፡፡ ሆኖም የቻይና መንግሥት የመልካም አስተዳደር መንግሥት ማሻሻያ (government reform) እያካሄደ አይደለም፤ በመአዓመ ስምምነት እና በበቂ ፍጥነት እንደ 1942-1975 የኢትዮጵያ መንግሥት የመአመ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርአቶችን እየዘረጋ እና የመአመ ተቋማትን እየገነባ አይደለም፡፡ የቻይና መንግሥት የመአዓመ አብዮት መንገድን በመከተል እተፓዎች የሚፈጠሩበትን መንገድ ካልተከተለ እና የመአመ ማሻሻያዎችን (government reform) በአስቸኳይ ካልወሰደ በስተቀር፣ በገበያ ማሻሻያ (market reform) ያገኘውን የገበያ ኢኮኖሚ አድገት ሊያጣው ይችላል፡፡[17]

---

[15] የአሜሪካ መንግሥት የገንዘብ እና የኢኮኖሚ ነውጡን ለመቋቋም ወደ አንድ ትሪሊዮን ዶላር ከሕዝቡ በመበደር እና "የወገብ አጥብቅ" ዘመቻ በማካሄድ ባንክና ኮርፖሬሽኖቹን ከክስረት ሊያድን ችሏል፡፡ የመንግሥት እና የገበያ ማሻሻያዎችን ተፈጻሚዎች ማድረግ የሚችል የመልካም አስተዳደር መንግሥት መሆኑንም አረጋግጧል፡፡

[16] በዘመነ ቅኝ አገዛዝ (colonialism) እና የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ (necolonialism) ዘመን ይኽ ተፈጻሚ እንደነበር ይታወቃል፡፡

[17] በዚህ ረገድ ቻይና የገበያ ኢኮኖሚ እድገቷን ቀጣይነት እያጣች መሆኑን የሚያመላክቱ መረጃዎችን እና የቻይናን ሕዝብ ለመታደግ በመአዓመ አብዮት መንግሥታት በመወሰድ ላይ ያሉ እርምጃዎችን ከመጽሐፉ ማግኘት ይቻላል፡፡

የአፓርታይድና የማፊያ ኢኮኖሚ ሥርዓቶች በአፍሪካ ተከስተዋል፡፡ በቦሮች ደቡብ አፍሪካ፣ በሮዴሺያ ነጮች፣ በሞዛምቢክ እና አንጐላ ፖርቹጋሎች እና በአውሮፓ ቅኝ ገዢዎች የተመሠረቱት የአፓርታይድ (separate development) የመንግሥት እና የማፊያ ኢኮኖሚ ሥርዓቶች የአፍሪካዊውን ሰብአዊ መብቶች የገፈፉ፣ የመሬት ሀብቱን የዘረፉ፣ በሰው ጉልበት ብዝበዛ እና የወል ግድያዎችን በመፈጸም የሚካሄዱ ነበሩ፡፡ የአፍሪካውያኖቹ የነጻነት ትግል አላማው የነጮቹ ዝግ የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ግንባታዎች ሥርዓት ለአፍሪካውያኑም እንዲዳረስ ለማድረግ ነበር፡፡ ይኸንንም አፍሪካውያኑ ፀረ የቅኝ አገዛዝ (colonialist) ጦርነቶችን በመዋጋት፣ የመአዓመ አብዮት መንግሥታትን ድጋፍ፣ የኢትዮጵያ መንግሥት ፈር ቀዳጅነት እና የሶቪየት ኅብረት መንግሥትን ርዳታ በማግኘት ዓላማቸውን ለማሳካት ችለዋል፡፡[18]

የነጮቹ የአፓርታይድ የመንግሥታት እና የማፊያ ኢኮኖሚ ሥርዓቶች ለነጮቹ የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት ገንብተዋል፡፡ ሰብአዊ መብቱን የሚገፉት፣ ንብረቱን የሚዘርፉት፣ ጉልበቱን የሚበዘብዙት እና የወል ግድያዎችን የሚፈጽሙት በአፍሪካው ላይ ነበር፡፡ የአፍሪካውም ትግል በመአዓመ ስምምነት፣ የመአመ ሥርአት ተዘርግቶ፣ የሰብአዊ መብቶች ለሁሉም ዜጋ ተከብረው የገበያ ኢኮኖሚ ግንባታ እንዲካሄድ ነበር፡፡

በድህረ-ቀዝቃዛው ዘመን (ከሶቪየተቹ መፍረስ በኋላ) በአፍሪካ የአገር በቀል የአፓርታይድ መንግሥት እና የማፊያ ኢኮኖሚ ሥርዓቶች ተከስተዋል፡፡ እነዚህ ከላይ የታዩት የነጮቹ እና የቅኝ ገዢዎቹ የአፓርታይድ መንግሥት እና የማፊያ ኢኮኖሚ ሥርአቶች ከአፍሪካውያኑ የአገር በቀል የአፓርታይድ መንግሥት የተለዩ ናቸው፡፡ የሁቱው የአፓርታይድ መንግሥት፣ በናይጄሪያ የኢግቦዎቹ የአፓርታይድ መንግሥት ወይም በኢትዮጵያ የትግሬው የወያኔ መንግሥት ለሁቱው እና ለኢግቦው ሕዝብ እንዲሁም ለትግሬው የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት የገነባ አልነበረም፡፡ ቱትሲዎቹ በሩዋንዳ፣ ሌሎቹ ናዳጂሪያኖች ደግሞ በናይጄርያ የተዋጉት በረዋንዳና ናይጄርያ የመአመ ሥርዓትና የገበያ ኢኮኖሚ ግንባታ እንዲካሄድ ለማስቻል ነበር፡፡ ሆኖም ጦርነቱን የመሩት መንግሥታት ተፈላጊዎች የመልካም አስተዳደር መንግሥት ማሻሻያዎችን (government reform) እና የገበያ ማሻሻያዎችን (market reform) ፈጻሚዎች ባለመሆናቸው የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ሥርአት ሳይገነባ ቀርቷል፡፡

የጽዮኑ የአፓርታይድ እና የማፊያ ኢኮኖሚ ሥርዓት ከደቡብ አፍሪካ የአፓርታይድ እና የማፊያ ኢኮኖሚ ሥርዓት ተመሳሳይነት አለው፡፡ የአፓርታይድ ሥርዓቱ ለይሁዲዎቹ የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓትን ሲያስገኝላቸው የፍልስጥኤም አረቦችን ሰብአዊ መብቶች በመግፈፍ፣ ንብረታቸውን በመዝረፍ፣ ሕገወጥ የሆኑ የወል ግድያዎችን በመፈጸም እና ከመኖሪያ እና ከሥራቸው በማፈናቀል ነው፡፡ የአረቦቹ የትግል አቅጣጫ ያለመው አረቦች እንደ ይሁዲው የራሳቸው ቦታ እና የመአመ መንግሥት እና የገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት እንዲኖራቸው ለማድረግ ስለሆነ ፍልስጥኤሞቹ እና ይሁዲዎቹ የመጠፋፋት ጦርነቶች በተከታታይ ለማካሄድ ተገደዋል፡፡ በጦርነት ደግሞ የጋራ ችግራቸውን ፈጽሞ መፍታት አይችሉም፡፡[19]

ከነዚህ የአፓርታይድ እና የማፊያ ኢኮኖሚ ሥርዓቶች የወያኔ/ኢሕአዴግ የአፓርታይድ እና የማፊያ ኢኮኖሚ ሥርዓትን የተለየ የሚያደርገው የወያኔ/ኢሕአዴጉ የአፓርታይድ መንግሥት የተነሳው በኢትዮጵያ በ1942-1975 በመገንባት ላይ የነበረውን የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት በማፍረሱና በምትኩ የ(ትግሬ) ብሔር የአፓርታይድ እና የማፊያ ኢኮኖሚ ሥርዓት በመዘርጋት መሆኑ ነው፡፡

የወያኔ/ኢሕአዴግ የአፓርታይድ መንግሥት እና የማፊያ ኢኮኖሚው ከደቡብ አፍሪካው እና ከጽዮኑ እንደሁም ከሮዲሺያው የአፓርታይድ መንግሥት ሥርዓት የሚለየው እነዚህኞቹ በራሳቸው ሀብት እና የጦር ኃይል የሚመኩ ሲሆኑ የወደቁት ወይም የሚወድቁት የውጭ ኃይል ድጋፍ ባለመቀጠሉ እና የሥርዓቱ ጥፋት ሰለባ የሆነው አፍሪካዊው እውነቱን አውቆ ከምር በመቃወሙ ነው፡፡ የወያኔው ተጋላቢ የትሮይ ፈረስ መንግሥት የተፈጠረው የውጭ የትሮይ ፈረስ ጋላቢ መንግሥት በጠፋበት (ወይም በመአዓመ ቁጥጥር ሥር በዋለበት) ሰዓት ነው፡፡ ይኸም የወያኔውን የአፓርታይድ  እና የማፊያ ኢኮኖሚ ሥርዓተ መንግሥት ጊዜው ያለፈበት ወይም ጋላቢ (የሚገራው) ያጣ የትሮይ ፈረስ ያደርገዋል፡፡

---

[18] በጣሊያን ፋሺስቶች ይኸን የአፓርታይድ መንግሥት እና የማፊያ ኢኮኖሚ ሥርዓት በኢትዮጵያ ለመትከል ተሞክሯል፡፡ የጣሊያን የቅኝ ገዢ መንግሥት "የጋራ ጠላታችን የሆነውንና የኢትዮጵያን ሕዝብ ጨቁኖ የገዛውን አማራ እንውጋ የሚል" ጥሪ ለሕዝቡ አቅርቦ ነበር፡፡ ሆኖም የጣሊያንን የከፋፍለህ ግዛው ተንኮልን የተረዳው ሕዝብ በአንድነት በመቆም እና አጥብቆ በመዋጋት ጦርነቱን አሸንፎ ጣሊያኑን ካገር አስወጥቶታል፡፡ ለጣሊያን ያደረውን ባንዳ የ1942-1975ቱ መንግሥት (አፄ ምኒሊክ በመጀመሪያው የጣሊያን ጦርነት እንዳደረጉት) "ምህረት" በማድረግ የዜጋነት መብቶቹ እንዲከበሩለት አድርጓል፡፡

[19] የጋራ ችግራቸውን ለመፍታት የሚችሉት በሰላማዊ መንገድ በመስማማት፣ በመካካስ፣ ይቅር በመባባል እና በጋራ ሁሉንም ባቀፈ የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት ሥር መኖር ሲችሉ ብቻ ነው፡፡

VIII

ስለመአዓመ አብዮት፣ የመአመና የገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት አሠራር፣ እተፓ፣ ተጋላቢ እና ጋላቢ የትሮይ ፈረስ መንግሥታት፣ ሞብ፣ በእውነት እውቀት እየተመራ ሕዝበ-ውሳኔ የሚሰጥ ሕዝብ እና ስለኢትዮጵያ የ1942-1975 የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት የበለጠ ግንዛቤ እንዲኖረን በ2016 መባቻ (መግቢያ) ላይ የተፈጸሙ አራት ክስተቶችን እንመልከት፡፡ **መጽሐፉ እኒህን ክስተቶች ከምንረዳበት የሀሳብ መንገድ ጋር ያስተዋውቀናል፡፡**

(ሀ) የመአዓመ አብዮት መንግሥታት የሩዋንዳው ሕዝበ-እልቂት (genocide) በብሩንዲ ሊደገም ይችላል በማለት ዓለምን በቅድሚያ የመከላከያ ርምጃ እንዲወስድ አሳሰቡ፤
(ለ) የሩዋንዳው ፕሬዚዳንት ካጋሜ የሩዋንዳ ሕዝብ ለ3ተኛ ጊዜ እንዲመሩት ከመረጣቸው ለማገልገል ወደ ኋላ አልልም አሉ፣
(ሐ) የዓለም ባንክና የዓለም አቀፍ የገንዘብ ፈንድ በ2016 መጀመሪያ የቻይና ገንዘብ ዮዋን/ሬንሚንቢ የዓለም መገበያያ ገንዘብ (special drawing right፣ (SDR) currency) እንደሚሆን አሳወቀ፣ እና
(መ) በጥር 2008 (January 2016) የአሜሪካ እና የአውሮፓ ኅብረት መንግሥታት (የሰብአዊ መብት ድርጅቶች ጭምር) በኦሮምያ ክልል እየተከሰተ ያለው የሰብአዊ መብት ጥሰት አሳሳቢ ደረጃ መድረሱን ይፋ አድርገዋል፡፡

IX

የብሩንዲው አምባገነን መንግሥት በሞብ ተመርጦ አዲሱን የግዛት ዘመኑን መጀመሩን ዓለም አልተቀበለውም፡፡ የተጠበቀው የሕዝብ እልቂት ከመፈጸሙ በፊት የአፍሪካ ኅብረት ጥፋቱን ለመከላከል ይቻል ዘንድ የኅብረቱን ጦር ወደ ብሩንዲ ለመላክ ወስኗል፡፡[20] የብሩንዲው መንግሥት ጣልቃ ገብነቱን የሚቃወምና ለኅብረት ጦሩም ብሩንዲ እንዲገባ ፈቃድ የማይሰጥ መሆኑን ገልጧል፡፡[21]

X

የሩዋንዳው ፕሬዚዳንት ለ3ተኛ ጊዜ ሕዝቡ ከመረጣቸው የሚያገለግሉ መሆናቸውን ይፋ አድርገዋል፡፡ ሰውየው በ "ተወዳጅነት ማዕበል" እየተንሳፈፉ ስለሆነ፣ ያለባቸውን የሕግና የሥነ-ልቡና (የመሪ) ግዴታቸውን የዘነጉ ይመስላሉ፡፡ የሩዋንዳ መንግሥታቸው (የ1942-1975 የኢትዮጵያ መንግሥት የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓተ መንግሥት እንደገነባ) በሁለቱ የፕሬዚዳንትነት ዘመኑ በመአዓመ ስምምነት መሠረት የመአመ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓትን አልዘረጋም፣ ሰብአዊ መብቶችን (የንብረት ባለቤትነትን መብት ጨምሮ) የተከበሩ አላደረገም፣ በዚህ ምክንያት የገበያ ኢኮኖሚ ግንባታዎችን አላካሄደም፡፡ ከዚህ በመነሳት የብዙዎች ትንበያ ፕሬዚዳንት ፓል ካጋሜ በ3ተኛው የግዛት ዘመናቸው መጨረሻ ላይ (እስከዛ ከቆዩ) ምንም አይነት የመንግሥት ማሻሻያ (government reform) እና የገበያ ማሻሻያ (government reform) ሳይደረግ አሁን ያደረጉትን "ሕዘቡ ከመረጠኝ አገለግላለሁ" የሚለውን ዲስኩር ለ4ተኛው ጊዜ የፕሬዚዳንትነት ምርጫቸው እንደሚደግሙት ነው፡፡

XI

የቻይና ዩዋን/ሬንሚንቢ የዓለም እቃና አገልግሎት መለዋወጫ ገንዘብ [special drawing right (SDR) currency] መደረጉ ለቻይናም ሆነ ለዓለም የገበያ ኢኮኖሚ እድገት ትልቅ ጠቀሜታ አለው፡፡ ቻይናን የነጻ ገንዘብ ፖሊሲ (monetary policy) ለማካሄድ ያስችላታል፡፡ ሆኖም የመአዓመ አብዮት መንግሥታት ይኸን ሲፈቅዱ ቻይና የመአመ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት እና የመአመ ተቋማትን በቅጡ የዘረጋች አለመሆኗን ያውቃሉ፡፡ የቻይና የኮሚኒስት መንግሥት መአመ አይደለም፡፡ በመአመ 3ቱም ክፍላተ መንግሥቱ ውስጥ (ማለትም በሕግ አውጪው፣ ሕግ አስፈጻሚው እና ሕግ ተርጓሚው ክፍሎች ውስጥ) በነጻነትና ከኮሚኒስት ፓርቲው ጋር በመተባበር ለመሥራት የሚችሉትን እውነተኛ ተቃዋሚ ፓርቲዎች (እተፓዎች) "ማዋለድ" እና አብረው እንዲሠሩ ለማድረግ አልቻለም፡፡ ይኸን የመንግሥት ማሻሻያ (government reform) አለማድረግ ቻይና በገበያ ማሻሻያ (market reform) ያገኘችውን የገበያ ኢኮኖሚ ግንባታ እንድታጣው (እንድታፈርሰው) ያደርጋታል፡፡ መንግሥቱና የገበያ ኢኮኖሚ ግንባታው ቀጣይነት ላይኖረው ይችላል፡፡

[20] የቀረ ነገር ቢኖር የአፍሪካ መንግሥታት ወጪውን ለመሸፈን አቅም የሌላቸው በመሆኑ የመአዓመ አብዮት መንግሥታት የገንዘብ እና የቴክኒክ ርዳታ ይፋ የመውጣት ጉዳይ ነው፡፡

[21] በኮፊ አናን የሚመራው መአዓመ (የተባበሩት መንግሥታት) በሩዋንዳ የቱትሲዎቹ እና ለዘብተኛ ሁቱዎቹ እልቂት በሁቱዎቹ የአፓርታይድ መንግሥት ተፈጻሚ እንደሚሆን እየታወቀ የመከላከያ ቅድመ ዝግጅት ባለመውሰዱ መወቀሱ ይታወሳል፡፡ በየካቲት 2008 (February 2016) የዩሪ ሙሰቬኒ መንግሥት በምርጫ ማሸነፉን የተከታተሉት የመአዓመ አብዮት መንግሥታት (የአሜሪካን እና የአውሮፓ ኅብረት መንግሥታት) አጥላልተውታል፡፡ አምባገነኑ መንግሥት የሰብአዊ መብት ገፋፊ፣ የዲሞክራሲ እድገት እንቅፋት፣ የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት አፍራሽ እና የመአዓመ አብዮት ስምምነቶችን የጣሰ መሆኑን ያሳየ ነበር ብለውታል፡፡

በቻይና መአመ ባለመኖሩ እና የመአመ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት ባለመዘርጋቱ በዊጋ፣ ቲቤት፣ ሆንግ ኮንግ እና በመንግሥት ተቃዋሚዎች ጐራ የመንግሥቱ የሰብአዊ መብት ገፈፋው የዓለምን ትኩረት እያገኘ ነው፡፡ ቻይና የዓለም የጋራ ንብረት የባለቤትነት መብት (rights in global public goods) ሳይኖራት በደቡብ ቻይና ባሕር የዓለም መንግሥታትን የጋራ ንብረት መብት እየገፈፈች ትገኛለች፡፡ ከምስራቅ እና ደቡብ ምስራቅ እስያ አገሮች ጋር የገባችበትን የንብረት ባለቤትነት ውዝግብ በመአዓመ አብዮት ስምምነት መንገድ እየፈታችው አይደለም፡፡ የመአዓመ ስምምነቶችን በመጣስ፣ ለምሳሌ የዓለም ንግድ ድርጅትን (WTO) እና የሳይበር ደኅንነት (cyber security) ስምምነቶችን በመጣስ፣ ለአምባገነኑ የኢሕአዴግ መንግሥት የጥፋት እቃዎችን (economic bads፣ የጦር መሣሪያ፣ የኢንተርኔት መቆጣጠሪያ፣ የኮንትሮባንድ ንግድ፣ ወዘተ) በመሸጥ የኢኮኖሚ እቃዎችንና አገልግሎቶችን ከኢትዮጵያ እየወሰደች ነው፡፡

ቻይና በዚህ ሂደት በመአዓመ አብዮት መንግሥታት ርዳታ እና በወሰደችው የገበያ ማሻሻያ (market reform) ያገኘችውን የገበያ ኢኮኖሚ ግንባታ በመንግሥቱ ማሻሻያ (government reform) ማካሄድ አለመቻል ልታፈርሰውና የመንግሥቱም ቀጣይነት ያልተረጋገጠ ሊሆን ይችላል፡፡

XII

በመአዓመ አብዮት መንግሥታት እና ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ተቋማት የተጠቀሰውና አሳሳቢ የሆነው በኦሮምያ ክልል (Bantustan) የተከሰተው የሰብዓዊ መብት ገፈፋ በሁሉም የወያኔ ዘጠኝ የብሔር ክልሎች ተከስቷል፡፡[22] የኦሮሞዎቹ ተለጣፊ የብሔር ፓርቲዎች (ተለጣፊዎች)፣ የኦሮሞዎቹ ታማኝ ብሔርተኛ ተቃዋሚ ፓርቲዎች (ታብተፓዎች) እና የኦሮሞዎቹ ተቃዋሚ የብሔር ጦረኛ ፓርቲዎች (ተብጦፓዎች) በኦሮምያ ክልል ኦሮሞዎች ሰብአዊ መብቶቻቸውን እየተገፈፉ፣ ቋሚ ንብረቶቻቸውን (መሬት እና ህንፃ ወይም ጐጆ) እየተዘረፉ እና የወል ግድያ እየተፈጸመባቸው እንዲሁም ከሥራ እና ከመኖሪያቸው እየተፈናቀሉ መሆናቸውን ያስረዳሉ፡፡[23] የትግሬው (አግአዚ) ጦርና የደህንነት ኃይሉ፣ እንዲሁም የሕግ፣ የዜጋ፣ የሙያ እና የሥነ-ልቡናዊ ግዴታዎቹን ያልተረዳውና በራሱ ሕዘብ ላይ የዘመተው እና በትግሬው ጦር የሚመራው የብሔር ታጣቂው (የትግሬ አለቃውን ትእዛዝ "ሕግ ነው" እያለ) የኦሮሞ ገበሬውን እያፈናቀለ እና ብሶቱን በሕዘብ ትርኢት ለመግለጥ የወጣውን የኦሮሞ ተማሪ እና ወጣት እየረሸነ ነው በማለት ለዓለም እሮሮዋቸውን ያሰማሉ፡፡

በጉዳዩ የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት እየሰጠ ያለው መግለጫ የኦሮሞዎቹ ተጋላቢ የትሮይ ፈረሶች ከሚሰጧቸው መግለጫዎች የተለዩ ናቸው፡፡ የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት (እሱም ተጋላቢ የትሮይ ፈረስ መንግሥት ነው) በተለይ ለመአዓመ አብዮት መንግሥታት እያስረዳ ያለው የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት በኦሮሞ ክልል መንግሥት ሥራ ውስጥ አልገባሁም እያለ ነው፡፡[24] እንደ የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት አገላለጥ ቦታ የሚሸጠው፣ ገበሬውን የሚያፈናቅለው፣ እሱን ያልተቀበሉትን ኦሮሞዎች እና ኦሮሞ አይደላችሁም በማለት ኦሮሞ ያልሆኑትን የክልል ነዋሪዎች ለ24 ዓመታት ፍዳቸውን የሚያሳያቸው የኦሮሞ ተለጣፊው፣ ታብተፓው፣ ተብጦፓው እና በእነዚህ ኃይሎች የሚነዳው የኦሮሞ ሞብ እና የሞራል ፀፀት በሽታ (moral hazard) ተጠቂው ነው፡፡[25]

የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት እንደሚያስረዳው በኦሮምያ ክልል ትግሬዎች የቦታ ካርታ ያገኙት ለክልሉ (ተለጣፊ) መንግሥት ጥያቄ በማቅረብና ፈቃድ በማግኘት ሲሆን የካርታው ፈቃድ ላይ ፊርማውን ያሳረፈው የክልሉ መንግሥት (ኦህዴድ) እና የሳሎን ካቢኔው ተለጣፊ መንግሥት ባለሥልጣን ነው፡፡ የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት እንደሚያስረዳው በኦሮምያ ክልል ትግሬዎቹ ያላቸውን ቤት፣ ንብረት፣ የንግድ ማዕከል፣ የኮንትሮባንድ ንግድ፣ ወዘተ የክልሉ እና የሳሎን ካቢኔ

---

[22] በእያንዳንዱ በወያኔ የተፈጠረው ክልል ለኦሮምያ ክልልና ለኦሮሞዎቹ የተሰጠውን ማብራሪያ (ተመሳሳይነት ስላላቸው) መስጠት ይቻላል፡፡ በኦሮምያ ክልል የመብት ጥሰቱ ያሳሰባቸው ወገኖች ስለሌሎቹ የክልሎች የመብት ጥሰቶች ያላነሱት እና አሳሳቢነቱን ያልገለጡት ጥፋቱ ስላልተፈጸመ ወይም ስለመብት ጥሰቶቹ ስላላወቁ አይደለም፡፡ ለኢትዮጵያኑ ያወቁ መሆኑን በተደጋጋሚ ገልጠዋል፡፡ ኢትዮጵያውያኑን ሊያሳስቧቸው የሚፈልጉት የችግሩ መፍቺያ ቁልፍ በእጃቸው ያለ መሆኑን ነው፡፡ ለዛ ደግሞ ስለአንዱም ባንቱስታን (የብሔር ክልል) ችግር መግለጥ ለማሳሰቢያነት በቂ ነው፡፡ በሁሉም ክልሎች ስላሉት ተመሳሳይ የመብት ጥሰቶች ማወቅና ማሳወቅ የኢትዮጵያውያኑ የዜግነት፣ የሕግ፣ የሙያ እና የሥነ-ልቡናዊ ግዴታቸው ነው፡፡

[23] ተለጣፊዎቹ፣  ታብተፓዎቹ እና ተብጦፓዎቹ ሁሉም ተጋላቢ የትሮይ ፈረሶች ናቸው፡፡ የውጭ ኃይል (ጋላቢ የትሮይ ፈረስ መንግሥት) ጥይት ካላቀበላቸው፣  ስንቅ ካልሰፈረላቸው እና አመራር ካልሰጣቸው (ካልገራቸው) በራሳቸው ምንም አይነት ለውጥ ማምጣት የሚችሉ አይደሉም፡፡

[24] በድህረ ቀዝቃዛው ጦርነት ዘመን ደግሞ መአዓመ (የተባበሩት መንግሥታት) እና የመአዓመ አብዮት መንግሥታት የትሮይ ፈረስ ጋላቢ መንግሥታቱንና ተጋላቢ የትሮይ ፈረሶቹን መቆጣጠር የቻሉበትና ፀረ-አሸባሪዎች ጦርነቶችን የሚዋጉበት የእድገት ደረጃ የደረሱበት ዘመን ነው፡፡ የዚህ ግንዛቤ የሚያመለክተው በድህረ ቀዝቃዛው ጦርነት ዘመን ተጋላቢ የትሮይ ፈረሶቹ በመአዓመ ፍጹም ቁጥጥር ሥር የወደቁ መሆናቸውን ነው፡፡

[25] ተብጦፓውን በበደኖ፣ ጨለንቆ፣ አርባጉጉ፣ አሰቦት ገዳም፣ በቡሬ፣ ወለጋ፣ ምዕራብ ሸዋ፣ ወዘተ በአማሮች ላይ (በአሜሪካ እና የአውሮፓ ኅብረት መንግሥታት፣ ኢሰመጉ፣ የሰብአዊ መብት ተቋማት፣ የጋዜጠኞች ማኅበራት፣ ወዘተ) የተረጋገጡትን የወል ግድያዎች፣ ሰብአዊ መብት ገፈፋዎች እና ንብረት ዝርፊያዎች ፈጻሚ መሆኑን በማረጋገጣችን "አሸባሪ ብለን በመፈረጅ ከፖለቲካ ጨዋታው አስወጥተነዋል፣ እያደንን በጥፋቱ እየቀጣነው እንገኛለን" ይላል የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት፡፡ አሁን ደግሞ በተመሳሳይ ሁኔታ ተለጣፊውን እና ታብተፓውን በጥፋቱ እየቀጣው መሆኑን የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት ለዓለም እያሳወቀ ይገኛል፡፡

መንግሥታት ፈቃድን በማግኘት እና ለአገልግሎቱ ከፍለው ነው። በኦሮምያ ክልል ትግሬዎች ያገኟቸው ንብረቶች በገንዘባቸው ያስገነቧቸው ሲሆን በሙሉ የክልሉን የመንግሥት ፈቃድ በማግኘት እና ገንዘባቸውን በመክፈል መሆኑን የወያኔ/ኢሕአዴግ መግንሥት ያስረዳል። ለዚህም የኦሮሞ ክልል እና የሳሎን ካቢኔው ተለጣፊ መንግሥት ባለስልጣናት የተሰጣቸው መረጃ መኖሩንም ይገልጣል።[26] ለዚህም በኦሮሞ ክልል እና የሳሎን ካቢኔው ተለጣፊ መንግሥት የተሰጡ የቦታ ካርታ፣ የቤት ባለቤትነት ሠርቲፊኬት፣ የንግድ ሥራ ፈቃድ፣ የግብር ክፍያ ደረሰኞች፣ ወዘተ በዋቢነት (በመረጃነት) ያቀርባሉ። ስለዚህም፣ ይላል የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት፣ "የኦሮሞ ተለጣፊዎቹ (የክልሉ እና የሳሎን ካቢኔው መንግሥታት)፣ ታብተፓዎች አና ተብጦፓዎቹ የኦሮሞ ሕዝብ በወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት ሰብአዊ መብቶቹ ተደፍረዋል፣ ንብረቱ ተዘርፏል፣ ወዘተ የሚሉት ውሸት እና መረጃ የሌለው አሉባልታ" ነው። በወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት አገላለጥ በሕገ ወጥ መንገድ ቦታ የሚሸጡት የኦሮሞ የክልሉ እና የሳሎን ካቢኔው ተለጣፊ መንግሥታት ናቸው።

ስለኦሮሞ ተማሪዎችና ወጣቶች እንደሁም የኦሮሞ ገበሬዎች ግድያ፣ እስር እና እንግልት የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት የሚለው ይኸ ጥፋት የደረሰባቸው ስለ ኦሮምያ ነጻነት እና ስለ ኦሮሞዎች ጥቅም መከበር ባነሱት ጥያቄ ምክንያት አይደለም። ይኸ "በደል" የተፈጸመባቸው የተለጣፊዎቹ (የክልል እና የሳሎን መንግሥቱ)፣ የታብተፓዎቹ እና የተብጦፓዎቹ "ሞብ" በመሆን ኦሮሞ ባልሆኑ የክልሉ ነዋሪዎች ላይ በፈጸሙት ሰብአዊ መብት ገፈፋ፣ ንብረት ዝርፊያ እና ንብረት ማውደም እንዲሁም ከመሥሪያ እና ከመኖሪያ የማፈናቀል የጥፋት ሥራ ጋር በተገናኘ ከሕግ አስከባሪው ታጣቂ ጋር በተደረገ ግጭት ነው። የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት እንደሚያስረዳው የኦሮሞ ተማሪዎቹ የክልሉ ዩኒቨርስቲዎች የኦሮሞዎች ንብረት ናቸው ብለው እንደሚያምኑ እና በዛ የሚማሩና የሚሠሩ ኦሮሞ ያልሆኑ ዜጐችን መብቶች ገፋፊዎች ናቸው።

በደል የደረሰበት የኦሮሞ ሕዝብ በአንድ በኩል በተለጣፊው፣ በታብተፓው እና በተብጦፓው የወያኔ/መወቤካው መንግሥት ከልሎ ለሰጠው አገርና ባንዲራው ተዋደቅ እየተባለ በሞብነት የአጥፍቶ መጥፋት ጦርነቶችን እንዲዋጋ ተደርጓል። በሌላ በኩል ደግሞ በኦሮምያ ክልል የሚኖሩትን ኦሮሞ ያልሆኑ የብሔር አባላት ሰብአዊ መብት ገፈፍክ፣ ንብረት ዘረፍክ፣ ንብረት አወደምክ፣ የወል ግድያ ፈጸምክ፣ የሰዎችን ህይወት አደጋ ላይ ጣልክ እየተባለ በወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት (በፌደራል መንግሥቱ) የቁም ስቃዩን እያየ ይገኛል። የሞብ መመራምር (theorem) እንደሚያስረዳው (መጽሐፉን ተመልከት) ሞብ ሁልጊዜ የአጥፍቶ መጥፋት ጦርነቶችን የሚዋጋና በራሱ ላይ ጥፋትን የሚያመጣ የሕዝብ ክፍል ነው። ሞብ በእውነት እውቀት ላይ ተመሥርቶ ሕዝበ-ውሳኔ የሚሰጥ ሳይሆን በጥፋት መሪዎቹ (ማለትም በተለጣፊው፣ ታብተፓው እና ተብጦፓው) ላይ ባለው እምነት ጥፋትን እንዲፈጽም የሚነዱት ነው፣ ሌላውን አጥፍቶ በራሱ ጠፊ ነው።

*የወጣቱ የብሔር ፓርቲዎች "ሞብ" መሆን እና የሞራል ዝቅተት በሽታ (moral hazard) ተጠቂነት*

6 ጥር 2008 (15 January 2016) ጠዋት ላይ ደመናው ለእግር ጉዞ አመቺ በመሆኑ ወደ አራት ኪሎ አቅጣጫ በመሄድ ላይ እንዳለሁ የቀበና ድልድዩን እንደተሻገርኩ አንድ ወጣት ያስቆመኝና "የህንድ ኤምባሲ የት ነው?" ብሎ ይጠይቀኛል። "ፊት ሳውቀው ከፊታችን ያለው መንገድ ላይ ወደ አቧሬ ታጠፍ እንዳልክ ነበር" እለውና ቤንዚን ማደያው ጋ ያሉት ሰዎች የቆዩ ስለሆኑ ሊያረጋግጡለት እንደሚችሉ እነግረዋለሁ። አረጋገጡለት መሰለኝ ፈጠን እያለ ይደርስብኝና መታጠፊያውን እንዳሳየው አብረን መሄድ እንጀምራለን።

"ለምንድነው ወደ ህንድ ኤምባሲ የምትሄደው?" ብዬ ስጠይቀው ከጂማ ዩኒቨርስቲ የተመረቀ መሆኑን እና በቅርቡ የህንድ መንግሥት የስኮላርሺፕ ማስታወቂያ ስላወጣ ለድኅረ-ምረቃ ትምህርት ለማመልከት እንደሆነ ይነግረኛል። ጊዜው በኦሮምያ ክልል የኦሮሞ ተማሪዎች እና ወጣቶቹ በሁለት ወገን ጉዳት እየደረሰባቸው ያለበት ነው።[27] በአንድ በኩል የኦሮምያ ተጋላቢ የትሮይ ፈረሶች (ማለትም ተለጣፊው ኦህዴድ፣ ታብተፓው፣ ተብጦፓው አና የብሔር እና የሃይማኖት ማርክሲስቱ) "ወያኔ ከልሎ ለሰጠህ አገርህ (ክልልህ) እና ለኦሮምያ ባንዲራህ ሙት" ይሉታል። በሌላ በኩል የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥቱ (እንዲሁም የመወቤካው እና የሳሎን ካቢኔው መንግሥት ወይም የፌደራል መንግሥቱ) ደግሞ በኦሮምያ ክልል ነዋሪ የሆነውን ኦሮሞ ያልሆነ ሕዝብ ሰብአዊ መብቶቹን ገፈፋችሁ፣ ኦሮሞ ያልሆኑ ተማሪዎችን እንዳይማሩ አደረጋችሁ፣ ኦሮሞ ያልሆነውን ሰው ንብረት ዘረፋችሁ፣ የልማት ተቋማትን አፈረሳችሁ እና የሕዝቡን ደኅንነት አደጋ ላይ ጣላችሁ እየተባሉ በትግሬው አግአዚ ጦርና በሱ ሥር መወቤካው ባዋቀረው እና

[26] ወያኔዎቹ ይኸን ሕገ-ወጥ ሥራ የሚፈጽሙበትን ገንዘብ እና ሥልጣን ከየት አመጡት ለሚለው ጥያቄም የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት መልስ አለው። ለኢትዮጵያ ሕዝብ የገንዘባቸውን እና የሥልጣናቸውን ምንጭ አያሳወቁት እንጂ (ይኸም የመንግሥትን ህላፊነት/ግዴታ አለመወጣት ነው) ገንዘቡን ለሰጧቸው የመአዓመ አብዮት መንግሥታት ጉዳዩን ሁሉ እንዳስረዱ ይገመታል። ተለጣፊው፣ ታብተፓው እና ተብጦፓው በቁጥጥራችን ሥር ያለ ስለሆነ በዚህ ጉዳይ ላይ ሊጠይቀን አይገባም የሚሉም ይመስላሉ። ሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት ሞብ ተደርጐ ተወስዷል።

[27] ከላይ እንደገለጥነው የአሜሪካ አና የአውሮፓ ኅብረት "ስለ ኦሮምያ ክልል የሰብአዊ መብት ጥሰት" ይናገሩ እንጂ ጥሰቱ ባሁኑ ጊዜ በሁሉም ክልል እና ብሔር ወጣት ላይ ተከሳች ነው። ትግሬ በመሆኑ በመወቤካው መንግሥት በሕገ-ወጥ መንገድ ተጠቃሚ የሆነ፣ አማራ በመሆኑ በብአዴን መንግሥት በሕገ-ወጥ መንገድ ተጠቃሚ የሆነ፣ ወዘተ (በአጠቀላይ የብሔር አባል በመሆኑ ተጠቃሚ የሆነ የሞራል ፀፀት በሽታ (moral hazard) ተጠቂ ነው። በዚህ ድርጊቱ ሕጋዊ እና ሥነ-ልቡናዊ ግዴታዎቹን ባለመወጣቱ በመአመ ፍርድ ቤት ተጠያቂ ነው።

ያለበትን ሕጋዊ፣ ሙያዊ እና ሥነ-ልቦናዊ ግዴታዎቹን ያልተረዳው (ወይም አውቆ አጥፊ የሆነው) የብሔር ታጣቂ እየተገደሉ፣ እየታሠሩ፣ እየተሰቃዩ እና እየተሰደዱ ያለበት ጊዜ በመሆኑ እሱ ውጭ ሄዶ ለመማር እንዴት መንግሥቱ እንደፈቀደለት ጠየቅሁት፡፡ ተማሪዎች እና የመንግሥት ሠራተኞች በመንግሥቱ አመራር ሰጪነት በብሔር ፓርቲዎች የተደራጁ በመሆናቸው "የየትኛው የብሔር ፓርቲ አባል ነህ?" ብዬም ጠየቅሁት፡፡ ወጣቱ በጂማ ዩኒቨርስቲ ሲማር በኦሮሞ ብሔርተኞቹ በሚፈጠሩ የጥፋት ሥራዎች ትምህርት በየጊዜው እንደሚቋረጥና በችግር ትምህርቱን የጨረሰ መሆኑን ነግሮኛል፡፡ ለጠየቅሁት የብሔር ፓርቲ አባልነት ግን የሰጠኝ መልስ የመልሶ ጥያቄ ነበር፡፡ "እርስዎ ኢትዮጵያዊ አይደሉም እንዴ?" ብሎ ነበር የጠየቀኝ፡፡

የኢትዮጵያን የፖለቲካ ምኅዳር የሚቆጣጠሩት/የተቆጣጠሩት ተጋላቢ የትሮይ ፈረሶች (ደርግ፣ ወያኔ፣ ሻቢያ፣ ጀብሀ፣ ኦነግ፣ ተለጣፊዎች፣ ታብተፓዎች እና ተብጦፓዎች እንዲሁም የብሔር እና የሀይማኖት ማርክሲስቶች) ከፈጠሯቸው ጥፋቶች ዋናው አዲሱን ትውልድ ሞብና በማራል ዝቅጠት በሽታ (moral hazard) ተጠቂ እንዲሆንና በአጥፍቶ መጥፋት ጦርነት እራሱን እና አገሩን እንዲያጠፋ ማድረግ ነው፡፡[28]

የኦሮሞ ወጣት (እንዲሁም የማንኛውም ብሔር ወጣት) የእውነቱን እውቀት ባለመሻቱ እና ባለማወቁ በብሔር ተጋላቢ የትሮይ ፈረሶቹ የሚነዳ "ሞብ" ሆኗል፡፡ በዚህም ምክንያት የኦሮሞ ወጣት በራሱና በሌላውም ዜጋ ላይ ጥፋቶችን ፈጻሚና አጥፍቶ ጠፊ ተደርጓል፡፡ የወያኔ ደጋፊ የሆነው የትግሬ ወጣት እና የተለጣፊው ደጋፊዎች ወጣቶች ደግሞ የሞራል ዝቅጠት በሽታ (moral hazard) ተጠቂዎች ተደርገዋል፡፡ በአፓርታይድ ሥርዓቱ ባለሥልጣኖች ወይም በተጋላቢ የትሮይ ፈረስ መንግሥቱ የንብረት ባለቤቶች፣ "ማን አለብኝ" እና "ሁሉም በእጄና በደጄ" ባዮች እንዲሆኑ ተደርገዋል፡፡

ባሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ የሚታዩት ሁለቱም የወጣቶች አይነቶች የቅድመ-መብት ዓለም ነዋሪዎች ሲሆኑ በድኅረ-መብት ዓለም (ወይም በመአዓመ አብዮት ዘመን ዓለም) ቦታ የላቸውም፡፡[29] በድኅረ-መብት ዓለም ውስጥ ሞቦች እና የሞራል ዝቅጠት ተጠቂዎች በመአዓመ እና መአመዎች ቁጥጥር ሥር ይውላሉ፣ ለጥፋታቸውም ሕጋዊ፣ ሙያዊ እና ሥነ-ልቡናዊ ግዴታዎቻቸውን እንዲወጡ ይገደዳሉ፡፡

ባሁኑ ወቅት የመአዓመ አብዮት መንግሥታት ምን አዲስ ነገር ተከሠተ እና ነው በኦሮምያ የወያኔ ክልል የተፈጸመው የሙብት ጥሰት ያሰጋናል የሚሉት? በወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት በኩል ሲታይ የጉዳዩ እንደምታ ወይም አትኩሮት ያገኘ አይመስልም፡፡ የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት ለመአዓመ አብዮት መንግሥታት እያለ ያለው የመአዓመ አብዮት መንግሥታት በሰጡኝ ገንዘብ (ለ 24 ዓመታት ለትግሬዎቹ እንዳደረኩላቸው አሁን ደግሞ) ለ"አማሮቹ" አፓርትሜንቶች ሠርቼ ማከፋፈል ጀምሬአለሁ ነው፡፡[30] ለዚህም ማረጋገጫ የሚያቀርበው በሚቆጣጠረው የኢቲቪ እና ሬዲዮ ፕሮግራሞች በሂደቱ ተጠቃሚ የሆኑ "አማሮችን" ምስክርነት ነው፡፡ ይኸም እንደ ሌሎቹ የወያኔ/ኢሕአዴግ ቀረባዎች ውሸት እና አሳሳች መልእክትን የሚሰጥ ነው፡፡

አንደኛ፣ በኢቲቪ እና ሬዲዮ እየቀረቡ የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥትን የሚያቆላጽሱት የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት የግል እና የጋራ ንብረታቸውን የዘረፋቸው አማሮች አይደሉም፡፡ እነሂ አሁን ንብረት በወያኔ እየታደላቸው የሚገኙት አማሮች (ኢሕአዴግ እንደሚለው) በሆብሰን ምርጫዎቹ (ኦነግ፣ የኦሮሞ እስላም ፓርቲ፣ ኦብነግ፣ ወዘተ) በበደኖ፣ አርባጉጉ፣ አሰቦት ገዳም፣ ጂማ፣ አምቦ፣ ቡሬ፣ ወለጋ ወዘተ በግፍ የተገደሉትና የዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ድርጅቶች፣ ኢሰመጉ፣ የጋዜጠኞች ማኅበር እና የመአዓመ አብዮት መንግሥታት ያረጋገጧቸው የወል ግድያዎች ሰለባዎች ልጆች አይደሉም፡፡[31]

ሁለተኛ፣ እነዚህ በወያኔ ሚዲያ እየቀረቡ መንግሥቱ ንብረት እንድንገዛ እና የባንክ ብድርም እንድናገኝ ፈቀደልን የሚሉት "አማሮች" ተፈቅዶልናል የሚሉትን ንብረት እና የባንክ እዳ በእጃቸው ያስገቡ አይደሉም፡፡ ምናልባት የእውነቱ እውቀት

---

[28] "ሞብ" የሚባለው (በእውነት እውቀት ሳይሆን) በትሮይ ፈረስ ፓርቲዎች ባለሥልጣኖች ላይ ባለው እምነት በመመራት ሕዝብን እና አገርን አጥፍቶ ጠፊ ነው፡፡ በሞራል ዝቅጠት ተጠቂ የሆነውም (የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት አባልና ደጋፊ እንዲሁም ተጠቃሚ የሆነው ወጣት) "የሌባ አይነደረቅ፣ መልሶ ልብ ያደርቅ" ሆኗል፡፡ ሞቡም ሆነ የሞራል ዝቅጠት በሽታ ተጠቂው ተማሪ እና ወጣት መንግሥቱ እና እሱ በፈጠሩት ለሕግ፣ ሙያ እና ሥነ-ልቡናዊ ግዴታቸውን አለመወጣት በመአዓመ እና የመአመ ፍርድ ቤቶች ተጠያቂዎች መሆናቸውን የተገነዘቡት አይመስሉም፡፡

[29] እነሂ "ሞቦችና የሞራል ዘቅጠት በሽታ ተጠቂ የሆኑ ወጣቶች ከተጋላቢ የትሮይ ፈረስ መሪዎቻቸው ጋር ለቅድመ መብቱ ዓለም ወደኋላ መቅረት እና መውደቅ ምክንያቶች መሆናቸውን ልብ-ልንለው ይገባል፡፡

[30] የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት ለኢትዮጵያ ሕዝብና ለዓለም የሚያስተላልፋቸው መልእክቶች የተለያዩ ናቸው፡፡ ለኢትዮጵያውያኑ በሚያስተላልፈው መልእክት ለሕዝቡ አሳቢ እንደሆነና በገንዘቡ ቅድመ-ግንባታ ሥራዎችን (infrastructure) እየሠራና ንብረቶችን እየገነባ ለሕዝቡ እያከፋፈለ መሆኑን ነው፡፡ ይኼ ተፈጻሚ የሚሆነው ሕዝቡ ገንዘቡን ከየት አመጣው ብሎ የመጠየቅ ግንዛቤ ባጣበት ሁኔታ ነው፡፡

እስከ ግንቦት 2013 ድረስ የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት በሙሉ ኃይሉና በመወቤካው አመራር የመንግሥት አገልግሎት ይሰጥ የነበረው ለወያኔ፣ ደጋፊው ለሆነ ትግሬ እና ለተለጣፊዎቹ ባለሥልጣናት ነበር፡፡ የወያኔ/መወቤካው የምሥጢር መንግሥት ዓላማው የትግራይን ነጻነት እና የትግሬውን ጥቅም ማስጠበቅ ስለሆነ ይኸንኑ አላማውን ተፈጻሚ አድርጓል፡፡ ከግንቦት 2013 በኋላ፣ ይኸን አላማውን ተፈጻሚ ካደረገ በኋላ የብሔር ተለጣፊ እና የሆብሰን ምርጫዎቹን ሁሉ በጸረ-አማራነት እንዳላስተባበረ በመምሰል አሁን ደግሞ እነሱን በአማራው ላይ ለተፈጸሙት ጥፋቶች ተጠያቂ በማድረግ "የአማራው እንባ አባሽ" ሆኖ ቀርቧል፡፡

[31] እነሂ አማሮች እነኩማ ደመቅሳ (ኦሕዴድ) ከክልላችን ውጡሉን እያሉ ከመኖሪያቸው የመኖር መብታቸውን በመግፈፍ ያባረሯቸው እና በአዲስ አበባ ደግሞ የሳሎኑ ካቢኔ ተለጣፊዎች የሠራተኛ እና የመኖር መብታቸውን በመግፈፍ ከሥራቸውና ከመኖሪያቸው ያፈናቀሏቸው "አማሮች" አይደሉም፡፡

ግንዛቤ ስለሌላቸው በኢቲቪ እና ሬዲዮ እየቀረቡ ያጨበጭባሉ እንጂ ብዙዎቹ (እንደ ባዶ ኪሳቸውን ይዘው አዲስ አበባ ገብተው በጠመንጃ ሚሊዮነር የሆኑት ትግሬዎች አይደሉም) ለብድራቸው የሚከፍሉት ገንዘብ የላቸውም፡፡ ባንዳንድ ድርጊቶች ማረጋገጥ እንደሚቻለው "አማሮቹ" ከወያኔ እሥር ካመለጡ በመንግሥቱ ድጋፍ ከፍለን ለመግዛት እድሉን ሰጥቶናል የሚሉትን ንብረት አሳልፈው ለትግሬው ማፊያ ሻጮች ናቸው፡፡[32] በብዙ መረጃዎች ማረጋገጥ እንደሚቻለው አማሮቹ ከገበያ ዋጋ በላይ ከፍለው (ጉቦ ጭምር ከፍለውበት) ያገኙትን ንብረት ይዘረፋሉ፣ የተበደሩትን ገንዘብ አልከፈላችሁም ተብለው ይታሰራሉ፡፡[33]

ይኸን ተከትሎ የጥር 2008 (January 2016) የኦሮሞ እና አማሮች የለንደኑ "ተባብረን ወያኔን እናስወግድ" ሕዝበ-ትርኢት ለወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት የፕሮፖጋንዳ ሥራ በግብአተ-ምርትነት አገልግሏል፡፡ ለእንግሊዝ እና ለመአዓመ አብየት መንግሥታት "በፊት አማሮቹን ለመታደግ ኦነግ እና የኦሮሞ እስላም ፓርቲዎችን "አሸባሪ" በማለት ከኢትዮጵያ ፖለቲካ እንዳገድኳቸው የታወቀ ነው፡፡ አሁን ደግሞ የኦሮሞ ተለጣፊዎቹ፣ ታብተፓዎቹ እና ተብጦፓዎቹ፣ አማሮቹን ተጠቃሚ የሚያደርገውን ሥራ በመሥራቴ በኦሮሞ ሞባቸው መሣሪያነት ሊያደናቅፉ ሲሞክሩ በሕግ እና በታጣቂዎቼ አማካኝነት እየተቆጣጠርኳቸው ነው" የሚሉ መልእክቶችን እያስተላለፈ መሆኑ በግልጽ ይታያል፡፡ በሌሎቹም ክልሎች ቢሆን የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት በመስጠት ላይ ያለው የውዝግቦቹ መግለጫ ከኦሮምያ ክልሉ መግለጫ ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ ለጥፋቶቹ ተጠያቂ የሚያደርጋቸው የየብሔሩ ተለጣፊዎቹን፣ ታብተፓዎቹን እና ተብጦፓዎቹን ነው፡፡ እነዚህ ደግሞ ለወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት **የሆብሶን ምርጫዎቹ** ናቸው፡፡[34]

የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት በውሸት እና አሳሳች መረጃ ተጠቃሚ መሆኑ የተረጋገጠ ነው፡፡ በዚህ መጽሐፍ የተብራራው አንዱ መመራምር (theorem) የሚያስረዳው ማንኛውም ሰው፣ ቡድን ወይም መንግሥታዊ ድርጅት በውሸት እና አሳሳች መረጃ በመጠቀም ያለመውን ግብ አይመታም፡፡ በሚፈጽመው ሕገ ወጥ ሥራ ሕዝቡን ያልተፈለገ ምርጫ (adverse selection) እንዲያደርግ ይገፋፋዋል እና የሥነ-ልቡና ቀውስ (moral hazard) ውስጥ ይከተዋል፡፡ በዚህ መንገድ ግቤን እመታለሁ ብሎ ቢሞክር (በሌላው መመራምር ምዕራፍ 19ን ተመልከት) ማስረዳት እንደሚቻለው ግቡን ለመምታት እልፍ የዶላር ወጪ ማውጣት ይኖርበታል፡፡[35]

መጽሐፉ ግልፅ ካደረጋቸው ጉዳዮች አንዱ በወያኔ/መወቤካው ሥርዓተ መንግሥት (1991-2013) ወያኔ እና የሥርዓቱ ደጋፊ ትግሬ ባለንብረት፣ ባለሥልጣን፣ "ማንም አይነካኝ" ባይ (immunity አለኝ ባይ) እና "ሁሉም በእጄ እና በደጄ" ነው (ባለ

---

[32] በዚሕ መጽሐፍ (በተለየ ካልተገለጠ በስተቀር) "አማሮች" የሚባሉት እራሳቸውን በአማርኛ ቋንቋ የሚገልጡ፣ የኢትዮጵያን የጋራ ሥልጣኔ የገነቡ፣ ኢትዮጵያዊነትን እና ሰብአዊነትን የማንነታቸው መገለጫ ያደረጉ፣ ብሔርተኝነትን ወይም ዘረኝነትን የሚቃወሙ፣ የ1942-1975 የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓቱንና ቀጣይነቱን የተቀበሉትን ሁሉ ነው፡፡ እነሂ "አማሮች" ብሄራቸውን ወይም ሀይማኖታቸውን ለጥፋት ሥራ አያውሉትም፡፡ ከብሔራቸው ወይም ሀይማኖታቸው ማንነት ይልቅ ለሰብአዊነት እና ኢትዮጵያዊነት ቅድሚያ የሚሰጡ ናቸው፡፡ በተቃራኒው ወያኔዎቹ፣ ተለጣፊዎቹ፣ ታብተፓዎቹ እና ተብጦፓዎቹ ቅድሚያ የሚሰጡት ለብሔር፣ ጐጥ እና የእምነት ተከታይ አባሎቻቸው ነው፡፡ አማራ፣ ጉራጌ፣ ኦሮሞ፣ ወዘተ የሚሉት የብሔር መለያዎች የተሟላ እና ሕጋዊ ፍቺ (precise or legal definition) ያላቸው አይደሉም፡፡ በወሎ እና በአንዳንድ አካባቢዎች "አማራ" ማለት "ክርስቲያን" ማለት ነው፡፡ የሐረር ቆቱዎች "አማራ" የሚሉት "አማርኛ ተናጋሪ የሆነውን ክርስቲያንና የሸዋ ኦሮሞውን ጭምር ነው፡፡ የወለጋ እና የደቡብ ሕዝቦች የብሔር እና የሐይማኖት ማርክሲስቱ ደግሞ "አማራ" የሚለው አጥብቦ የኦርቶዶክስ ሀይማኖት ተከታይ የሆነውን ብሔረ አማራውን ነው፡፡ የወለጋ የብሔር እና የሀይማኖት ማርክሲስቱ የሸዋን "ኦሮሞ" ንጹህ ያልሆነ ከአማራው የተዳቀለ እና በፖለቲካ አቋሙም ለዘብተኛ አድርጐ ያየዋል፡፡ ወያኔዎች ደጋፊያቸው ያልሆነውን ትግርኛ ተናጋሪ "ሀማሴን" ሲያደርጉት ሻቢያም እንዲሁ ደጋፊው ያልሆነውን ትግርኛ ተናጋሪ "ትግሬ" ያደርገዋል፡፡ በ1936 – 1941 ኢትዮጵያን የተቆጣጠረው የፋሺስት ኢጣሊያ ጦር (መንግሥት) "አማራ ለዘመናት የጨቆናችሁ የጋራ ጠላታችን ስለሆነ አብረን እና ተባብረን እናጥፋው" ብሎ አማራ አይደሉም ያላቸውን ብሔሮች እና እሰላሞችን ለማስተባበር ሞክሮ ነበር፡፡ ነገር ግን እኒህ ወገኖች በጣሊያን ማባበያ ሳይደለሉ ሁሉም "አማሮች" ሆነውበት እና አጥብቀው በመዋጋታቸው ኢትዮጵያን ነጻ ሊያወጧትና ኢትዮጵያዊውንም ሰብአዊ ክብሩን ሊጠብቁለት ችለዋል፡፡

[33] አንዳንዶቹ ከዚህ ችግር ለማምለጥ የሚሞክሩት ከፍለው እንዲያገኙት ተደረጉትን ንብረት አሳልፈው ለትግሬ ማፊያው በመሸጥ ነው፡፡ የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት በወያኔዎች ቁጥጥር ሥር ስለሆነ የትግሬ ማፊያው ያለምንም ለመንግሥት ክፍያ የንብረቱ ባለቤት ይሆናል፡፡

[34] የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት "የሆብሶን ምርጫ" ማለት የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ግንባታ ሥርዓት በማፍረስ፣ በሰብአዊ መብት ገፈፋው፣ ንብረት ዝርፊያው፣ ያለ ሕግ እና የወል ግድያው ከወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት የከፋ ወይም ይበልጥ (የባሰ) አጥፊ መንግሥት ማለት ነው፡፡

[35] የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት የውሸት እና አሳሳች መረጃዎችን (asymmetric information and deceptive signals) ተጠቃሚ ነው፡፡ የዚህ ውጤት ሕዝቡን አላስፈላጊ ምርጫ (adverse selection) እንዲያደርግ ያደርገዋል እና የሞራል ውዥንብር (moral dilemma) ውስጥ ይከተዋል፡፡ መንግሥቱ የፈለገውን ቢያደርግ ሕጋዊ፣ ሙያዊ እና ሥነልቦናዊ ግዴታውን መወጣት አይችልም፤ በዚህ ተፀፃች ይሆናል፡፡ መንግሥቱ የፈለገውን አላደርግም ቢል ደግሞ በሀሰት ጥፋት ይወነጀላል፣ መንግሥቱም በቀጥታ በፖሊስ እና በደህንነት ኃይሉ ወይም በካንጋሩ ፍርድ ቤቱ በመጠቀም እምቢ ባይውን ግለሰብ ያስረዋል፣ ይገለዋል፣ ንብረቱን ይዘርፈዋል እና ሰብአዊ መብቶቹን ይገፋል፡፡

ወያኔውን፣ የሥርዓቱ ደጋፊና ተጠቃሚ ትግሬውን እና ተለጣፊውን ደግሞ የሞራል ውድቀት (moral hazard) ውስጥ ይከተዋል፤ ንብረት አለኝ፣ ማንም አይነካኝ፣ የፈለግሁትን ሁሉ ማድረግ እችላለሁ፣ ለጥፋት ተጠያቂ አልደረግም ባይ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡ እብሪተኝነት፣ ወገናዊነት፣ እንደ እስስት ተለዋዋጪነት፣ ሕግ አፍራሽነት፣ ወዘተ የዚህ የአገዛዝ ሥርዓቱ ሰው (የተጋላቢ የትሮይ ፈረሱ) መገለጫ ጠባዮቹ ናቸው፡፡

የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት የውሸት እና አሳሳች መረጃዎችን የሚጠቀመው ተለጣፊዎቹን እና የታብተፓዎቹን ባለሥልጣናት የጥፋት ሥራዎችን ፈጻሚዎች በማድረግ ነው፡፡ በመአመ አገሮች የጥፋት ሥራዎችን የሚፈጽሙት (ቦንድ መሸጥ፣ የኢሳት ቲቪ እና ሬዲዮን ለመዝጋት መሞከር፣ በሀሰት እና አሳሳች መረጃ ስደተኛውን መክሰስ፣ ወዘተ) ትግሬ ባልሆኑት የተለጣፊ ተሿሚዎች እና በታብተፓው መሪዎች (ትግሬዎች ያልሆኑ ግለሰቦች) ነው፡፡

privilege ነኝ) ባይ መሆን ችሏል፡፡ ጀነራል ሀጐስ (የፈጠራ ስም) በቦሌ ላሠራው ግዙፍ ፎቅ ቤት (የቋሚ ንብረት) የቦታው ካርታ ከወያኔ/ኢሕአዴግ ማዘጋጃ ቤት ተሠርቶ በተለጣፊው ባለሥልጣን ተፈርሞ ይሰጠዋል፡፡ ጀነራል ሀጐስን ቤቱን ከየት ባመጣኸው ገንዘብ አሠራኸው?" ብለህ ብትጠይቀው "ከባንክ ተበድሬ ነው" ይልሀል፡፡ ውሸቱን ነው፡፡ የመጣው ከትግራይ ሲሆን አዲስ አበባ የገባውም ባዶ ኪሱን ነው፡፡ ከባንክ ለመበደር ምን ማስያዣ አለው? እውነቱ የወያኔ/መወቤካው መንግሥት (የጀነራል ሀጐስ መንግሥት) ገንዘቡን ከባንክ ዘርፎ ወይም አትሞ ነው የሰጠው፡፡ ለዚህ ማስረጃው ተበደርኩ ወዳለው ባንክ ብትሄድ ባንኩ ጀነራል ሀጐስ መበደሩን የሚያሳይ መረጃ አይጠብቅም፡፡

የመወቤካው አባል የነበረው ስዬ ስለዘመዶቹ የባንክ ብድር እና በወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት (ወይም በወያኔ/መወቤካው መንግሥት) በሙስና ስለመከሰሱና በኢትዮጵያ ሕግ እና ፍትህ የሌለ ስለመሆኑ ጽፏል፡፡ በኢትዮጵያ ሕግ እና ፍትህ ስላለመኖሩ የሁኔታው ፈጣሪ እሱ በመሆኑ ኑዛዜው አግባብነት አለው፡፡ ስለባንኩ ብድሩ የጻፈው ግን እውነትነት ያለው አይደለም፡፡ ከባንክ የተበደሩ ስለመሆናቸው ባንኩም ሆነ ስዬ እና ዘመዶቹ መረጃ የለም፡፡[36]

ትግሬ ያልሆነው ኢትዮጵያዊ ግን የባንክ ብድር እንዲወስድ "ከተፈቀደለት" በወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት ብድሩን በ1942-1975 የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት ሕገ-መንግሥት ደንብ መሠረት በሕጋዊ፣ ፍትሐዊ እና ሥነ-ልቡናዊ ተቀባይነት ባለው መንገድ ያገኘው መሆኑን እንዲያረጋግጥ ይገደዳል፡፡ ነገር ግን የመአመ የፈረሰ ስለሆነ የተበደረው ገንዘብ የባለቤትነት ሙብቱ የተከበረ አይደለም፡፡

በምዕራፍ 16 ለማስረዳት እንደተሞከረው ከ2013/2006 በኋላ የመንግሥት ሥልጣን የጨበጠው የኃይለማርያም/ኢሕአዴግ መንግሥት ማንኛውም የባንክ ብድር በብሔራዊ ባንክ ማቋቋሚያ አዋጆች እና በ1942-1975 በወጡ የመአመ እና የገንዘብ ገበያ ሕግና ሥርዓት መሠረት እንደሆነ ይናገራል፡፡ ሆኖም የኃይለማርያም/ኢሕአዴግ መንግሥት ቢሮክራሲ በ1991-2013ቱ የመወቤካው/ኢሕአዴግ መንግሥት ተቀጣሪዎች የተያዘ ስለሆነ የ1942-1975 የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት ተፈጻሚ አይደለም፡፡ ያ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት በመወቤካው የምሥጢር እና የሳሎን ካቢኔው የገህድ መንግሥት (የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት) ፈርሷል፡፡[37]

XIII

ሶርያ ዛሬ በተለያዩ ጦረኞች ጥቃት እየደረሰባት ትገኛለች፡፡ የባሲስቱን የሶርያ አምባገነን መንግሥት በመደገፍ የሶርያ የጦር ሠራዊት (ያገር መከላከያ ኃይል)፣ ሻቢያ፣ የክርስትያን ታጣቂዎች፣ የሶሪያ ኩርዶች፣ ሂዝቦላ፣ ኢራን እና ሩሲያ ተሰልፈዋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የሶሪያ መግሥት ተቃዋሚዎች፣ የሳላፊስት አንጃ፣ የኢራክ እና ላቫንት የእስላም መንግሥት እና የመአዓመ አብዮት መንግሥታት ቡድን በጦርነቱ ተሳታፊዎች ሆነዋል፡፡ ይኸ ብቻ አይደለም ከአንዱ ወይም ከሌላው ቡድን ጋር የሚሠሩ መንግሥታትም ቁጥር ብዙ ነው (ለምሳሌ፣ ቱርክ፣ ሳውዲ አረብያ እና የአረብ ጋልፍ አገሮች)፡፡

እንዴት ሶርያን ቦምብ በማድረግ የሩሲያን ኦሊጋርኪ ወደ መአመ የውጭ ፈሰስ ማፊያ ኢኮኖሚውን ደግሞ ወደ ገበያ ኢኮኖሚ መለወጥ ይቻላል? የሩሲያ ኦሊጋርኪ በሶርያ ረብሻ ውስጥ ለተሳታፊነቱ አሳማኝ ምክንያት ያገኘለት አይመስልም፡፡ ከአጣብቂኙ ለመላቀቅም ግልጽ የሆነ ፕላን B ያለው አይደለም፡፡ የሐይማኖት መንግሥታቱም (theocracies) እንዴት አምባገነን መንግሥታቸውን ወደ መአመ የቅድመ-መብት ኢኮኖሚያቸውን ደግሞ ወደ ድህረ-መብት የገበያ ኢኮኖሚ መለወጥ እንደሚችሉ የሚያመላክት ሁኔታ የለም፡፡ ለጊዜው በጦርነቱ ተሳታፊ መንግሥታት መካከል አሸባሪዎችን ለመውጋት ስምምነት ቢኖርም፣ "አሸባሪው ማን ነው?" የሚለው ጥያቄ በተባበሩት መንግሥታት (በመአዓመ አብዮት መንግሥታት) የስምምነት መልስ አላገኘም፡፡
የመአዓመ አብዮት መንግሥታት (አሜሪካ እና የአውሮፓ ኅብረት የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ መንግሥታት) የሶርያ ጦርነት ውስጥ መግባታቸው አሳማኝ የሆነ ምክንያት አለው፡፡ የጸረ-ሽብርተኛ ጦርነትን መዋጋት የመአዓመ

[36] በ 1991-2013 የመንግሥቱ እና የግሉ የትግሬ ማፊያዎች ለሚበደሩት ወይም ለሚዘርፉት ገንዘብ ባንኮቹ መረጃ እንዳይጠብቁ ይደረጋል፡፡

[37] ለመአመ እና የኢትዮጵያ እተፖዎች በኢትዮጵያ የ1942-1975 የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓትን ለማስፈን፣ ለማጠናከር እና ቀጣይነት እንዲኖረው ለማድረግ በጣም ቀላል መሆኑን ከዚህ ቀረባ እንረዳለን፡፡ የትግሬው ማፊያ የሚጠየቀው በእጁ አለኝ የሚለው ገንዘብ፣ ቋሚ ንብረት እና ሀብት በሕጋዊ፣ ፍትሐዊ እና ሥነ-ልቡናዊ ተቀባይነት ባለው መንገድ ያገኘው መሆኑን እንዲያረጋግጥ ነው፡፡ ይኸን ግዴታ ያሟሉት ዜጐች በሕጋዊ፣ ፍትሐዊ እና ሥነ-ልቡናዊ ተቀባይነት ባለው መንገድ ያገኙት ገንዘብ፣ ንብረት እና ሃብት የወያኔ/መወቤካው መንግሥት የመአመን ስላፈረሰው የባለቤትነት ሙብታቸው አልተከበረላቸውም፡፡ እንዲከበርላቸው ማድረጉ በመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት ቀላል ነው፡፡ መአመ የሚሆነው እውነቱን ባወቀ (ሞብ ባልሆነ እና በሞራል ፀፀት በሽታ ባልተጠቃ) ሕዝብ ሕዝበ-ምርጫ የተመረጠው እተፓ ነው፡፡

እና የተባበሩት መንግሥታት የስምምነት ውሳኔ ነው፡፡ ይኸን ውሳኔ ተፈጻሚ ማድረግ ደግሞ የስምምነቱ አባል መንግሥታት የሕግ እና የሥነ-ልቡናዊ ግዴታቸው ነው፡፡[38]

የሶርያ ሕዝብ የዚህ ቅጥ የሌለው ጦርነት የጥፋት ሠለባ ተደርጓል፡፡ ከሕዝቡ ግማሹ ያህል የውጭ እና የአገር ውስጥ ተፈናቃይ እና ስደተኛ ሆኗል፡፡ ከተማዎችና ቅድመ-ግንባታዎች (infrastructure) ፈርሰዋል፡፡ ብዙ የሶርያ ህጻናት፣ አሮጊቶች እና ሽማግሌዎች ህይወታቸውን አጥተዋል፡፡ ቁጥሩ ብዙ የሆነ ሶርያዊ በሊባኖን፣ ቱርክ እና ጆርዳን በተዘረጉ እፍግፍግ ያሉና አቅርቦት ያልተሟላላቸው የመጠለያ ጣቢያዎች ውስጥ ኗሪዎች ሆነዋል፡፡ ብዙዎች ደግሞ ወደ መአመ አገሮች ለመግባት የሕይወት መስዋእት እየከፈሉ ይገኛሉ፡፡[39]

በዚህ ሁኔታ ነው እንግዲህ የመአዓመ አብዮት መንግሥታት (የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ መንግሥታት) በተባበሩት መንግሥታት ስምምነቶች አማካይነት ሶርያን እንደ አገር ለማቆየት እና የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት እንዲኖራት ለማድረግ እየጣሩ የሚገኙት፡፡ ሶርያኖቹ በየአገሩ ስደተኞች ስለሆኑ በምን አኳኋን እና የት ተገናኝተው ነው ሕዝበ ምርጫቸውን ማሳወቅ የሚችሉት? ሕዝበ-ምርጫ ማድረግ የሚያስችሏቸው አተፓዎችስ የት አሉ? የሶርያ ሕዝብ ከጥፋቱ ለማምለጥ ወደ አውሮፓ ኅብረት መጉረፍ ጀምሯል፡፡ ስደተኛውን ተቀላቅሎ የገባውና በአውሮፓ ኅብረት የተፈጠረው አሸባሪ ኃይል የአውሮፓ ኅብረት መንግሥታትን እንግዳ ተቀባይነት እንዳይሠራ እያደረገው ይገኛል፡፡ ስደተኛውም እተፓዎች ስለሌሉት በስደተኛ እና በአዲስ አገር ዜግነት መብቱ ተጠቃሚ አልሆነም፡፡ ግዴታዎቹንም የተረዳ አልሆነም፡፡ ስደተኛው ለመአመ አገሮቹ ለሚመለከተው የመንግሥት አካል በመሀሉ የሚገኙትን አሸባሪዎች የማሳወቅ የሕግ፣ ሙያ እና ሥነ-ልቡናዊ ግዴታዎች አሉበት፡፡ ይኸ አለመፈጸሙ የመአዓመ አብዮት አገራት ሕዝብ ስደተኛውን እንዳይቀበል እያደረገው ይገኛል፡፡ እተፓዎችንም በጊዜው ከመሀሉ መፍጠር አለመቻሉ በመንግሥታቱ ርዳታ እና ከመንግሥታቱ ጋር በውይይት ችግሩን መፍታት እንዳይችል አድርጎታል፡፡[40]

XIV

ከሶርያኖቹ ጋር በንጽጽር ሲታይ ኢትዮጵያውያን እና የመአዓመ አብዮት መንግሥታት የገጠማቸው ችግር ቀላል እና ግልጽ መፍትሄ ያለው ይመስላል፡፡የመአዓመ አብዮት መንግሥታት በኢትዮጵያ የ1942-1975 የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት እንዲጠናከር እና ቀጣይነት እንዲኖረው ለማድረግ እንደ ሶርያ የሚደራደሯቸው ከ13 በላይ የአምባገነን መንግሥታትና ቁጥረ ብዙ የሆኑ የሶርያ ተጋላቢ የትሮይ ፈረሶች የሉባቸውም፡፡ እንደሶርያ በኢትዮጵያ ጦርነት የገጠሟቸው የአይሲስ፣ የአልቃይዳ፣ የአልሸባብ፣ የሂዝቦላ ወይም ሌላ አሸባሪ እና አረመኔ ቡድን የለም፡፡

የትሮይ ፈረስ ጋላቢ የሆነው አምባገነኑ የሶቪየት ኅብረት የኮሚኒስት መንግሥት ለተጋላቢው የትሮይ ፈረስ መንግሥቱ (ለደርግ/ኢሠፓ መንግሥት) እና ለእምነት እና ለብሔር ማርክሲስቱ የሞብ መንጋ ነጂዎች ጥይት በማቀበል (የጥፋት እቃዎችን እና አገልግሎቶችን ወደ ኢትዮጵያ በገፍ በማስገባት) የኢትዮጵያን የመአዓመ አብዮት አዳፍኖታል፡፡[41] በአምባገነኑ የደርግ መንግሥት ዘመን (1975-1991) ከሶቪየቶቹ በተገኘ የወል ግድያ መሣሪያ (weapons of mass destruction) እና የማርክሲስት ሌኒኒስት (የሀሰት) እምነት በመጠቀም እና የእውነቱ እውቀት የሌለውን የሞብ መንጋ በመንዳት የኮሚኒስት መንግሥት (የሕገ-መንግሥት ሳይሆን) የእዝ ሥርዓት ለመዘርጋት እና የስብስብ ኢኮኖሚ ግንባታ ለማካሄድ ሞክሯል፡፡ የኢትዮጵያ የመአዓመ አብዮት አራማጅነትን እንደወንጀል የጥፋት ሥራ በመቁጠር ከ3 እስከ 5 ሚሊዮን የሚደርሱ የሥርዓቱን መሥራቾች፣ አዋቂዎች፣ ደጋፊዎች እና ተጠቃሚዎችን በመግደል የቀሩትንም በማስገደድ የሥርዓቱ አገልጋዮች አድርጓቸዋል፡፡ በመጨረሻም የመንግሥቱን የጥፋት እቃዎችንና አገልግሎቶችን የማምረቻ ወጪዎቹን በዝርፊያ መሸፈን አቅቶት፣ ከሥሮ የስብስብ ኢኮኖሚውንም ሳይገነባ ጥይት እና አመራር ሰጪው የሶቪየት መንግሥት ሲፈርስ የደርግ መንግሥትም አብሮ በ1991 ፈርሷል፡፡

---

[38] ሽብርተኞች የተባሉት አይሲስ፣ ሂዝቦላ፣ አልቃይዳ፣ ወዘተ ናቸው፡፡ በመአዓመ አብዮት መንግሥታት እይታ በራሱ ሕዝብ ላይ ጦሩን ያዘመተው የሶርያ የአምባገነን መንግሥት በአሸባሪነት ተፈርጇል፡፡ ሆኖም የመንግሥቱን አሸባሪነት በሚመለከት የመንግሥታቱ ስምምነት የለም፡፡

[39] በጦርነቱ ውስጥ ተሳታፊዎች ወደሆኑት አምባገነን መንግሥታት አገሮች የሚያቀኑ ሶርያኖች ስለመኖራቸው መረጃዎች እስከ ዛሬ አልቀረቡም፡፡

[40] በ1942-1975 የኢትዮጵያ መንግሥት በዓለማችን የመአዓመ አብዮት እንዲሰፍን እና በመልካም አስተዳደር የዓለም መንግሥታት ስምምነት መሠረት በኢትዮጵያ የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት እንዲዘረጋና ቀጣይነት እንዲኖረው የፊር ቀዳጁን ሚና የተጫወተ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

[41] የብሔር ማርክሲስቱ የኔ ብሔር በገዢው ብሔር ተጠቅቷል ብሎ ሲያምን፣ የሀይማኖት ማርክሲስቱ ደግሞ የኔ እምነት ተከታዮች በገዢው መደብ የእምነት ተከታዮች ተጠቂዎች ናቸው ብሎ ያምናል፡፡

የመአዓመ አብዮት መንግሥታት የኢትዮጵያ የጦር መኰንኖች “በራሴ ሕዝብ ላይ አልዘምትም” በማለት የደርግ/ኢሠፓን መንግሥት የጣሉ መሆኑን እና ይኸንንም እራሳቸውን መስዋእት በማድረግ በመፈጸማቸው የግዙፉን ጦር ተራ አባል ከፀፀት ኑሮ እና የኢትዮጵያንም ሕዝብ ከአላአስፈላጊ የጥፋት ጦርነት ያዳኑት መሆኑን ተረድተዋል፡፡ የዚህን ጦር መሪዎች አባላት በአገራቸው በስደተኝነት በመቀበል በኢትዮጵያ የመአዓመ አብዮት (የ1942-1975 የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ግንባታ) እንዲጠናከር እና ቀጣይነት እንዲኖረው ለማስቻል አስተዋጽኦ ማድረግ እንዲችሉ ሁኔታዎችን አመቻችተውላቸዋል፡፡[42]

በሶርያ ጉዳይ ላይ የሩሲያው ኦሊጋርኪ “የሶርያ ሕዝብ ይወስን” በማለት ለአሳድ አምባገነን መንግሥት ከሱ ለወገነው ጦር ድጋፍ የሚሰጥ መሆኑን ሲገልጥ የመአዓመ አብዮት መንግሥታትም ቢሆኑ “የሶርያ ሕዝብ ይወስን” ባዮች ናቸው፡፡ ልዩነቱ የሩሲያው ኦሊጋርኪ መንግሥት “የሶርያ ሕዝብ” የሚለው የሶርያን የሞራል ዝቅጠት በሽታ ተጠቂ እና ሞብ ሲሆን የመአዓመ አብዮት መንግሥታት ሕዝበ-ውሳኔውን መስጠት የሚችለው የእውነቱን እውቀት ያወቀ የዜግነት፣ የሕግ፣ የሙያ፣ እና የሥነ-ልቡና ግዴታዎቹን የተረዳውን እንዲሁም የመአዓመ አብዮት መንገድን የተቀበለውን ሕዝብ ነው፡፡[43]

የደርግ መንግሥት (1975-1991) የተተካው በሆብሶን ምርጫው በወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት በ1991 ሲሆን፣ መንግሥት አልባ የሆነችውን ኢትዮጵያ ለመታደግ መአዓመን (የተባበሩት መንግሥታትን) በመወከል በኔቶ የመአመ መንግሥታት አደራዳሪነት ነበር፡፡[44] በ1991 በወያኔዎች ለሚመራው የብሔር አፓርታይድ (separate development) መንግሥት (ለወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት) የመአዓመ አብዮት መንግሥታት ኢትዮጵያን አሳልፈው (on a silver platter) አልሰጡም፡፡ የመአዓመ አብዮት መንግሥታት የኢትዮጵያን ጉዳይ የያዙት በ1942-1975 የተቀጣጠለውን የመአዓመ አብዮት (የ1942-1975 የመአመ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓትና የገበያ ኢኮኖሚ ግንባታ) ቀጣይነት እንዲኖረው ለማድረግ የሚያስፈልጉትን ወጪዎች በመሸፈንና ያንን እንዲፈጽም ከወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት ጋር ዓለም ያወቃቸው ስምምነቶችን በመፈራረም ነበር (ምዕራፍ 17ን ተመልከት)፡፡[45]

ከመአዓመ አብዮት መንግሥታት ጋር የተፈራረመውን ስምምነት በመጣስ እና ውሉን በመቅደድ፣ ሰብአዊ መብቶችን በመግፈፍ እና የ1942-1975 የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓቱን በማፍረስ የወያኔ/ኢህአዴግ መንግሥት የአፓርታይድ (separate development) (የብሔር) መንግሥት ሥርዓቱን መሥርቷል፣ በገበያ ኢኮኖሚ ግንባታው ፋንታ ያንን በማፍረስ የማፊያ ኢኮኖሚውን አስፋፍቷል፡፡[46]

ይፋ የወጣው የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት ዓላማ “የትግራይን ነጻነት የተጠበቀ ማድረግና የትግሬውን ጥቅም ማስከበር” ነበር፡፡ ይኸን ዓላማውን ተፈጻሚ ለማድረግ ሁለት ረድፍ ያለው የአገዛዝ ሥርዓት [የወያኔ(መለስ) የወጥ ቤት ካቢኔ (መወቤካ) መንግሥት እና በሱ እዝ ሥር የተዋቀረ የክልሎችና የሳሎን ካቢኔው የተለጣፊ መንግሥት] መሥርቷል፡፡ በመወቤካው ቁጥጥር ውስጥ የሚሠራ በራሱ ሕዝብ ላይ ዘማች የሆነ የትግሬ ጦር (የብሔሮች ተለጣፊ መንግሥቱ ታጣቂዎችን ጨምሮ) አቋቁሟል፡፡ የ1942-1975 የመአመ የበጀት ሥርዓቱን ስላፈረሰው የግብር ቀጠና እና የመንግሥት

---

[42] በሶርያ የሶርያ ጦር ለአሳድ መንግሥት በማደር የራሱን ሕዝብ በአጥፍቶ መጥፋት ጦርነት እያመሰው ይገኛል፡፡ በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ የመአዓመ አብዮት መንግሥታት የወሰዱት ርምጃ የሶቪየት መንግሥት ሲፈርስ ተጋላቢው የትሮይ ፈረሱ የደርግ/ኢሠፓ መንግሥት አብሮ በኢትዮጵያ ጦር መኰንኖች እንዲፈርስ መደረጉን ተከትሎ፣ (ሀ) የሶቪየት ኃብረት ጦር አካባቢውን ለቆ እንዲወጣ፣ (ለ) በኢትዮጵያ ጦር የፈረሰው የደርግ/ኢሠፓ መንግሥት ከሥልጣን እንዲወርድ እና (ሐ) ለጊዜው በሜዳው የነበሩ የብሔር ነጻ አውጪዎች (ሻቢያ፣ ወያኔ፣ ኦነግና ሌሎችም የብሔር ነጻ አውጪ ፓርቲዎች) በወያኔዎቹ ሰብሳቢነት የጊዜያዊ መንግሥት እንዲያቋቁሙና ወደ ሕዝበ-ምርጫ እንዲሻገሩ አደራድረዋል፡፡

[43] የመአዓመ አብዮት መንግሥታት የአሳድ መንግሥትን መወገድ ከሩሲያው መንግሥት ጋር ላላቸው ስምምነት እንደ ቅድመ-ሁኔታ ወስደውታል፡፡

[44] የኢትዮጵያ ጦር መኰንኖች ይኸን እርምጃ የህይወት መስዋዕት ከፍለው በመውሰዳቸው የግዙፉ ጦር አባል ከፀፀት ኑሮ ሕዝቡንም ከጥፋት እና እልቂት አድነውታል (በአፍሪካ እና በመካከለኛው ምሥራቅ የተከሰቱትን የራስ ማጥፋት ጦርነቶች አጢናቸው)፡፡ የኢትዮጵያ ጦር የኢትዮጵያን ዳር ድንበር እና ነጻነት በመጠበቅ ረገድ፣ እንዲሁ ለመልካም አስተዳደር መንግሥት እና የገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት በኢትዮጵያ እንዲሰፍን ስለተጫወተው አዎንታዊ ሚና የኢትዮጵያ የጦር (military) ታሪክ ጸሐፊዎች ብዙም አልጻፉም፡፡ የደርግ/ኢሕአዴግ መንግሥትን ከሥልጣን ካወረዱ በኋላ የኢትዮጵያ ጦር አባላት የሻቢያን ኢትየጵያን የማፍረስ ጦርነት ገተውታል፡፡ ለትግሬ እና ሀማሴን የብሔር ጦሮች እራሳቸውን የጥፋት መሣሪያዎች አላደረጉም፡፡ ታደሰ ቴሌ ሳልቫኖ እኒህ የብሔር ነጻ አውጪዎች በኢትዮጵያ ጦር ላይ ስለፈጸሙት የጦር ወንጀል (war crime) ጽፏል፡፡ እኒህ የጦር ወንጀለኞች በሥልጣን ላይ በመቆየታቸው እስከዛሬ በመአዓመ እና መአመ ፍርድ ቤቶች ተጠያቂዎች አልሆኑም፡፡

መወቤካው ያቋቋመው የትግሬ ጦር የሚመራው የአንደኛ ደረጃ ትምህርት በሌላቸው ሙያ ቢስ የትግሬ ጀነራሎች ነው፡፡ የትግሬውን ጦር ዘመናዊ ለማድረግ ወጣት ትግሬዎችን መልምሎ ሥልጠና እንዲያገኙ ለማድረግ መወቤካው ሞክሯል፡፡ የዚህን ሂደት የሚገልጥ የመንግሥት ሪፖርት ባይወጣም፣ አንዳንድ መረጃዎች የሚያሳዩት የጦር ትምህርት የተማሩ ትግሬዎች መንግሥታቸውን በግልፅ ለማገልገል ፈቃደኞች አይደሉም፤ አንዳንዶቹም ይኸን ላለመፈጸም አገር ላቀው ኰብልለዋል፡፡

[45] መንግሥት አልባ የተደረገችውን ኢትዮጵያ እንደ ኦቶማን ቱርኮች፣ የጣሊያን ፋሺስቶች፣ የሶቪየት ኅብረት አምባገነኖች እና ተስፋፊ አረቦችን የመሰሉ የውጭ ኃይሎች ተጠቂ እንዳትሆንና የአገሪቱም የግዛት አንድነት እንዳይደፈር ለመከላከል የመአዓመ አብዮት መንግሥታት በጅቡቲ የኔቶ የጦር ኃይል እንዲመሽግ አድርገዋል፡፡ እስከዛሬ ድረስ ኢትዮጵያውያን በውጭ ኃይሎች ጥፋት መሠቃየታቸው አብቅቶለት የራሳቸውን አጥፊዎች ማወቅ እና መቆጣጠር ወደሚችሉበት መንገድ እንዲሻገሩ ሁኔታዎችን አመቻችተውላቸዋል፡፡

[46] የዚህን የአፓርታይድ መንግሥት እና የማፊያ ኢኮኖሚውን አሠራር በመጽሐፉ በክፍል አራት ለመግለጽ ተሞክሯል፡፡

ገቢ/ወጪ መረጃ (fiscal jurisdiction and trail records) የሉትም፡፡ አላማውን ለማሳካት በዝርፊያ ገንዘብ እና በሙያ ቢስ የቢሮክራሲው የጥፋት ሠራዊት ይጠቀማል፡፡[47]

የወያኔ/መወቢካው መንግሥት በዚህ አኳኋን በሙሉ ኃይሉ በመነቃነቅ ከ1991/1983 ጀምሮ እስከ ግንቦት 2006 (May 2013) (ወይም መለሰ በኃይለማርያም የተተኩበት ጊዜ ድረስ) ባለው ጊዜ ውስጥ ዓላማውን ተፈጻሚ አድርጓል፡፡ በሁሉም ክልሎቹ "የትግራይን ነጻነት ማስከበርና የትግሬውን ጥቅም ማስጠበቅ" ችሏል፡፡ ለሥርዓቱ ግብ መምታት አቶ መለሰ አመራር ሰጥተዋል፡፡ በ 1991-2013 ባለው ጊዜ የአፓርታይድ እና የማፊያ አኮኖሚ ሥርዓቱ አገልግሎት ይሰጥ የነበረው ለወያኔ፣ የሥርዓቱ ደጋፊ ትግሬ እና ለተለጣፊዎች ባለሥልጣናት ብቻ ነበር፡፡ የወያኔ/መወቢካው የምሥጢር መንግሥት እነሂን የንብረት እና የሥልጣን ባለቤት እንዲሁም "አልከሰስም" (immunity አለኝ) ባዮች እንዲሆኑ እና "ሁሉም ይገባኛል" (privilege አለኝ) እንዲሉ አድርጓቸዋል፡፡

ማንኛውም ትግሬ ያልሆነ ኢትዮጵያዊ ህይወቱ በሙሉ በክልሉ እንዲወሰን ሲደረግ በክልሉ እና በፌደራል (የትግሬ) መንግሥቱ ሰብአዊ መብቶቹ ይገፈፋሉ፣ ንብረቱ ይዘረፋል፣ ያለ ሕግ እና ፍትሕ ይታሰራል፣ ይገደላል፡፡ ትግሬ የሆነ ለወያኔ/መወቢካው መንግሥት ተጠሪ ሲሆን ለሳሎን ካቢኔው መንግሥት እና ለክልል መንግሥቱ (ማለትም ለተለጣፊው መንግሥት) ተጠያቂ (accountable) አይደለም፤ የተለጣፊው መንግሥት ትግሬውን አያዝም ትግሬውም አይታዘዝለትም፡፡

ማንኛውም ሌላ ኢትዮጵያዊ ለሳሎን ካቢኔው እና ለክልሉ መንግሥት እንዲሁም ለወያኔ/መወቢካው (ለፌደራል) መንግሥቱ ተጠያቂ (ወይም ታዛዥ) ሲሆን፣ ትግሬ የሆነው ተጠሪነቱ ለመወቢካው ወይም የፌደራል መንግሥት ሆኖ በማንኛውም የመንግሥቱ ክልሎች እና መሥሪያ ቤቶች አዛዥና ተናዛዥ ተደርጓል፡፡[48] ትግሬው በምድረ ኢትዮጵያ የንብረት እና የሥልጣን ባለቤት (proprietor and person with power or authority)፣ "ማንም አይነካኝ" (immunity አለኝ) እና "ሁሉም ይገባኛል" (privilege አለኝ) ባይ ሆኗል፡፡ የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥትና የማፊያ ኢኮኖሚው የ1942-1975 ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን ስላፈረሰው በሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት የሚተዳደር አይደለም፣ በትግሬ አለቃ (ተለዋዋጭ) ትእዛዝ የሚመራ ነው፡፡[49]

በ1991/1983 የደርግ መንግሥት ሲፈርስ ኢትዮጵያ መንግሥት አልባ እንደሆነች በ2013 አቶ መለሰ ሲሞት እና የወያኔ/መወቢካው የምስጢር መንግሥት ሲፈርስ ኢትዮጵያ መንግሥት አልባ ሆናለች፡፡ መለሰ እና አቡነ ጳውሎስ ሲሞቱ የወያኔ/መወቢካው መንግሥት ፈርሷል፡፡ የወያኔ/መወቢካው የአፓርታይድ መንግሥት እና የማፊያ ኢኮኖሚው እንዲጠናከር እና ቀጣይነት እንዲኖረው ለማድረግ እንዲሁም የመለሰን ተተኪ ለመምረጥ ወያኔዎች በመቀሌ ተሰብስበው ነበር፡፡[50]

የመአዓመ አብዮት መንግሥታትን በመወከል የአሜሪካ መንግሥት በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የአፍሪካ ጉዳይ ሀላፊዋ በመንግሥቱ ሥነ-ሥርዓት ላይ በመገኘት የአሜሪካ መንግሥት በኃይለማርያም የሚመራውን የኢሕአዴግ መንግሥት እውቅና የሰጠችው መሆኑን አሳውቃለች፡፡ በምዕራፍ 17 ግልፅ የተደረገውን በኢትዮጵያ የ1942-1975 የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ሕገመንግሥታዊ ሥርዓት ለማጠናከርያ እና ቀጣይነት እንዲኖረው ለማድረግ የሚያስፈልገውን ወጪ እና የሎጂስቲክስ ድጋፍ ለኃይለማርያም/ኢሕአዴግ መንግሥት እንደሚሰጥ የመአዓመ አብዮት መንግሥታትን በመወከል መልእክተኛዋ ገልጻለች፡፡[51]

---

[47] "የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት ያደረገውን ከማድረግ ሌላ ምን አማራጭ ነበረው?" የሚለውን ጥያቄ ኢትዮጵያውያን አልተከራከሩበትም፡፡

[48] የወያኔ/ኢሕአዴግ ወይም የፌደራል መንግሥት የሚባለው ይኸ የመወቢካው እና የተለጣፊው (የክልሉ እና የሳሎን ካቢኔው) መንግሥት የጥምረት መንግሥት ሲሆን ዓላማውም የትግራይን ነጻነት እና የትግሬውን የወል ጥቅም የተጠበቀ (የተከበረ) ማድረግ ነው፡፡ የወል ጥቅሙን ማስከበር ማለት የወል ሙብቱን ማስከበር ማለት አለመሆኑን ማጤን ያስፈልጋል፡፡

[49] የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት ዳኞች የ1960/1952 የንግድ ሕግ፣ የ1960/1952 ፍትሐ-ብሔር ሕግ እና የወንጀለኛ መቅጫውን ሕግ (ስለማያውቁት/ስላልተማሩት) ተርጓሚዎች አይደሉም፡፡ የንግዱ ሥራ በንግድ ሕጉ እና በተዘረጋው የመአመ ሥርዓት አይሠራም፡፡ የካንጋሩ ፍርድ ቤቶቹ፣ የካንጋሩ ፍርድ ቤቶቹ ዳኞች እና አቃቤ ሕጎች የትግሬ ወይም ተለጣፊ የሥርዓቱን ባለሥልጣናት ትእዛዝ አስፈጻሚዎች ሲሆኑ፣ የመንግሥት (የክልል እና የሳሎን ካቢኔ መንግሥት) ሥራዎች በጥፋት ሥራዎች አምራቾች እና አከፋፋዮች ተይዘዋል፡፡

[50] ድርጅቱን የለቀቁ የመወቢካው አባላት "ይቅር በመባባል" በስብሰባው የተገኙ ነበሩ፡፡

[51] የወያኔ/መወቢካው መንግሥት ከመአዓመ አብዮት መንግሥታት ጋር የፈጸመውን ስምምነት በማፍረስ የአፓርታይድ መንግሥት እና የማፊያ ኢኮኖሚ ሥርዓት ዘርግቷል፡፡ በመጽሐፉ በክፍል አራት ይኸ የወያኔ/መወቢካው የአፓርታይድ (የትግሬ ብሔርተኛ) መንግሥት ሁለት ረድፍ መንግሥት በመፍጠር፣ የትግሬውን ጦር በማደራጀት እና በዝርፊያ ገንዘብ በመጠቀም የአፓርታይድ (separate development) ሥርዓተ መንግሥቱን ለመዘርጋት እና የማፊያ ኢኮኖሚውን ለማስፋፋት እንደቻለ ለማስረዳት ተሞክሯል፡፡ በዚህ አኳኋን በ1991-2013 ባለው ጊዜ ውስጥ የወያኔ/መወቢካው መንግሥት አላማውን ለማስፈጸም (ማለትም የትግራይ ነጻነትና የትግሬውን ጥቅም ማስጠበቅ) ችሏል፡፡ የመንግሥቱን እና የግሉን ትግሬ የማፊያ ኢኮኖሚ ገንብቷል፡፡ ማንኛውንም ትግሬ ያልሆነ ሰው መወቢካው በከለለለት ክልል እንዲወሰን ሲያደርግ ትግሬውን ግን በሁሉም ክልል ባለንብረት እና ባለሥልጣን፣ አልከሰስም ባይ እና ሁሉም በእጄና በደጄ እንዲል አስችሎታል፡፡ የወያኔ/መወቢካው መንግሥት ትግሬውን

አሁን የወያኔ/መወቤካው የምስጢር መንግሥት የለም፡፡ የወያኔ/መወቤካው መንግሥት የፈረሰ መሆኑን የሚያረጋግጡት የመወቤካው አባላት ናቸው፡፡ በትግራይ መንግሥት የመወቤካው አባል (አቶ ስብሃት) ስለሚያስተዳድረው በዝርፊያ ገንዘብ የተቋቋሙ ኩባንያዎች ሲጠየቅ የሰጠው መልስ "አሁን እኔ የሀላፊነቱን ሥልጣኔን የለቀቅሁ ስለሆነ ስለመንግሥቱ ፋብሪካዎች እና የኢኮኖሚ ፖሊሲ የማውቀው ነገር የለም" የሚል ነበር፡፡ ባሁኑ ወቅት እሱን የመሰሉ የመወቤካው አባላት ሥልጣናቸውን የለቀቁ ሲሆኑ፣ አንዳንዶቹ ድርጅቱን የሚያወግዙ፣ መሪውን አቶ መለሰን ለጥፋቶቹ ሁሉ ተጠያቂ አድራጊዎች እና የራሳቸው ተቃዋሚ ድርጅት ያቋቋሙ እና ሌሎች ተቃዋሚ ድርጅቶችን እየተቀላቀሉ ይገኛሉ፡፡

አሁን የዓለም አቀፍ እውቅና ያለው የኢትዮጵያ መንግሥት የኃይለማርያም/ኢሕአዴግ መንግሥት ሆነ፡፡ ይኸን መንግሥት እንዲሠራ ለማድረግ ኃይለማርያም ሶስት የአማራጭ መንገዶች አሏቸው፡፡ አንደኛው በትግሬ አለቃና በተለጣፊ ባለሥልጣን "ትእዛዝ" የሚሠራውን የወያኔ/መወቤካውን የአፓርታይድ መንግሥት (የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት) እና የማፊያ ኢኮኖሚ እንዲቀጥል ማድረግ ነው፡፡ ይኸ የመአዓመ አብዮት መንግሥታት ስምምነትን ከመጣሱ ባሻገር የኃይለማርያም/ኢሕአዴግ መንግሥትን በመለሰ የሙት መንፈስ የሚመራ የመወቤካው "ዛር" የሰፈረበት ያደርገዋል፡፡

ሁለተኛው መንገድ ወያኔዎቹ እንዳደረጉት ኃይለማርያም የመአዓመ አብዮት መንግሥታት የኢትዮጵያን የ1942-1975 የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ለማጠናከሪያና ቀጣይነት እንዲኖረው በሚሰጡት ገንዘብ የወላይታ ጦር በመገንባትና የኃይለማርያም የወጥ ቤት ካቢኔ (ኃወቤካ) መንግሥት በማቋቋም የኃወቤካውን የአፓርታይድ መንግሥት መዘርጋት እና የወላይታ የማፊያ ኢኮኖሚ ማስፋፋት ነው፡፡[52] ኃይለማርያም ይኸን መንገድ ቢመርጡ በትግሬ አለቃ እና በተለጣፊ ባለሥልጣን ትእዛዝ የሚሠራው የወያኔ/መወቤካው የሳሎን እና የክልል መንግሥቱ፣ የትግሬ ጦሩ እና የፖሊስ እና የደህንነት እንዲሁም የብሔር ታጣቂው ተቃውሞ ይገጥማቸዋል፡፡ ከታብተፓዎች እና ተብጦፓዎችም የኃወቤካው መንግሥት ተቃውሞ ይገጥመዋል፡፡ ዋናውና ወሳኙ ጉዳይ ደግሞ የኃወቤካውን መንግሥት ወጪዎች የሚሸፍነውን የመአዓመ አብዮት መንግሥታት የገንዘብ እና የሎጂስቲክስ ርዳታ (ስምምነቱን በመጣሱ) የኃወቤካው መንግሥት ማጣቱ ነው፡፡

ለኃይለማርያም/ኢሕአዴግ ቀላሉና የሚያዋጣው መንገድ ሶስተኛው መንገድ ነው፡፡ ሶስተኛው መንገድ የኃይለማርያም/ኢሕአዴግ መንግሥት ከ1942-1975 የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚውን የገነቡት ኢትዮጵያውያን ጋር፣ ስለ መአዓመ አብዮት እና የ1942-1975 የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ እውቀት ካላቸው ኢትዮጵያውያን ጋር እና ለመአዓመ አብየት እና ለ1942-1975 የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት እንዲጠናከር እና ቀጣይነት እንዲኖረው መስዋእት ከከፈሉ ኢትዮጵያውያን ጋር ተስማምቶ መሥራት መቻል ነው፡፡[53]

የኃይለማርያም/ኢሕአዴግ መንግሥት "መንገድ ሶስትን" ብቻ እንዲከተል መንግሥቱ ግዴታ አለበት፡፡ ያንን መንገድ አልከተልም ቢል ግዴታውን መወጣት አይችልም፤ ከመአዓመ አብዮት መንግሥታት ጋር የፈጸማቸውን ስምምነቶች ይጥሳል እና ኢትዮጵያንም ያለ ወያኔ/መወቤካው መንግሥት በወያኔ/መወቤካው የአፓርታይድ እና የማፊያ ኢኮኖሚ ሥርዓት ውስጥ እንድትማቅቅ ያደርጋል፡፡

## XV

ከዚህ መጽሐፍ በአንባቢዎች የሚነሳው አንዱ ጥያቄ፣ "ለምንድነው የመአዓመ አብዮት መንግሥታት የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት የመአዓመን መንግሥታት ስምምነቶችን ሊጥስ፣ የኢትዮጵያ የ1942-1975 የመአመና የገበያ ኢኮኖሚ እንዲያጠናክር እና ቀጣይነት እንዲኖረው እንዲያደርግ የሰጡትን ገንዘብ ሲዘርፍ፣ የአፓርታይድ መንግሥታዊ ሥርዓት ሲዘረጋ እና የማፊያ ኢኮኖሚ ሲያስፋፋ የእርምት ርምጃ ያልወሰዱት?" የሚል ይሆናል፡፡

የዚህን ትክክለኛ መልስ ለመረዳት ወደ **2000 ዓ.ም የተባበሩት መንግሥታት የሚሊኒየም ውሳኔ** (UN Millennium Declaration) መመለስ ይኖርብናል፡፡ ወደኋላ የቀሩ አገሮችን በሚመለከት በመአዓመ አብዮት መንግሥታት አመራር ሰጪነት የተባበሩት መንግሥታት በ2000 በሙሉ ስምምነት አገሮቹን የመአዓመ አብዮትን መንገድ እንዲከተሉ (ማለትም

---

እንዲታጠቅ እና በትግሬ ጦሩ፣ በደህንነት መሥሪያ ቤቱ፣ በተለጣፊ የሳሎን እና የክልል መንግሥቱ በትግሬ አለቃ እና በተለጣፊው ባለሥልጣን ቁጥጥር ሥር መውደቅ እንዲጠቀም አድርጎታል፡፡

52 ኃይለማርያም "ወላይታ" ናቸው ብሎ በመገመት ነው፡፡

53 የመአዓመ አብዮት መንግሥታት እንደናዚ የጀርመን ጦር የነዚህን የመአዓመ አብዮት እና የ1942-1975 የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ እውቀት ያላቸው ኢትዮጵያውያንን አረመኔነት ለማሳየት ከሚሞክሩት የኢትዮጵያ ተጋላቢ የትሮይ ፈረሶች፣ አሸባሪዎች እና አረመኔዎች (ኢተትፈአ) ጋር ልሥራ ቢሉ፣ የተባበሩት መንግሥታት እና የመአዓመ አብዮት መንግሥታት "አሸባሪ" ብለው ከፈረጇቸው እና ጦርነት ከከፈቱባቸው አጥፊዎች ጋር ተባብሮ ለመሥራት ወስነዋል ማለት ነው፡፡

የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት እንዲዘረጉ፣ እንዲያጠናክሩ እና ቀጣይነት እንዲኖረው እንዲያደርጉ) ለማስቻል የ21ኛውን መቶ ዓመት **የሚሊኒየም የልማት ግቦች (ሚልግ)**[54] መርሃ-ግብር በሥራ ላይ ለማዋል ወስነዋል፡፡

ሚልግ የ15 ዓመታት እድሜ (2000-2015) ያለው ሲሆን ለተረጂ መንግሥታቱ ሁለት አይነት ርዳታዎችን ይሰጣል፡፡ አንደኛ **የምግብ (food) ወይም የሰብአዊነት (humanitarian) ርዳታ** ለማንኛውም አገር ወይም ሕዝብ (መንግሥት ይኑረው ወይም አይኑረው) ያለአንዳች ቅድመ ሁኔታ ይሰጣል፡፡ ሶማሊያ የሲያድ ባሬ መንግሥት ሲወድቅ መንግሥት አልነበራትም፣ በሶርያም እንዲሁ መንግሥት አልባ ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ ነገር ግን ለእኒህና መሰል አገሮች የምግብ ወይም የሰብአዊነት ርዳታ በተባበሩት መንግሥታት ቢሮ አስተባባሪነት ይደረግላቸዋል፡፡

ሁለተኛ **የልማት (የእድገት) ርዳታ** የሚባለው ከምግብ ርዳታ ወለል በላይ ያለው ርዳታ ሲሆን በቅድመ-ሁኔታ የሚሰጥ ነው፡፡ የሚሰጠው የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ግንባታ ሥርዓት ለዘረጉ እና/ወይም ያንን ለመዘርጋት አስተማማኝ ርምጃዎችን መውሰድ ለቻሉ አገሮች ብቻ ነው፡፡

የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት ለ24 ዓመታት (1991-2013) የምግብም የልማትም ርዳታ የተሰጠው የ1942-1975 የመአመ እና የገበያ ኢኮናሚን አጠናክሮ ቀጣይነቱን ለማረጋገጥ ከመአዓመ አብዮት መንግሥታት ጋር በመስማማቱና ውል በመፈራረሙ ነው (ምዕራፍ 17ን ተመልከት)፡፡ በ1991-2013 ጊዜ ውስጥ የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት ስምምነቱን በመጣስ የ1942-1975 የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓቱን በማፍረስ የብሔር አፓርታይድ መንግሥታዊ ሥርዓቱን ዘርግቷል፣ እንዲሁም የማፊያ ኢኮኖሚውን አስፋፍቷል፡፡

የመአዓመ አብዮት መንግሥታት በኢትዮጵያ የ1942-1975 የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት እንዲጠናከርና ቀጣይነት እንዲኖረው ለማድረግ ያልተቆጠበ ድጋፍ እየሰጡ ናቸው፡፡ አንደኛ፣ በጅቡቲ የኔቶ የጦር ኃይልን በማስፈር የኢትዮጵያ የግዛት አንድነትን እንዲጠበቅ አድርገዋል፣ የውጭ የጋላቢ የትሮይ ፈረስ አምባገነን መንግሥታት (ወይም አልሸባብን፣ ባኩሀራምን፣ አልቃይዳን እና አይሲስን የመሰሉ የውጭ የጥፋት ኃይሎች) የኢትዮጵያን ነጻነት እና ዳር ድንበር እንዳይደፍሩ እና የሕዝቡን ሰብአዊ መብቶች እንዳይገፉ ለማድረግ ችለዋል፡፡ የውጭ ጠላትን የመቋቋም የረጅም ጊዜ ታሪክ ያላት ኢትዮጵያ ያገሯ ዳር ድንበሯ የተጠበቀ እና የሕዝቧ ነጻነት ከውጭ የጥፋት ኃይል ተጽእኖ ነጻ እንዲሆን አድርገዋል፡፡

በዛሬ ጊዜ የኢትዮጵያ የግዛት አንድነት እየጠፋ እና የሕዝቡ ነጻነት እየተገፈፈ ያለው ጋላቢ ወይም የሚገራቸው ባጡ የኢትዮጵያ ተጋላቢ የትሮይ ፈረሶች፣ ኢትዮጵያውያን አረመኔዎች እና አሸባሪዎች (ኢተትፈአዎች) ነው (እኒህን የጥፋት ኃይሎች እነማን እንደሆኑ ለማወቅ V ን ተመልከት)፡፡ እኒህን የጥፋት ኃይሎች የኢትዮጵያ ሕዝብ መቆጣጠር ይችል ዘንድ የመአዓመ አብዮት መንግሥታት ከማስቻል ባለፈ የኢትዮጵያን ጦርነት የመዋጋት ግዴታ የለባቸውም፡፡ ኢትዮጵያውያን አገራቸውን ለማፍረስ እና የሕዝቡንም ነጻነት ለመግፈፍ ከራሳቸው ውጭ ምክንያት እንዳይኖራቸው ተደርገዋል፡፡

ሁለተኛ፣ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ምኅዳር በተጋላቢ የትሮይ ፈረሶች፣ አረመኔዎች እና አሸባሪዎች (ኢተትፈአዎች) ቁጥጥር ሥር መሆኑን የተገነዘቡት የመአዓመ አብዮት መንግሥታት ኢትዮጵያውያኑን ለመታደግ በአገራቸው ስደተኛውን በመቀበል ለማንም ስደተኛ ማህበረሰብ ያላደረጉትን ኢትዮጵያውያኑ ስለመአዓመ አብዮት እና ስለ 1942-1975 የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት እንዲጠናከርና ቀጣይነቱ የተረጋገጠ እንዲሆን የሚያስፈልገውን ርዳታ አድርገውላቸዋል፡፡ አሁንም ቢሆን ኢትዮጵያውያኑ እተፓዎችን እንዲፈጥሩ፣ እንዲደራጁ፣ በመአመ እና መአዓመ ፍርድ ቤቶቹ ተጠቃሚዎች እንዲሆኑና በኢትዮጵያና በዓለም ኗሪ የሆነው ኢትዮጵያዊ የ1942-1975 የመአመ እና ገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት የእውነቱ እውቀት ባለቤት እንዲሆን እንዲያስችሉት የመአዓመ አብዮት መንግሥታት ሠፊ ርዳታዎችን እያደረጉ ይገኛሉ፡፡[55]

---

[54] በእንግሊዝኛ Millennium Development Goals (MDG) ይባላል፡፡

[55] በሌላ አነጋገር ኢትዮጵያ በሞብ እና በሞራል ፀፀት በሽታ ተጠቂ ሕዝብ ሆሆይታ የምትገዛ አገር ሳትሆን በእውነት እውቀት በመመራት ሕዝበ-ውሳኔውን መስጠት በሚችል ሕዝብ እንድትተዳደር ለማድረግ የመአዓመ አብዮት መንግሥታት እና የተባበሩት መንግሥታት ያልተቆጠበ ጥረት ያደርጋሉ፡፡

ሶስተኛ የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥትን (1991-2013) የተካው የኃይለማርያም/ኢሕአዴግ መንግሥት (2013-) የመአዓመ ስምምነቶችን በመጣስ የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥትን ቀጣይ በማድረግ ኢትዮጵያን በአፓርታይድ መንግሥት እና በማፊያ ኢኮናሚ መቀጠል እንድትማቅቅ በማድረጉ የልማት (የእድገት) ርዳታ ተጠቃሚ እንዳይሆን ተደርጓል፡፡[56]

ባሁኑ ወቅት ወደ 15 ሚሊዮን የሚደርሱ ኢትዮጵያውያን የተባበሩት መንግሥታት እና የመአዓመ አብዮት መንግሥታት የምግብ ርዳታ እያገኙ ሲሆን ርዳታውን የማስተባበሩ፣ የሎጂስቲክስ ሥራዎችን እና የማከፋፈሉን ሥራ የሚያከናውኑት የዓለም አቀፍ የበጎ አድራጎት (የመንግሥት ያልሆኑ) ድርጅቶች (NGO) አና በመአዓመና በ1942-1975 የሠራተኛ ሕግ እና ሥርዓተ ደንብ የተቀጠሩ ኢትዮጵያውያን ናቸው፡፡ እንደሚታወቀው የወያኔ/መወቤካው (የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት) በ1991-2013 እኒህን ድርጅቶችና ኢትዮጵያውያን እንዳይሠሩ አግዷቸው ነበር፡፡[57] ከ2013 ወዲህ የኃይለማርያም/ኢሕአዴግ መንግሥት ኤንጂኦዎቹ እንዳይሠሩ፣ ባለሙያ ኢትዮጵያውያኑ እንዳይቀጠሩ እያደረገ አይደለም፡፡ የመአዓመ አብዮት መንግሥታት የኢትዮጵያን ሁኔታ ምን ያህል የተቆጣጠሩት እንደሆነ ለመረዳት እንድንችል የጥር 2008 “በኦሮምያ ክልል የተከሠተው ሰብአዊ መብት ጥሰት አስጊ ደረጃ ደርሷል” የሚለውን ማሳሰቢያ እናጢነው፡፡ የኃይለማርያም/ኢሕአዴግ መንግሥት በአንድ በኩል፣ የኦሮሞ ተለጣፊዎቹ፣ ታብተፓወቹ እና ተብጦፓዎቹ እንዲሁም መንግሥቱ እነዚህ የሚነዱቸው ሞቦች ናቸው ያላቸውን የመንግሥቱ የመብት ጥሰት ሰለባዎች ደግሞ በሌላ በኩል በጉዳዩ የሚሉትን አይተናል፡፡ ያንን ተከትሎ በመንግሥቱ ሚዲያ መንግሥቱ አጥፊዎች ያላቸውን በእሥር፣ ግድያ እና ድብደባ እንዲሁም ከሥራ እና መኖሪያቸው በማፈናቀል የተቆጣጠሯቸው መሆኑን ገልጧል፡፡ ምንም ያልተነገረለት የመአዓመ አብዮት መንግሥታት (እና የተባበሩት መንግሥታት) ጣልቃ ገብነት ባይኖር ኖሮ ሁኔታው በዛ መልክ አይገለጥም ነበር፡፡ የትግሬው ጦርና የተለጣፊው፣ ታብተፓው፣ ተብጦፓው ታጣቂዎችና ሞቦቻቸው የአጥፍቶ መጥፋት ጦርነትን ያካሄዱና የትግሬውን ጦር በአጥፍቶ መጥፋት ጦርነት ያጠፉት ነበር፡፡ ይኸ ሁኔታ በዘጠኙም የወያኔ/መወቤካው ክልሎች ተፈጻሚ ይሆን ነበር፡፡ የመአዓመ አብዮት መንግሥታት የኃይለማርያም/ኢሕአዴግ መንግሥት ታጣቂዎችን ደሞዛቸውን እንዲከፍል አስችለውታል፡፡ መጠነ ሰፊ ገንዘብ በማፍሰስ “አህያ ቢራገጥ ጥርስ አይሳበር” በሆነው ግጭት ሕዝቡ እንዳይጐዳ ቤንዚን እና ሌሎች ሸቀጦች ሁሉ ዋጋቸው እንዳይጨምር እና እንደልብ እንዲገኙ አድርገዋል፡፡ የተራቡትንም ኢትዮጵያውያን ከመንግሥቱ ቁጥጥር ውጪ በሆነ ርዳታ አና የሰው ኃይል እንዲረዱ ታድገዋቸዋል፡፡ በዚህ መልክ ግጭቱን በማርገባቸው ነው የጥር 2008 ግጭቶች ምንም ሳይባልላቸው የዓለም-አቀፍ “የዜናነት” ዋጋቸውን ያጡት፡፡[58]

አሁን ባለው ሁኔታ የመአዓመ አብዮት መንግሥታት የኃይለማርያም/ኢሕአዴግ መንግሥትን ፈቃድ ሳይጠይቁ በዓለም ሕግና በ1942-1975 የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓተ ሕግ መሠረት [በ1963 የመሠመድ (CPA) ሕግና ሥርዓት እንደሁም በ1964 የሠራተኛ ሕግ አና የሠራተኛ እና ማኅበራዊ እድገት ሚኒስቴር ሥርዓተ ደንብ መሠረት] ሠራተኛ እየቀጠሩ አና እያሠሩ ናቸው፡፡[59] ማንኛውም የእውቀት (ሙያ)፣ ሕጋዊ፣ የዜግነት እና የሥነ-ልቡናዊ ግዴታዎቹን የተረዳ ሠራተኛ በፈቃዱ የኃይለማርያም/ኢሕአዴግ መንግሥት ሠራተኛ አይሆንም፡፡ አሁንም ያሉት የመወቤካው ተቀጣሪዎች በመአዓመ እና በ1942-1975 መአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓተ ደንብ መሠረት የመንግሥት እና የግሉ ኢኮኖሚ ሠራተኞች እንሁን የሚሉ ስለሆነ የኃይለማርያም/ኢሕአዴግ መንግሥት ይኸን ፍላጐታቸውን ተፈጻሚ ካላደረገ የሥርዓቱን

---

[56] ከብዙ መመራምሮች አንዱ በምዕራፍ 19 የታየው የማለቂያ የለሽ ወጪ መመራምር (ማየወመ) (transaction cost theorem) የመአዓመ አብዮት መንግታት ለምን የኃይለማርያም/ኢሕአዴግን መንግሥት በምግብ ርዳታ እንዲወሰን እንዳደረጉት ያስረዳናል፡፡ ይኸ መመራምር የሚለው የመአዓመ አብዮት መንግሥታት ለኃይለማርያም/ኢሕአዴግ መንግሥት የልማት (እድገት) ርዳታ እንስጥ ቢሉ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ርዳታው ከሚሰጠው ጥቅም በሕዝቡ ላይ የሚያመጣው ጉዳት ሁሌም ይመዝናል፡፡ ለኃይለማርያም/ኢሕአዴግ መንግሥት የልማት (እድገት) ርዳታ በመስጠት የኢትዮጵያን የ1942-1975 የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚውን ለማጠናከር እና ቀጣይነት እንዲኖረው ማድረግ አይቻልም፤ ለማድረግ ቢሞክሩ እልፍ ዶላር ማውጣት ይኖርባቸዋል፡፡ ለኢትዮጵያም ሕዝብ ሆነ ለነሱም የሚበጀው የልማት (እድገት) ርዳታውን በማቆም የኃይለማርያም/ኢሕአዴግን መንግሥት በምግብ ርዳታ እንዲወሰን መገደቡ ይሆናል፡፡

[57] በXV እንደተገለጠው የመአዓመ አብዮት መንግሥታት ለወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት (1991-2013) የልማት እና የሰብአዊ (የምግብ) ርዳታዎችን ሲሰጡ ነበር፡፡ በኃይለማርያም/ኢሕአዴግ መንግሥት ዘመን (2013-) የሚሰጡት ርዳታ የሰብአዊ (የምግብ) ርዳታ ብቻ ሆኗል፡፡ ይኸ የሆነበት ምክንያት የኃይለማርያም/ኢሕአዴግ መንግሥት የልማት ርዳታ ተጠቃሚ የሚያደርገውን መስፈርት (የ1942-1975 የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ መጠናከር እና ቀጣይነቱን ማረጋገጥ) ማሟላት ባለመቻሉ ነው፡፡ የኃይለማርያም/ኢሕአዴግ መንግሥት በኢትዮጵያ የመአዓመን አብዮት ተፈጻሚነት ወይም የ1942-1975 የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ መጠናከር እና ቀጣይነት መግታት እንዳይችል ተደርጓል፡፡ ለመግታት ቢሞክር ስለነዚህ እውቀት ያላቸው፣ ለመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓቱን የዘረጉ እና መስዋእት የከፈሉ ኢትዮጵያውያንና የመአዓመ አብዮት መንግሥታት ይፋረዱታል፡፡

[58] በመአዓመ አብዮት መንግሥታት የኃይለማርያም/ኢሕአዴግ መንግሥት የ1942-1975 የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓቱ ተጠናክሮ እና ቀጣይ ከመሆን ሊገታው እንዳይችል ተደርጓል፡፡

[59] የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት ሠራተኛ የሚቀጥረው በብሔር፣ በኢሕአዴግ አባልነት፣ በዝምድና፣ ለሥርአቱ ታማኝነት፣ ወዘተ ሲሆን በ1942-1975 ሕገ-ደንብ መሠረት ሠራተኛ የሚቀጠረው በእውቀቱ (ሙያው)፣ የሥራ ልምዱ እና ግዴታዎቹን ያወቀ በመሆኑ በክፍት ውድድር ያለ ምንም የጾታ፣ የብሔር ወይም ሀይማኖት ተጽእኖ (መድልኦ) አሸናፊ ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡ ከ2013 ወዲህ የመአዓመ አብዮት መንግሥታት “የልማት ርዳታውን” በማቆም ላይ ይገኛሉ፡፡ የኃይለማርያም/ኢሕአዴግ መንግሥት “የልማት ርዳታውን ቅድመ ሁኔታ ማሟላት ባለመቻሉ “በምግብ (ሰብአዊ) ርዳታ” እንዲወሰን ተደርጓል፡፡ እሱም በኃይለማርያም/ኢሕአዴግ መንግሥት በኩል ሳይሆን በተባበሩት መንግሥታት በቀጥታ ለተጐጂው ሕዝብ እየተሰጠ ነው፡፡

ሠራተኞች የሚከፍለው ገንዘብ የለውም። የመአዓመ አብዮት መንግሥታት በአንድ በኩል በፈጠሯቸው ኤንጂዎች አማካይነት በመአዓመ አብዮት እና በ1942-1975 የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓተ ሕግ የሚሠራ ሕጋዊ፣ ሙያዊ፣ የዜግነት እና ሥነልቡናዊ ግደታውን የተረዳ ሠራተኛ ሲቀጥሩ እና ሲፈጥሩ፣ በሌላ በኩል ደግሞ በትግሬ አለቃ እና በተለጣፊ ባለሥልጣን ትእዛዝ የሚሠራ የኃይለማርያም/ኢሕአዴግን የጥፋት ሠራዊት ደሞዝ መክፈል ዘላቂነት ያለው ሥራ አይደለም። የኃይለማርያም/ኢሕአዴግ መንግሥት ባሁኑ ወቅት የመንግሥትን ሥራዎች እየሠራ አይደለም። ሠራተኛው ተከፋፍሏል፣ አትራፊ እና ጠቀሜታ ያለው የመንግሥት አገልግሎት እየሰጠ አይደለም። የኢትዮጵያ ሕዝብ አሁን እንደሚረዳው የመአዓመ አብዮት መንግሥታት ለኃይለማርያም/ኢሕአዴግ መንግሥት ሠራተኞች (ማለትም ለወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት ተቀጣሪዎች) በ1942-1975 የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት ተጠናክሮ ቀጣይነት የሚያገኝበትን ሥራ እስከሠሩ ድረስ የኮንትራት ደሞዛቸውን የሚከፍሏቸው መሆኑን ለኃይለማርያም/ኢሕአዴግ ያረጋገጡለት መሆናቸውን ነው። ለብዙ ዓመታት የእንግሊዝ መንግሥት የበጀት ድጋፍ፣ ሌሎቹም የመአዓመ አብዮት መንግሥታት የተለያዩ የውጭ ምንዛሪዎችን ለዚሁ የመአዓመ አብዮት ዐላማ ማስፈጸሚያነት ይለግሱ እንደነበረ ታውቋል።

የወያኔ/መወቤካው መንግሥት (1991-2013) አቶ መለሰ እና አቡነ ጳውሎስ ሲሞቱ (የሞቱትም የፈጠሩት የአፓርታይድ መንግሥት እና የማፊያ ኢኮኖሚያቸው በህይወት እያሉ በመፍረሱ ምክንያት በመደንገጣቸው እንደሆነ ይነገራል) አብሮ የፈረሰ መሆኑን በXII ተመልክተናል። ነገር ግን በወያኔ/መወቤካው የተፈጠረው የተለጣፊው መንግሥት (የሳሎን ካቢኔው እና የክልሉ መንግሥት)፣ የመንግሥት እና የግሉ የማፊያ ፋብሪካዎች እና ተቀጣሪዎቹ የወያኔ/መወቤካው መንግሥት ቢፈርስም እነሱ ግን አሉ። በሌላ አነጋገር የኃይለማርያም/ኢሕአዴግ መንግሥት(2013-) የመወቤካው/ኢሕአዴግ መንግሥት (1991-2013) ያለመወቤካው ሆኗል።

ሠራተኛው ያለበትን ሁኔታ እና የሕግ፣ የሙያ፣ የዜግነት እና የሥነ-ልቡናዊ ግዴታዎቹን እየተረዳ ሲመጣ ለወያኔ/መወቤካው መንግሥት (ለሌለ መንግሥት) እሞታለሁ፣ ለአቶ ስብሃት ወደ ሥራውና ሥልጣኑ እንዲመለስ እታገላለሁ እያለ አይደለም።[60] እያለ ያለው በ1942-1975 የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ የሠራተኛነት መብታችን እና የሥራ ዋስትናችን ይከበርልን ነው።

የወያኔ/መወቤካው መንግሥት የጥፋት ሥራዎችን እንዲሠራለት እና ለትግሬው በሕግ ከለላነት (በሕግ ተጠያቂነት) እንዲያገለግል ያሠማራውም የሳሎን ካቢኔ መንግሥት እና የክልል መንግሥቱ ሠራተኛ የአፓርታይድ መንግሥቱን የምሥጢር መመሪያዎች እና የትግሬ አለቃውን እና የተለጣፊው ባለሥልጣን ትእዛዞችን አስፈጻሚዎች አይደለንም እያለ ይገኛል። ሠራተኛው እያለ ያለው ያለብንን የዜጋ፣ የሕግ፣ የሙያ እና የሥነ-ልቡናዊ ግዴታዎቻችንን የተረዳን ስለሆንን በ1942-1975 የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት እና ሕግ እንተዳደር ነው።

(ሀ) የመንግሥት ሠራተኛው ሁሉ (በ1942-1975) በ1963/1955 የመንግሥት ሠራተኛ መተዳደሪያ ድርጅት ማቋቋሚያ አዋጅ እና ደንብ [1963 Central Personnel Agency (CPA) Establishment Proclamation and Regulations] እንተዳደር ባይ ነው።

(ለ) የግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ ሠራተኛ ሁሉ የሠራተኛ መብታችን እና የሥራ እና የመኖር ዋስትናችን በ1964/1956 የሠራተኛ ሚኒስቴር ሥርዓት እና ደንብ መሠረት ይጠበቅልን እያለ ይገኛል።[61]

ዛሬ በማንኛውም የሥራ ቦታ የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት ባለሥልጣናት እና የነሱን ትእዛዝ አስፈጻሚ የሆነው ሠራተኛ ተፋጠዋል። በሌላ በኩል ደግሞ የመወቤካውን መፍረስ ተከትሎ ትግሬዎቹ እና ተለጣፊዎቹ (ትግሬ ያልሆኑት) ባለሥልጣናት አብረው እና ተባብረው መሥራት አልቻሉም። የሁለቱ ፍጥጫ ሥርዓቱ ለፈጠረው የቢሮክራሲ የጥፋት ሠራዊት ዝርፊያ እና የወንጀል ሥራዎችን እንዲሠራ እና ሰብአዊ መብቶችን እንዲገፍ አመቺ ሁኔታን ፈጥሮለታል። የሚከተሉትን ሁለት ክስተቶች እንመልከት፣

---

[60] ተቀጣሪ የመንግሥቱ የማፊያ ኢኮኖሚ እና የወያኔ/መወቤካው የተለጣፊ መንግሥት ሠራተኛው ዛሬ የወያኔ/መወቤካው መንግሥት ለጥፋት ሥራ እና የሕግ ከለላ እንድሆነው የሚከፍለኝን ገንዘብ፣ የትግሬ ማፊያውን ባለንብረት፣ ባለሥልጣን፣ አልከሰስም እና ሁሉም ይገባኛል ባይ እንዲሆን የሚያስችለውን ገንዘብ እና ጠቅላላውን የመንግሥቱን ሠፊ የወጪ መሸፈኛ ገንዘብ ከየት አመጣው? ብሎ ለመጠየቅ ችሏል። በራሱ ሕዝብ ላይ ዘማች የሆነውን የትግሬ እና የተለጣፊውን ጦር ወጪዎች የሚሸፍነው በዝርፊያ ገንዘብ መሆኑንም እየተረዳ መጥቷል።

[61] የ(ሀ) እና (ለ) የተመሠረቱት በተባበሩት መንግሥታት የሰብአዊ መብት ድንጋጌ (UN Bill of Human Rights) እና በዓለም-አቀፍ የሠራተኛ ድርጅት ስምምነት (Convention of the international Labour Organization, ILO) ስለሆነ ሠራተኛው በዓለም ሕግ እንተዳደር ባይ ነው።

**የትግሬ አለቃ እና ተለጣፊው ባለሥልጣን የሥርዓቱን የጥፋት ሠራዊት ለጥፋቶች ተጠያቂ ሲያደርጉ**

በኃይለማርያም/ኢሕአዴግ የግዛት ዘመን (2013-) አቶ አስታጥቄ (የፈጠራ ስም) ከ30 ዓመታት በፊት በየካ ክፍለ ከተማ የሠራው ቤት በሕገ-ወጥ መንገድ የተሠራ ነው ተብሎ በቀበሌዎቹ ይታሸጋል፡፡ የኢቲቪ ጋዜጠኞች በቦታው በመገኘት አስታጥቄን እና የአካባቢውን ሰዎች በማነጋገር ቤቱ የተሠራው በአቶ አስታጥቄ መሆኑን እና የሠራውም በሕጋዊ፣ ፍትሐዊ እና ሥነ-ልቡናዊ ተቀባይነት ባለው መንገድ መሆኑን ያረጋግጣሉ፡፡
የትግሬ አለቃው እና ተለጣፊው ተሿሚ እና የኢቲቪ ጋዜጠኞች በዚህ አኳኋን የሕጋዊ፣ ፍትሐዊ እና ሥነልቡናዊ ግዴታዎቹን ያልተገነዘበውን ወይም ግዴታውን አውቆ ለገንዘብ የሸጠውን የቀበሌ ተቀጣሪ በካንጋሩ ፍርድ ቤታቸው እንዲቀርብ በማስገደድ ቅጣቱን እንዲቀበል ያደርጋሉ፡፡

እዚህ ላይ ከተሰጠው ቀረባ ሦስት ጉዳዮችን እንድናጤናቸው ይገባል፡፡

አንደኛ፣ የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት የቀበሌ ሠራተኛውን የሚቀጥረው በብሔሩ (ወይም ሐይማኖቱ)፣ በብሔር ፓርቲ አባልነቱ፣ የትግሬ አለቃው እና የተለጣፊው ባለሥልጣን ትእዛዝ አስፈጻሚ መሆኑን እና የትምሕርት ወይም የሙያ እውቀት የሌለው መሆኑን በማረጋገጥ ነው፡፡

ሁለተኛ፣ የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት ሙያቢሱን የቀበሌ ሠራተኛ የቀጠረው የጥፋት ሥራዎችን እንዲሠራለት እና ለትግሬው እና ለተለጣፊው ባለሥልጣን የሕግ ተጠያቂ (ከለላ) በመሆን እንዲያገለግለው ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ የሚያገለግል ሰው የሕግ፣ የሙያ፣ የዜግነት፣ እና የሥነልቡና ግዴታዎቹን ያልተገነዘበ ነው፡፡

የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት እራሱ ለጥፋት ሥራ የቀጠረውን ሰው ጥፋተኛ ነው ብሎ የሚቀጣ ነው፡፡ በቀበሌው ተቀጣሪ የጥፋት ሥራ በደል የተፈጸመበት አቶ አስታጥቄ በደል የፈጸሙበት የትግሬ አለቃው እና የተለጣፊው ሹመኛ መሆናቸውን ይገነዘባል ብለው አይገምቱም፡፡ እነዚህ ሹመኞች መአመ በመፍረሱ እና ከሕግ በላይ ስለሆኑ በሕግ ተጠያቂዎች አይደሉም፡፡ አድራጊ እና ፈጣሪዎቹ እነሱው ስለሆኑ እና የሚጠይቃቸው ስለሌለ የዜጋ፣ የሕግ፣ የሙያ እና የሥነ-ልቡናዊ ግዴታዎቻችንን አላሟላንም ብለው አይጨነቁም፡፡

ሦስተኛ፣ የጥፋት ሥርዓቱን ገላጭ የሆነው ጉዳይ ደግሞ አቶ አስታጥቄ በ1942-1975 በመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት ልተዳደር በማለቱ ይኸ ሁሉ ግፍ ያለካሳ ክፍያ ሲፈጸምበት፣ በ1991-2013 የመወቤካው እና የማፊያ ኢኮኖሚው ሥርዓት በሕገ-ወጥ መንገድ (በዝርፊያ፣ በሙስና፣ በማጭበርበር፣ በኰንትሮባንድ ንግድ፣ ወዘተ) ተጠቃሚው የሆነው ትግሬው (የኢሕአዴግ መንግሥቱ እና የግሉ ኢኮኖሚ ማፊያው) በማንም ምንም አይነካም፡፡ የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት በቀበሌ ተቀጣሪው የጥፋት ሥራ ድራማው የዜሮ ድምር ጨዋታ እየተጫወተ ነው፡፡ የቀበሌውን ተቀጣሪ አስታጥቄን እንዲበድል ካደረገው በኋላ የቀበሌውን ተቀጣሪ በመቅጣት የአስታጥቄ "እንባ አባሽ" ሆኖ ይቀርባል፡፡ መወቤካው (1991-2013) ስለፈረሰ ይኸ ድራማ እየተፈጸመ ያለው የኃይለማርያም/ኢሕአዴግን የሳሎን እና የክልል መንግሥቱን (የተለጣፊውን መንግሥት) በሚቆጣጠሩት የመወቤካው ተሿሚዎች ነው፡፡

**የጥፋት ሠራዊቱ እምቢተኛነት ሲረጋገጥ**

የብሔር ክልሉ የፖሊስ ጣቢያው ኃላፊው ትግሬ የክልሉ ብሔር ተቀጣሪ ፖሊሶቹን የታሠሩትን ሰዎች በጭለማ ወደ ተወሰነ ቦታ እንደተለመደው ወስደው እንዲያስረክቡ የቃል እትዛዝ ይሰጣቸዋል፡፡ የቃል ትእዛዝህን መፈጸም ከተጠያቂነት አያድነንም፡፡ በፍርድ ቤት ትእዛዝ እንጂ ሰዎችን የማሠር ሥልጣን የለንም፤ ሌላ የሙብት ገፈፋ ሥራ (ያውም በቃል ትእዛዝ) አናደርገውም ይሉታል፡፡ የፖሊስ ትምህርቱ ስለሌለህ (ስለማታውቀው) እንጂ ከ 24 ሰዐት በላይ ማሠርም አይቻልም ብለው ይነግሩታል፡፡ የፖሊስ ተቀጣሪዎቹ ያለባቸውን የዜግነት፣ የሕግ፣ የሙያ እና የሥነ-ልቡና ግዴታቸውን የተረዱ ስለሆኑ ለትግሬው አለቃ አና ለተለጣፊው ሹም ትእዛዝ አስፈጻሚዎች አይደለንም እያሉ ናቸው፡፡

በ1991-2013 በተዘረጋው የወያኔ/ኢሕአዴግ የአፓርታይድ እና የማፊያ ሥርዓት የትግሬ አለቃው ከመወቤካው እና ከተለጣፊው መንግሥት የውሳኔ ደብዳቤ በማስመጣት ተቀጣሪውን የጥፋት ሠራዊቱንም ሆነ የተለጣፊውን ሹመኛ አዞ ፍላጐቱን ተፈጻሚ ማድረግ ይችል ነበር፡፡ አሁን መወቤካው ስለሌለ (ስለፈረሰ) የትግሬ አለቃው ያንን ማድረግ አይችልም፡፡ ብቻውን ያለአጋር የቀረ ግለሰብ ሆኗል፡፡ ተለጣፊው ተሿሚም የጥፋት ሠራዊቱም የትግሬ አለቃቸውን "ማነው የሾመህ? ሥራህ ምንድነው? የሚከፈልህስ ደሞዝ ስንት እና ከየት የመጣ ነው?" ብለው እየጠየቁ መሆናቸው እየተነገረ ነው፡፡ የትግሬ አለቃው መልስ የለውም፡፡ ሌሎቹ ወያኔዎች በዝርፊያ ገንዘብ የምሥጢር ሥራቸውን በመተው መኖር እንደቻሉ ይኸ የመንግሥት ሥራውን መኖሪያው ያደረገ ትግሬ ማምለጫ አጥቷል፡፡

አንዳንድ የቀበሌዎቹን ሰዎች እና እምቢ ባይ የፖሊስ አባላትን አነጋግሬአለሁ፡፡ ምን ያህል የአይነታቸው ወኪሎች መሆናቸውን ማረጋገጥ ባልችልም፣ በ1991-2013 እና ከዚያም በኋላ በትግሬ አለቃ ሁልጊዜ የምንታዘዘው ትግሬ ያልሆነውን

ዜጋ እንድንበድል ነው ብለዋል፡፡ በሚሠሩት ሥራ ጉዳት የደረሰባቸው ትግሬዎች እንደሌሉም አረጋግጠውልኛል፡፡ ሁልጊዜ በነሱ ጥፋት የተጐዱት ወይም የሚጐዱት ትግሬዎች ያልሆኑት ናቸው፡፡

የክልል ሠራተኞችም ቢሆኑ የወያኔ መወቤካውን መንግሥት ዐላማ (የትግራይን ነጻነት እና የትግሬውን ጥቅም) አስከባሪዎች አይደለንም ባዮች ሆነዋል፡፡[62] የሠራተኛው ፍላጐት ግን በመአዓመ አብዮት መንገድ (በ 1942-1975 የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት) እንተዳደር የሚል ነው፡፡ የወያኔ/መወቤካውን መንግሥት ዓላማ (የትግራይን ነጻነት እና የትግሬውን ጥቅም) አስፈጻሚዎች እና የመንግሥቱን የምሥጢር መመሪያዎች እና የትግሬ አለቃ እና የተለጣፊው ባለሥልጣናትን ትእዛዝ ፈጻሚዎች አይደለንም እያሉ በኢቲቪ እና በአደባባይ ስብሰባዎች እየተናገሩ ናቸው፡፡[63]

የወያኔ/መወቤካው መንግሥት የ1942-1975 የገንዘብ ገበያውን (the money and financial market) ያፈረሰው በመሆኑ እና በምትኩ "የብሔር ባንኮች" ማቋቋሙና የመአመ የብሔራዊ ባንኩን ሥልጣንም የገፈፈው በመሆኑ የትግሬ (የመንግሥቱን እና የግሉን) ማፊያውን እና ተለጣፊውን ሲጠቅምበት ከዛ ውጪ ያለውን ሕዝብ የገንዘብ ባለቤትነት እና በገንዘብ የተጠቃሚነት መብቱን ገፎታል፡፡[64]

ያለፈው የጥር 2008 (January 2016) የመአዓመ አብዮት መንግሥታት "በኢትዮጵያ የሰብአዊ መብት ጥሰት አደጋ አስጊ ደረጃ ደርሷል" የሚለው ማሳሰቢያ ሁለት ነገሮችን ግልፅ አድርጓል፡፡ አንደኛ በኢትዮጵያ የመአዓመ አብዮት ተፈጻሚ እንዳይሆን አድራጊ እና የ1942-1975 የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚውን እንዳይጠናከር እና ቀጣይነት እንዳይኖረው ያደረገው የወያኔ/መወቤካው ምሥጢራዊ መንግሥት ከመለሰ እና ከአቡነ ጳውሎስ (ሁለቱ የመወቤካው መሪዎች) መሞት ጋር ወድቋል ወይም ፈርሷል፡፡

የመወቤካው አባላት ለጥፋቱ ሁሉ አቶ መለሰን ተጠያቂ ሲያደርጉ፣ አንዳንዶቹም ተቃዋሚ ፓርቲዎች ሲያቋቁሙ ሌሎች ደግሞ ሌሎች ተቃዋሚ ፓርቲዎችን ተቀላቅለዋል፡፡ አሳዛኙ ጉዳይ እኒህ የወያኔ/መወቤካው አባላት እራሳቸውን ለጥፋቶቹ ተጠያቂዎች አለማድረጋቸው እና የሕግ፣ የዜግነት፣ የሙያ እና የሥነ-ልቡናዊ ግዴታቸውን ባለመወጣታቸው እስከ ዛሬ ድረስ በመአዓመ እና በመአመ ፍርድ ቤቶች ተጠያቂዎች አለመደረጋቸው ነው፡፡ የሥርዓቱ ተጠቃሚዎች እና የሞራል ፀፀት (moral hazard) በሽታ ተጠቂዎች "የመወቤካው አባል አይደለንም፤ የወያኔ/ኢሕአዴግ ፓርቲ አባል አይደለንም፤ ተለጣፊውን፣ ታብተፓውን፣ ተብጦፓውን እና ሞቦቹን እንቃወማለን እንዲሁም እኛ የኢትዮጵያን የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት መጠናከር እና ቀጣይነት ደጋፊዎች ነን" እያሉ ናቸው፡፡

ሁለተኛ ተለጣፊዎቹ፣ ታብተፓዎቹ፣ ተብጦፓዎቹ እና ሞቦቹ የወያኔ/መወቤካው መንግሥት ለሰጣቸው "ለክልላችን (ዞን፣ ወረዳ እና ቀበሌ)፣ ለብሔራችን፣ ለባንዲራችን፣ ለነጻነታችን እና ለቋንቋችን እንሞታለን" ሲሉ፣ በሌላ በኩል ደግሞ በወያኔ/መወቤካው መንግሥት (በወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት) የሌሎቹን ብሔር አባላት(ወይም የህይማኖት ተከታዮች) ገላችኋል፣ ከክልላችን ውጡ በማለት ከሥራ እና ከመኖሪያቸው አፈናቅላችኋል፣ ንብረታቸውን ዘርፋችኋል፣ ወዘተ ተብለው እነሱ እና እነሱ የሚነዷቸው ሞቦች ይከሰሳሉ፡፡ ሌላው በጥር 2008 የተከሰተው አስገራሚው ጉዳይ እኒህኞቹ ብሄርተኞች እና የህይማኖት ማርክሲስቶች (ተጋላቢ የትሮይ ፈረሶች) የብሔር መለያቸውን አሽቀንጥረው በመጣል የሰብአዊ መብት አክባሪዎች ነን ማለታቸውና ከወያኔ ጋ በመሆን በደል የፈጸሙባቸውን ወገኖች የወያኔ/መወቤካውን እና የወያኔ/ኢሕአዴግን መንግሥት ተባብረን እንጣል ባዮች መሆናቸው ነው፡፡[65]

---

62 የክልል መንግሥት (የወረዳ፣ ክ/ከተማ እና ቀበሌዎችን ጨምሮ) የወያኔ/መወቤካው መንግሥት የወያኔን ዓላማ ተፈጻሚ ለማድረግ የፈጠረው ሲሆን በመአመ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት አይደለም፡፡ የሠራተኛው የሥራ እና የሥራ ዋስትና መብቶቹ ከመጀመሪያውም የተከበሩ አልነበሩም፡፡

63 የክልል መንግሥት (የወረዳ፣ ክ/ከተማ እና ቀበሌዎችን ጨምሮ) የወያኔ/መወቤካው መንግሥት የወያኔን ዓላማ ተፈጻሚ ለማድረግ የፈጠረው ሲሆን በመአመ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት አይደለም፡፡ የሠራተኛው የሥራ እና የሥራ ዋስትና መብቶቹ ከመጀመሪያውም የተከበሩ አልነበሩም፡፡

64 በ1991-2013 የመወቤካው መንግሥት ተጠቃሚ የሆነ ትግሬ መረጃ ያልተያዘበት ገንዘብ ከብሔራዊ እና ከንግድ ባንኩ ይሰጠዋል፡፡ የዛን ጊዜም ሆነ ከ2013 በኋላ የሌላ ብሔር አባል በ1942-1975 በመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት ሕግና ደንብ መሠረት እንዲበደር ይገደዳል፡፡ ይኸንንም ብድር ለማግኘት ጉቦና ከገበያው ዋጋ በላይ የወለድ ክፍያ እንዲከፍል ይጠየቃል፡፡ ያንንም ፈጽሞ ገንዘቡን በሕጋዊ፣ ፍትሐዊ እና ሥነ-ልቡናዊ ተቀባይነት ባለው መንገድ ያገኘ መሆኑን የሚያረጋግጥለት የመልካም አስተዳደር መንግሥት (መአመ) ስለሌለ የገንዘብ ባለቤትነት መብቱ የተከበረ አይደለም፡፡ ይኸንን የተረዱ የሥርዓቱ ደጋፊ እና ተጠቃሚ የሆኑ ትግሬዎች በወያኔ/መወቤካው መንግሥታቸው ላይ እምነት ስለሌላቸው ገንዘባቸውን በትግሬዎቹ ባንኮች ሳይሆን በሌሎቹ የብሔር ባንኮች ሲያስቀምጡ ይታያሉ፡፡ ዋናዎቹ ወያኔዎች ደግሞ ገንዘቡን በውጭ ምንዛሪ ቀይረው በውጭ አገር ባንኮች ውስጥ ያስቀምጣሉ፡፡ የወያኔ/መወቤካው መንግሥት ለትግሬ ባንኮቹ ህይወት ለመስጠት ሲል ማንኛውንም ለመንግሥት ክፍያ ፈጻሚ ግለሰብ ወይም ድርጅት በትግሬ ባንክ በኩል ክፍያውን እንዲፈጽም ያስገድደዋል፡፡

ከ2013 በኋላ የኃይለማርያም/ኢሕአዴግ መንግሥትን የሚቆጣጠሩት ትግሬዎች (የወያኔ/መወቤካው መንግሥት ተቀጣሪዎች) መወቤካው የሌለ ወይም የፈረሰ ስለሆነ፣ ሁሉም የባንክ ተጠቃሚ በ1942-1975 የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት እና ሕግና ደንብ መሰረት እንዲሆን እያደረግን ነው ባዮች ሆነዋል፡፡

65 መጽሐፉ የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት የዜሮ ድምር የፖለቲካ ጨዋታ ተጫዋች መሆኑን ያስረዳል፡፡

በ1991-2013 ተለጣፊ ባለሥልጣኖች በዋሽንግተን፣ በጀርመን፣ ስዊድን እና ደቡብ አፍሪካ ቦንድ እንሸጣለን እያሉ ዝርፊያ ሲያካሄዱ እንደነበር ይታወቃል፡፡ በኃይለማርያም/ኢሕአዴግ መንግሥት (2013-) እነህ ተለጣፊዎች ይኸንን የውንብድና ሥራ አቁመዋል፡፡ እንዲያቆሙ ያስገደዳቸው ብዙ ምክንያት አለ፡፡ አንደኛ በመአዓመ አብዮት መንግሥታት አገራት የተሰባሰበው ኢትዮጵያዊ እነህን ጥፋተኞች ተጠያቂ እንዲያደርጋቸው የዜግነት እና የስደተኛነት የሕግ ግዴታዎች አሉበት፡፡ የኢትዮጵያ ዲያስፖራው እየተደራጀ እና እነህ ግዴታዎቹን እየተገነዘበ ሲመጣ እነህን የወያኔ/ኢሕአዴግ ተለጣፊዎች በመአመ ፍርድ ቤቶች ተጠያቂዎች እንደሚያደርጋቸው ተረጋግጧል፡፡ የኢትዮጵያዊነት እና የሰብአዊነት ሥነ-ልቡናዊ ግዴታዎቹ በተጨማሪ እነህን ጥፋተኞች ለሕግ ተጠያቂዎች ማድረግ እንዳለበት ያስገነዝቡታል፡፡

ሁለተኛ የመአዓመ አብዮት መንግሥታት በአገራቸው ከጥፋት በማምለጥ የተጠለሉትን ኢትዮጵያውያን እንዲደራጁ እና በመአመ እና በመአዓመ ፍርድ ቤቶች ተጠቃሚዎቹ እንዲሆኑ ሁኔታዎችን አመቻችተውላቸዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ተለጣፊው ለትግሬው ጥፋት ሠሪ እና የሕግ ከለላ ሆኖ ለማገልገል አሳማኝ ምክንያት አጥቶበታል፡፡

ሶስተኛ እና ዋናው ጉዳይ የወያኔ/መወቤካውን መንግሥት የጥፋት ሥራዎችን በመሥራት እና ሕጋዊ ከለላ (ሽፋን) በመስጠት ወይም መከለያ (የህግ ተጠያቂ) በመሆን ትግሬውን አገልጋይ ላለመሆን የተለጣፊው ባለሥልጣንን የከለከለው ያለበት የዜግነት፣ የሕግ፣ የሙያ እና የሥነ-ልቡና ግዴታዎቹን መረዳቱ ነው፡፡[66] መለስ ከሞተ እና የኃይለማርያም/ኢሕአዴግ መንግሥት ሥልጣኑን ከተረከበ ወዲህ ትልቅ የመአዓመ አብዮት እመርታ ይታያል፡፡ የኃይለማርያም/ኢሕአዴግ መንግሥት ተለጣፊ ባለሥልጣኖች ያለባቸው የሕግ፣ የዜግነት፣ የሙያ እና የሥነ-ልቡናዊ ግዴታ የ1942-1975 የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት እንዲጠናከር እና ቀጣይነት እንዲኖረው ማድረግ መሆኑ ለማንም ግልፅ ሆኗል፡፡

ለትግሬው ጦር ያደረው የተለጣፊ ጦር በኃይለማርያም/ኢሕአዴግ ዘመነ መንግሥት (ከ2013 ወዲህ) በራሴ ሕዝብ ላይ አልዘምትም፣ ከውጭ ጠላት ጥቃት አገሬን እጠብቃለሁ፣ ሰብአዊ መብቶች እንዲከበሩና የ1942-1975 የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት እንዲጠናከር እና ቀጣይነት እንዲኖረው እታገላለሁ እያለ ነው፡፡[67] ነገር ግን ትላንት በወያኔ/መወቤካው መንግሥት ዘመን የትግሬ እና ተለጣፊው ጦር ይፈጽም የነበረውን ግድያ እና ሰብአዊ መብት ገፈፋ (ለምሳሌ የፍርድ ቤት ትእዛዝን አልቀበልም በማለት፣ ሰላማዊን ሕዝብ ያለ ፍርድ ቤት ትእዛዝ ማሠር እና መግደል እና በአጠቃላይ ከሕግ በላይና አድራጊ እና ፈጣሪ መሆን) በኃይለማርያም/ኢሕአዴግ ዘመንም እየፈጸመ ይገኛል፡፡[68] በተለይ የተለጣፊው ታጣቂ የሕግ፣ የዜግነት፣ የሙያ እና የሥነልቡናዊ ግዴታውን መገንዘብ ያልቻለውን የትግሬ አለቃ እና የተለጣፊው ጦር አዛዥ ትእዛዝ አስፈጻሚ አለመሆኑን እያረጋገጠ ይገኛል፡፡ የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት ተቀጣሪው ታጣቂ በ1942-1975 የምድር ጦር፣ መርከበኛ፣ ፖሊስ እና የአየር ኃይል አካዳሚዎች ምሩቃን እየተመራን በ1942-1975 የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት እንዲጠናከር እና ቀጣይነት እንዲኖረው ለማስቻል የሕግ፣ የዜግነት፣ የሙያ እና የሥነ-ልቡናዊ ግዴታችንን እንወጣለን እያለ ነው፡፡

የተለጣፊው መንግሥት (ማለትም የወያኔ/መወቤካው የሳሎን ካቢኔው እና የክልል መንግሥቱ) ሠራተኛም በ1942-1975 የመአመ እና የገበያ ኢኮናሚ ሥርዓት ሕግ ነው እንጂ የምንተዳደረው ሙያቢስ የሆነው የትግሬ አለቃ እና የተለጣፊው ባለሥልጣን በየደቂቃው ተለዋዋጭ የሆነውን ትእዛዝ አስፈጻሚ አለመሆኑን በተጨባጭ ማረጋገጥ ችሏል፡፡ ይኸንን አቋም መውሰዱን እየገለጠ ያለው የሴላ ብሔር አባሉ ብቻ ሳይሆን የሥርዓቱ ተቀጣሪ ትግሬው ጭምር መሆኑ ሊሠመርበት ይገባል፡፡ የኃይለማርያም/ኢሕአዴግ መንግሥት የተለጣፊው መንግሥት (ማለትም የወያኔ/መወቤካው የሳሎን ካቢኔው እና የክልል መንግሥቱ) ሠራተኛውን በፊት በ 1991-2013 እንደተለመደው ሊያዘው አልቻለም፡፡

---

[66] የኃይለማርያም/ኢሕአዴግ ባለስልጣኖች ባሁኑ ወቅት እያሉ ያሉት ከፈለገ የኃይለማርያም/ኢሕአዴግ መንግሥት ለምን በነሱ ቦታ ትግሬዎቹን ሾሞ አያሠራቸውም ነው፡፡ እያሉ ያሉት እኛ ባጠፋነው እንጠየቅ፣ ነገር ግን ለጥፋቱ ዋና ተጠያቂ እና የሥርዓቱ ተጠቃሚው ትግሬው እራሱን ተጠያቂ ማድረግ ወይም ተጠያቂ እንዲሆን መደረግ አለበት ነው፡፡ በ2016 መግቢያ ጀምሮ የኃይለማርያም/ኢሕአዴግ መንግሥት ስለመልካም አስተዳደር መንግሥት ያወራል፣ ብዙ ተለጣፊዎችን እያሰረ እና በካንጋሩ ፍርድ ቤቶቹ እየከሰሰ መሆኑንም ይገልጣል፡፡ ነገር ግን ስለ ሥርዓቱ ዋና ተዋንያን እና ተጠቃሚዎች ስለሆኑት ትግሬዎች ምንም በማንም አይነገርም፡፡

[67] የኢትዮጵያ ጦር ተመሳሳይ አቋም በመውሰድ እንዴት የአምባገነኑን የደርግ/ኢሰፓ መንግሥት ከሥልጣን እንዳወረደው፣ የግዙፉን ጦር ተራ ወታደር ከፀፀት ኑሮ እንዴት እንዳዳነው እና የኢትዮጵያን ሕዝብ ከብጥብጥ እና ከጥፋት ጦርነት የጦር መሪዎቹ የራሳቸውን የህይወት መስዋእት በመክፈል እንዴት ሊያድኑት እንደቻሉ ተመልክተናል (አሁን በአረብ እና አፍሪካ አገሮች የአገሪቱ ታጣቂ የአምባገነኑ መንግሥት መሣሪያ በመሆን ሕዝቡን እያጠፋው መሆኑን ተመልከት)፡፡

[68] በ2005 ምርጫ የትግሬው ጦር የቅንጅትን ደጋፊዎች ሲጨፈጭፍ የአዲስ አበባ ፖሊስ እንደታገተ እና ተሳታፊ እንዳልነበረ ይነገራል፡፡ በጥር 2016/2008 የኦሮምያ ክልል ጭፍጨፋ የትግሬው ጦር ተለጣፊ የብሔር ጦሮቹን ከሌሎች ክልሎች አምጥቶ ሲጠቀምባቸው የመንግሥቱ የኦሮምያ ክልል ታጣቂዎች አልተሳተፉም የሚል ትንታኔ ሲሰጥ ይሰማል፡፡ የኢትዮጵያ የሰብአዊ መብት ጉባኤው ሪፖርት ደግሞ በኦሮምያ ክልል የክልሉ ታጣቂ በትግሬው የአግአዚ ጦር እየታዘዘ መንግሥቱ የኦሮሞ ሞቦች ናቸው ያላቸው ላይ ግድያ ፈጻሚ እንደነበረ ይገልጻል፡፡ መጽሐፉ እንደሚያስረዳው የኢትዮጵያ የጦር ሠራዊት የደርግ/ኢሠፓ መንግሥትን አፍርሶ ፈርሷል፡፡ የትግሬው ጦር እና የተለጣፊው የብሔር ታጣቂው አባላት ያለባቸውን የሕግ፣ የሙያ፣ የዜግነት እና የሥነልቡና ግዴታዎች እየተገነዘቡ ሲሄዱ በመፍረስ ላይ ይገኛሉ፡፡

የኃይለማርያም/ኢሕአዴግ መንግሥት ነው የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓትና የመአዓመ አብዮት እውቀቱ ያለው እና ሕጋዊ፣ የዜግነት፣ የሙያ እና የሥነ-ልቡናዊ ግዴታዎቹን የተረዳ ሠራተኛ እንዳይቀጠር እየከለከለ የሚገኘው፡፡[69] የኃይለማርያም/ኢሕአዴግ መንግሥት (ወይም የመወቤካው ተቀጣሪዎች እና ተጠቃሚዎች) ናቸው ኢትዮጵያውያን በገንዘባቸው ያቋቋሙት ኢሳት የቲቪ እና ሬዲዮ ጣቢያና የዜና እና የትምህርት መርሃግብሮቹ ለኢትዮጵያውያን እንዳይደርሱ የዓለም ንግድ ሕግ (WTO) እና የዓለም የሳይበር ደህንነት ሕጐችን በመጣስ ግልፅ ባላደረገው የገንዘብ ምንጭ በመጠቀም ከቻይና በተከራየው የኢንተርኔት መቆጣጠርያ ሕዝቡን የእውነቱን እውቀት እንዳያገኝና የመንግሥቱ ሞብ ሆኖ የአጥፍቶ ጠፊ ጦርነቶችን እንዲዋጋ የሚያደርገው፡፡ የኃይለማርያም/ኢሕአዴግ መንግሥት የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት እንዲቀጥል በማድረግ ሕዝቡን አደንቁሮ እና ሞብ አድርጐ ለመግዛት እየሞከረ መሆኑ ታውቋል፡፡

የወያኔ/ኢሕአዴግ የማስታወቂያ ሚኒስቴር ሚዲያዎች (ኢቲቪ፣ ሬድዮ፣ እና ጋዜጦች) ለኢትዮጵያ ሕዝብ ስለ የመአዓመ አብዮት እና ስለ 1942-1975 የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ትምህርት እና እውነተኛ ዜና መስጫ ሳይሆን፣ የመወቤካው እና ተለጣፊ ባለሥልጣናቱ የፈጠራ መስዋእትነት የሚዘከርበት፣ ያልነበሩትን እና ያልሆኑትን ሆነው የሚቀርቡበት እና የኢትዮጵያ የመአዓመ አብዮት ታጋዮች አረመኔነት የሚወራበት መድረኮች ሆነዋል፡፡

የኃይለማርያም/ኢሕአዴግ መንግሥት (የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት) ተቀጣሪዎቹን ከየት ያመጣውን ገንዘብ (ያውም በትግሬ አለቃ እና የተለጣፊ ባለሥልጣን ትእዛዝ የጥፋት ሥራዎችን ለማሠራት) እየከፈላቸው እንደሆነ አይነግራቸውም፡፡ አሁን የገንዘቡ ምንጭ የመአዓመ አብዮት መንግሥታት የ1942-1975 የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ግንባታን ለማጠናከር እና ቀጣይነት እንዲኖረው ለማድረግ የሰጡት መሆኑን ሁሉም ሲረዱ የገንዘቡ መጠንና የአጠቃቀም ሪፖርቱ ለኛም ለኢትዮጵያ ሕዝብም ለለጋሾቹም ይገለጥልን፣ እንዲሁም በ1942-1975 የመአመ የሠራተኛ ሕጐችና ሥርዓቶች ቅጥራችን እና የሥራ እና የሥራ ዋስትና መብታችን ይከበርልን እያሉ ናቸው፡፡ ሠራተኛውና ሕዝቡ የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት ያፈረሰው የበጀት እና የግብር ቀጠና እና የገቢ/ወጪ መረጃ (fiscal jurisdiction and trail records) ይመለስ እንዲሁም የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት መጠናከር እና ቀጣይነት ይረጋገጥልን እያለ ነው፡፡

የኃይለማርያም/ኢሕአዴግ መንግሥት ከመአዓመ አብዮት መንግሥታት ጋር የተስማማበትን ውል (የ1942-1975 የመአመ እና የገበያ ኢካኖሚ ግንባታን ሥርዓትን ማጠናከር እና ቀጣይነት እንዲኖረው ማድረግ) ለማስፈጸም ቢሞክር ኖሮ የሠራተኞቹን የሙብት ጥያቄዎች ይመልስ ነበር፣ የኢትዮጵያንም የኢኮኖሚ እና ማኅበራዊ ችግሮች መፍታት በቻለ ነበር፡፡ ይኸን ባለማድረጉ የኃይለማርያም/ኢሕአዴግ መንግሥት የኢትዮጵያን የመአመን መጠናከር እና የገበያ ኢኮኖሚ ግንባታ ሊያዘገየው ይችላል፤ ሂደቱን ማቆም ግን አይችልም፡፡

የኃይለማርያም/ኢሕአዴግ መንግሥት ይበልጥ አላሠራ ያለው የሕግ፣ የሙያ፣ የዜግነት እና የሥነልቡና ግዴታዎቹን የተገነዘበውና ያፈራውን ሀብት እና ንብረት ሁሉ በሕጋዊ፣ ፍትሐዊ እና ሥነልቡናዊ ተቀባይነት ባለው መንገድ ያገኘው መሆኑን በመአመ እንዲረጋገጥለት የሚፈልገው ኢትዮጵያዊ ነው፡፡[70] ይኸን ግለሰብ ወይም የኢኮኖሚ ድርጅት ከወያኔ/ኢሕአዴግ የትግሬ መንግሥቱ እና ከግሉ ማፊያ ጋር መወዳደር እንዳይችል አድርገውታል፡፡ ከትግሬ የመንግሥቱ እና የግሉ ማፊያ ውጪ ያለ ኢትዮጲያዊ ባለሀብት በወያኔ/ኢሕአዴግ (የብሔር) አፓርታይድ እና የማፊያ ኢኮኖሚ ሥርዓት ውስጥ ከመከሠር እና ከሥራ ፈትነት ውጪ የኑሮ ምርጫ የሌለው ነው፡፡ የኃይለማርያም/ኢሕአዴግ መንግሥት ተቀጣሪዎች ይህን ኢትዮጵያዊ ጉቦ ይበሉታል፣ ገንዘቡን ይቀሙታል፣ ሕጋዊ መረጃዎቹን ያጠፉቸዋል፡፡ የጠየቁትንም ከፍሎ ላወጣቸው ወጪዎች ሕጋዊ መረጃ ማግኘት አይችልም፡፡ ጥፋትን አልፈጽምም ካለ በፈጠራ ክስ በካንጋሩ ፍርድ ቤቶቻቸው ከሰው ይፈርዱበታል፡፡ ንብረቱን ለመቀማት ካልገደሉት በወያኔው ፖሊስ ጣቢያ እና እሥር ቤት በማሰቃየት የቁም ሙት ያደርጉታል፡፡

የውጭ ማፊያ ካልሆነ በስተቀር ከመአዓመ አብዮት መንግሥታት የሚነሳ ባለሀብት የኃይለማርያም/ኢሕአዴግ ኢትዮጵያ ውስጥ መዋዕለ ንዋይ አያፈስም፡፡ ዋናው ምክንያት የንብረት ሙብቶቹ (የመአመ ስለሌለ) በኢትዮጵያ ያልተከበሩ በመሆናቸው ነው፡፡ ዛሬ በእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ (neocolonialism) ዘመን ይደረግ እንደነበረው የመአዓመ አብዮት መንግሥታት ዜጐቻቸው የጥፋት እቃዎችን በማምረት እና አገልግሎቶችን በመፈጸም በኢትዮጵያ ተጠቃሚ እንዲሆኑ አይፈቅዱላቸውም፡፡ ፈጽመው ቢገኙ በመአመ ፍርድ ቤቶች ከሰው ይቀጧቸዋል፡፡ ከመአዓመ አብዮት መንግሥታት አገሮች

[69] የኃይለማርያም/ኢሕአዴግ መንግሥት የሚባለው በ 1991-2013 የነበረው የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት ያለመወቤካው መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

[70] ይኸን የመሰለ ግለሰብ ወይም የኢኮኖሚ ድርጅት በወያኔ/ኢሕአዴግ እና የሆሶን ምርጫዎቹ የ1942-1975 የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓቱ የፈረሰ ስለሆነ ሰብአዊ ሙብቶቹ (የንብረት ሙብቶቹን ጨምሮ) የተከበሩ አይደሉም፡፡

የሚነሱ ባለሀብቶች ወደ የወያኔ/ኢሕአዴግ ኢትዮድያ (እንዲሁም የሻቢያ ኤርትራ) ላለመግባታቸው ይኸ ዋናው ምክንያት ነው፡፡

የውጭ ማፊያውም ቢሆን ወደ ኢትዮጵያ የሚሄደው መዋዕለ ንዋይ ለማፍሰስ ሳይሆን ከወያኔ/መወቤካው ተሿሚዎች ጋር በመሰባጠር የኢትዮጵያን የመሬት ሃብት ለመዝረፍ እና የሥራ መብቱ ያልተከበረለትን ኢትዮጵያዊ ጉልበት ለመበዝበዝ ነው፡፡ በመሬት ሀብቱ እና በሕዝቡ የሚበዘበዝ ጉልበት ተጠቃሚ ለመሆን የረጅም ዘመን ኢንቨስትመንት (long term investment) ይጠይቃል፡፡ በተጨማሪ ድርጊቱ የዓለምን ንግድ ድርጅት (WTO) ድንጋጌ ይጻረራል፡፡ ኢትዮጵያ የሰብአዊ (የምግብ) ርዳታ ተመጽዋች አገር ስለሆነች፣ ያም ርዳታ ከኃይለማርያም/ኢሕአዴግ መንግሥት ቁጥጥር ውጪ እና በመአዓመ መንግሥታት ሙሉ ቁጥጥር ተፈጻሚ የሚሆን ስለሆነ የውጪ ማፊያ ከኢትዮጵያ የሚያገኘው ትርፍ አይኖረውም፡፡

የኃይለማርያም/ኢሕአዴግ ሥርዓተ መንግሥት ተጠቃሚዎች የሆኑትም የመንግሥቱ እና የግሉ ኢኮኖሚ የትግሬ ማፊያዎች፣ የሥርዓቱ ደጋፊ ትግሬዎች እና የተለጣፊ ባለሥልጣናትም ቢሆኑ የአጭር ጊዜ ተጠቃሚዎች ናቸው፡፡ በ1991-2013 ከኢትዮጵያ ሕዝብ የዘረፉትን ንብረት እና ሀብት እና የመአዓመ አብዮት መንግሥታት የ1942-1975 የመአመ እና የገበያ ኢኮናሚ ተጠናክሮ ቀጣይ እንዲሆን የሰጡትን ርዳታ ንብረት ገንብተውበታል፣ የኮንትሮባንድ ንግድና የማፊያ ተቋማት ዘርግተውበታል፣ እና ምናልባት የዚህን አብዛኛውን ገንዘብ ለቅንጦት እቃ እና ለመፍጅት (consumption) ተጠቅመውበታል፡፡ ከዚህ በተረፈ የሥርዓቱ ቁንጮዎች የመአመ ሥርዓቱን ያፈረሱት በመሆኑ እና የዝርፊያ ሀብታቸው የመብት ጥበቃ የሌለው በመሆኑ ሀብቱ ወደ ውጭ እንዲወጣ አድርገዋል፡፡ ከድህረ ቀዝቃዛው ጦርነት ወዲህ የመአዓመ አብዮት ተፈጻሚ በመሆኑ በመአዓመ አብዮት ባንኰች ገንዘቡን በሕጋዊ፣ ፍትሐዊ እና ሥነ-ልቡናዊ ተቀባይነት ባለው መንገድ ያገኙት ባለመሆኑ በመአዓመ አብዮት መንግሥታት ባንኮች ማስቀመጥ አይችሉም፡፡[71]

አንዳንድ የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት የአፓርታይድ መንግሥቱ እና የማፊያ ኢኮናሚ ሥርአቱ ተጠቃሚዎች በመአዓመ አብየት አገሮች ባንኮች መጠቀም ባለመቻላቸው የዘረፉትን ገንዘብ በአምባገነን መንግሥታት አገሮች ባንኮች አስቀምጠዋል፡፡ ያስቀመጡት ገንዘብ የመብት ጥበቃ የሌለው በመሆኑ ገንዘቡ ለአስቀማጮቹም ሆነ ለወራሾቻቸው ጠቀሜታ የለውም፡፡ ኢትዮጵያውያንም ሊጠቀሙበት አይችሉም፡፡ ለኢትዮጵያ የጠፋ ገንዘብ ነው፡፡

በመአዓመ አብዮት አገር ባንኰች የተቀመጡ ገንዘቦች እና የተገዙ ንብረቶች ባለቤቶች በመአመ ፍርድ ቤቶች በሕጋዊ፣ ፍትሃዊ እና ሥነ-ልቡናዊ ተቀባይነት ባለው መንገድ ያገኙት መሆኑን እንዲያረጋግጡ ይገደዳሉ፡፡ በመአዓመ አብዮት አገራት ዜጐች የሆኑ እና ስደተኛ ኢትዮጵያውያን በኢትዮጵያ የ1942-1975 የመአመ እና የገበያ ኢኮናሚ እንዲጠናከር እና ቀጣይነት እንዲኖረው ለማድረግ እየተዘጋጁ ሲሆኑ እኒህን ዘራፊዎች በመአዓመ አብዮት አገሮች (በኢትዮጵያ የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓቱን ማቋቋም ከተቻለ ደግሞ በኢትዮጵያ) ፍርድ ቤቶች ተጠያቂዎች እንደሚያደርጓቸው ይጠበቃል፡፡

በ1991-2013 የወያኔ የአፓርታይድ መንግሥት ትግሬው እንዲታጠቅ እና በአዲስ አበባ እና መቀሌ ለደህንነት ሲባል የሥርዓቱ ተጠቃሚ ትግሬዎች በተጠበቁ አካባቢዎች እንዲኖሩ ተደርጓል፡፡ በአዲስ አበባ የብሔር ክልል እንዲፈጥር እና በትግሬ አለቃ የሚተዳደር ቀበሌ እና በትግሬ አለቃ የሚመራ የፖሊስ ጣቢያ ዘርግቶለታል፡፡ በመንግሥቱ በአዲስ አበባ የመኖሪያውን አካባቢ የተጠበቀ እንዲያደርግ ያስቻለው በመሆኑ ለጊዜውም ቢሆን ተጠቃሚ ትግሬው የተሻለ ደህንነት ሊሰማው ይችላል፡፡ የኃይለማርያም/ኢሕአዴግ መንግሥት በዚህ ቢቀጥል ከሌሎች የአፍሪካ አገሮች (ደቡብ አፍሪካ፣ ኬንያ፣ ናይጀርያ፣ ወዘተ) እንደሚታየው የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት ተቀጣሪው ትግሬ ለምንድነው እኔ ለብቻዬ የምለፋው? እንደሚል ሲሆን ይኸም አሁን እየታየ ነው፡፡ ሞቡ እና የሞራል ፀፀት በሽታ (moral hazard) ተጠቂው ሕዝብ የመንግሥቱን ሥልጣን (መንግሥት ስለሌለ) በእጁ በማስገባት በሕዝቡ ላይ በደል እንደሚፈጽም ይጠበቃል፡፡ የሚጠበቀው በብሔር የተደራጀ የወንጀለኛ ቡድን በብሔር ያልተደራጀውን የከተማውን ነዋሪ እንደሚዘርፍ ሲሆን ይኸም አሁን መታየት ጀምሯል፡፡ የተራ ወንጀለኛ ቡድን የቆመ መኪና ይፈታል፣ ቤት ሰብሮ መግባት ጀምሯል፣ የመንግሥት ሠራተኛው የመንግሥት አገልግሎት ፈላጊውን በማን ይነካኛል ባይነት ደጅ ጠኚ ያደርገዋል፡፡ የማያልቅ ጉቦ እንዲከፍል ያስገድደዋል፡፡ የሚዘረፍ ገንዘብ ያለው ከትግሬው ሠፈር ስለሆነ የትግሬው ባለሀብት የሞቡ እና የሞራል ፀፀት በሽታ ተጠቂው መንጋ ሰለባ ከመሆን ግን ሊያመልጥ አይችልም፡፡ ሞቡን እና የሞራል ፀፀት በሽታ ተጠቂ የሆነ ሕዝብ ከአጥፍቶ መጥፋት ጦርነቶች ሰለባ ከመሆን ማዳን የሚቻለው እውነቱን (የመአዓመ አብዮት እና የ1942-1975 የመአመ እና የገበያ ኢኮናሚ መጠናከር እና ቀጣይነት ተፈላጊነትን) በማስተማር እና የሥነ-ልቡና ግዴታውን እንዲገነዘብ በማስቻል ነው፡፡

---

[71] የወያኔ/መወቤካው መንግሥት እና የሳሎን ካቢኔው እና የክልሉ ኢሕአዴግ መንግሥት መሪ የነበሩት አቶ መለሰ በዚህ አኳኋን የዘረፉትን በቢሊዮን ዶላር የሚቆጠር ገንዘብ በውጭ ባንክ በድብቅ ያስቀመጡ መሆኑ በዓለም አቀፍ የገንዘብ እና የሰብአዊ መብት ድርጅቶች ተረጋግጧል፡፡ ኢትዮጵያ በሙስና እና በካፒታል በረራ ቀዳሚ አገር ሆናለች፤ እንዲሁም በዓለም ውስጥ ለቢዝነስ ሥራዎች አመቺ ካልሆኑት ተርታ ተመድባለች፡፡

በቤተ እምነቶች አካባቢ ያለውን ሁኔታም ለመመልከት ሞክሬአለሁ፡፡ የወያኔ/መወቤካው መንግሥት (1991-2013) በሹመኞቹ ትግሬዎች የሚመራ የእምነት ሥርዓት ፈጥሯል፡፡ የዚህ ሂደት በአገሪቷ የእምነት ቦታዎች ሁሉ ተፈጻሚ ሆኗል፡፡ በዘመነ ኃይለማርያም/ኢሕአዴግ ዘመን (ድህረ-2013) ደግሞ ጐልቶ የታየው በእምነት ቦታዎች ሁሉ የትግሬዎቹ እና የሌላ ብሔር አባላቱ ፍጥጫ ነው፡፡ የወያኔ/መወቤካው መንግሥት በ1991-2013 ይኸ ፍጥጫ በመወቤካው የሳሎን ካቢኔ እና የክልል መንግሥቱ (የተለጣፊ መንግሥቱ) አካባቢ የፈጠረውን በድንነት (የመንግሥት ሥራዎችን መሥራት አለመቻል) በቤተ እምነቶች አካባቢም እንዲፈጠር አድርጎታል፡፡

በV ለመመልከት እንደተሞከረው የድህረ-ሙብት ሰዎች የሆኑት ኢትዮጵያውያን በቅድመ-ሙብት ኢትዮጵያ እንዲኖሩ በመገደዳቸው በጐተራ የታሸገውን ምግብ ከበው በረሀብ ሞተዋል፡፡ የመወቤካው/ኢሕአዴግ መንግሥት (1991-2013) የመአዓመ አብዮት መንግሥታት የ1942-1975 የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት እንዲጠናከር እና ቀጣይነት እንዲኖረው ለማስቻል የሰጡትን ርዳታ መራኰቻ በማድረግ የኢትዮጵያውያኑን አረመኔነት ማሳያ አድርጐታል፡፡[72]

ቢዘገይም አሁን በመታየት ያለው በእምነት ቦታዎች እራሳቸውን የመወቤካው ተሿሚዎች አገልጋዮች ያላደረጉ የሀይማኖት አባቶች ኢትዮጵያውያኑን የአባቶቻቸውን ሰብአዊነት እና የእምነት ጽንአት እንዲጠብቁ እያስተማሩ ነው፡፡ የዚህ ሂደት ጠቀሜታው ኢትዮጵያ በሀሰት እምነት በመመራት በአጥፍቶ መጥፋት ጦርነት የሚጠፋውን ሞብ እና የሞራል ፀፀት በሽታ ተጠቂ በእውነት እውቀት ላይ ተመሥርቶ ሕዝበ-ውሳኔ መስጠት የሚችል ሕዝብ ማድረግ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ አረመኔ አለመሆኑን ማረጋገጥ የሚችለው የወያኔ/መወቤካው መንግሥት እንዲራኰትበት ያቀረበለትን የመአዓመ አብዮት መንግሥታት ርዳታ ቁብ ሳይሰጠው ለኢትዮጵያዊነት እና ለሰብአዊነት የበለጠ ክብር ሲሰጥ ነው፡፡

XVI

ስለመአዓመ አብዮት እና ስለ 1942-1975 የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት መጠናከር እና ቀጣይነት እውቀቱ ያላቸው፤ ሥርዓቱን የገነቡ፤ የሥርዓቱን ቀጣይነት ማረጋገጥ የሕግ፣ ሙያ እና ሥነ-ልቡናዊ ግዴታቸው መሆኑን የተረዱ እና ለመአዓመ አብዮት ተፈጻሚነት ከፍተኛ ዋጋ የከፈሉ ኢትዮጵያውያን እና የመአዓመ አብዮት መንግሥታት በኢትዮጵያ የ1942-1975 የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ መጠናከር እና ቀጣይነት እንዲኖረው ለማድረግ የሚገጥማቸው ከባድ እንቅፋት የለባቸውም፡፡ ይኸን የጋራ አላማቸውን ከግቡ እንዳያደርሱት እንቅፋት የሆኑባቸው የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት፣ የመንግሥቱ የሆብሶን ምርጫዎች እና በነሱ የሚነዱ ሞቦች እና የሞራል ፀፀት/ዝቅጠት በሽታ ተጠቂዎች ብቻ ናቸው፡፡[73]

በአሁኑ ሰዓት የመአዓመ አብዮት መንግሥታት እና የ 1942-1975 የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት ደጋፊ ኢትዮጵያውያን የ 1942-1975 የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት መጠናከር እና ቀጣይነት እንዲኖረው ለማረጋገጥ መወሰድ ያለበት ተቀዳሚ ሥራ ነው ብለው የወሰኑት የሚከተለውን ነው፤[74]

1. የኢትዮጵያ ሕዝብ (ሞብ ወይም ደግሞ የሞራል ዝቅጠት በሽተኛ ሳይሆን)[75] በእውነቱ እውቀት በመመሥረት ሕዝበ-ውሳኔውን መስጠት መቻል ይኖርበታል፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ በመአዓመ ስምምነት የ 1942-1975 የመአመ

---

[72] ልክ የናዚው ጦር አንዲት በግ በተራበው የአፍሪካ ወታደር መሀል በመልቀቅ የአፍሪካውያኑን አረመኔነት ማሳያ እንዳደረገው፣ የወያኔ/መወቤካውም መንግሥት (1991-2013) የመአዓመ አብዮት መንግሥታት የ1942-1975 የመአመን እና የገበያ ኢኮኖሚ ለማጠናከርያ እና ቀጣይነት እንዲኖረው ለማስቻል የሰጡትን ርዳታ መራኰቻ በማድረግ የኢትዮጵያውያንን አረመኔነት አሳይቶበታል፡፡

[73] በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያን የፖለቲካ ምኅዳር የተቆጣጠሩት የኢትዮጵያ ተጋላቢ የትሮይ ፈረሶች፣ አሸባሪዎች እና አረመኔዎች (ኢተትፈአዎች) ናቸው፡፡ ባሁኑ ወቅት በሜዳው ላይ ያሉትን ኢተትፈአዎች የስም ዝርዝር አቅርበናል (Vን ተመልከት)፡፡ ኢተትፈአዎች ያለባቸውን የሕግ፣ የሙያ እና የሥነ-ልቡና ግዴታዎች መወጣት አይችሉም፡፡ ያለውጭ የትሮይ ፈረስ ጋላቢ መንግሥት ወይም የውጭ የጥፋት ኃይል ጥይት ካላቀረበላቸው፣ ስንቅ ካልሠፈረላቸው እና አመራር ካልሰጣቸው በራሳቸው መቆም እና ምንም ማድረግ የማይችሉ ናቸው፡፡ በዝርፊያ ገንዘብ እና በውሸት እና አሳሳች መረጃዎች ተጠቃሚዎች ናቸው፡፡ የኢተትፈአዎች መሪዎች "ዘጠኝ የድመት ህይወታቸውን" ነዋሪዎች ሲሆኑ፤ እነሱ የሚመሯቸው (የሚነዷቸው) ሞቦች እና የሞራል ዝቅጠት በሽታ ተጠቂዎች (በእውነቱ እውቀት ተመሥርተው ሣይሆን) በመሪዎቻቸው ላይ ባላቸው (የተሳሳተ) እምነት ሕዝበ-ውሳኔ አድራጊዎች ናቸው፡፡ የመአዓመ አብዮት መንግሥታት የኢተፈአዎችን በአሸባሪነት ፈርጀው የሚዋጓቸው ሲሆኑ፤ ኢተትፈአዎቹ እንደ እስስት የሚለዋወጥ ጠባያቸውን (በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያን የ1942-1975 የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ መጠናከር እና ቀጣይነት ደጋፊዎች ነን በማለት) በማሳየት ላይ ናቸው፡፡

[74] የመአዓመ አብዮት መንግሥታት በአንድ በኩል የ1942-1975 የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ እንዲጠናከር እና ቀጣይነት እንዲኖረው እየከፈሉ ሲሆን፤ በሌላ በኩል ደግሞ የወያኔ/ኢሕአዴግን የአፓርታይድ ሥርዓትና የማፊያ ኢኮናሚ ወጪዎችን (ለጥፋት ሥራ የሚደረጉ ወጪዎች) የሚሸፍኑበት ገንዘብ የላቸውም፡፡ የመአዓመ አብዮት መንግሥታት ወጪዎቹን የሚሸፍኑት ሠራተኞቹ እና ታጣቂዎቹ የ1942-1975 የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ግንባታ እንዲጠናከር እና ቀጣይነት እንዲኖረው ማረጋገጥ የሚያስችለውን ሥራ ሲሠሩ ብቻ ነው፡፡

**እና የገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት መጠናከር እና ቀጣይነት እንዲኖረው ማድረግ የኢትዮጵያን የኢኮኖሚ እና የማኅበራዊ ችግር ለመፍቻነት አማራጭ የሌለው ብቸኛ መንገድ መሆኑን የተረዳ እና ለተፈጻሚነቱም መስዋእት ለመክፈል የቆረጠ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡**

2. **በ(1) ተራ ቁጥር የታየውን ተፈጻሚ ማድረግ የሚቻለው በእውነተኛ ተቃዋሚ ፓርቲዎች (እተፓ) አማካይነት (አደራጅነት) ነው፡፡ ለምርጫ ከቀረቡት እተፓዎች መካከል እውነቱን ባወቀ ሕዝብ ሕዝበ-ውሳኔ ተመራጭ የሚሆነው እተፓ የኢትዮጵያ የመልካም አስተዳደር መንግሥት (መአመ) ይሆናል፡፡**

መጽሐፉ በ1 ተራ ቁጥር የታየውን "እውነት" ማንኛውም ያለበትን የሕግ፣ የሙያ፣ የዜግነት እና የሥነ-ልቡና ግዴታውን የተገነዘበ ሰው የሚቀበለው መሆኑን ያስረዳል፡፡[76] ሌላው ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ያለ አንዳች ማቅማማት የሚቀበለው የኢትዮጵያን የአገር ህልውና እና አንድነት መጠበቅ ነው፡፡[77]

ከላይ የታየውን ጉዳይ ታሳቢ በማድረግ የኢትዮጵያ ሕዝብ የአገር ዳር ድንበሩን ለማስከበር፣ የመአዓመ አብዮት እንዲሰፍን እና የ1942-1975 የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት ተጠናክሮ ቀጣይነት እንዲኖረው ለማስቻል የምክር ቤቱን አባላት እና ፖለቲካ ፓርቲዎችን እንዲመርጥ ማስቻል የኃይለማርያም/ኢሕአዴግ መንግሥት ግዴታው ነው፡፡[78]

አሁንም ቢሆን የጠቅላይ ሚ/ር ኃይለማርያም/ኢሕአዴግ መንግሥት የካቢኔውን ሹማምንት በማሰባሰብ የፖለቲካ ፓርቲዎች ስብሰባ ሊያዘጋጅ ይችላል፡፡[79] በሶርያው እንደታየው የኃይለማርያም/ኢሕአዴግ መንግሥት ምርጫውን ማዘጋጀት ካልቻለ በተባበሩት መንግሥታት የጸጥታው ምክር ቤት ውሳኔ ምርጫውን የሚመራ አካል ተሹሞ **የፓርቲዎች ስብሰባው** እና **የምክር ቤቱ አባላት ሕዝበ-ምርጫው** እንዲካሄድ ይደረጋል፡፡

የፓርቲዎቹ ስብሰባ የሚፈለገው **የምርጫ ቦርዱን** ለመሰየምና፣ የቦርዱ መርሀ-ግብሮቹን ለማጽደቅ ይሆናል፡፡[80] የቦርዱ አባላት የመአዓመ አብዮት እውቀት ያላቸውና የ1942-1975 የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት መጠናከር እና ቀጣይነት ተፈላጊነቱን የተረዱ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ በ1955/1947 የተሻሻለው ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 142፣ በ1987ቱ የደርግ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 116 እና በወያኔ/ኢሕአዴግ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 5 ድንጋጌ የኢትዮጵያ መንግሥት የመሥሪያ ቋንቋ አማርኛ በመሆኑ የቦርዱ አባላትም ሆኑ የምክር ቤቱ አባላት በአማርኛ ቋንቋ መጻፍ እና ማንበብ የሚችሉ መሆን አለባቸው፡፡ ሌላው የቦርዱ ዋና ተግባር የምርጫ አካባቢዎቹን (በፓርቲዎቹ ስብሰባ በተሰጠው መመርያ መሠረት)

---

[75] የኃይለማርያም/ኢሕአዴግ (ወይም የወያኔ መወቤካው መንግሥት) ተቃውሞ ለማሰማት እና ሕዝበ-ትርኢት ለማሳየት የወጡትን የኦሮሞ ተማሪዎች እና ሌሎች ተሰላፊዎች በተለጣፊው፣ ታብተፓው እና ተብጦፓው ለአጥፍቶ መጥፋት ሥራ የሚነዱ ሞቦች ሲያደርጋቸው፤ በሳጥን የታየው ወጣት እና የአፓርታይድ እና የማፊያ ኢኮኖሚው ተጠቃሚዎች ደግሞ የሞራል ዝቅጠት (moral hazard) በሽታ ተጠቂዎች ናቸው፡፡

[76] የመወቤካው/ኢሕአዴግ መንግሥት ከመአዓመ አብየት መንግሥታት ጋር የኢትዮጵያን የመአዓመ አብዮት ተፈጻሚ እንዲሆን እና የ1942-1975 የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት አጠናክሮ ቀጣይነት እንዲኖረው ለማድረግ ተስማምቶ ነበር፡፡ ነገር ግን ስምምነቱን በመጣስ፣ የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚውን በማፍረስ የብሔር የአፓርታይድ መንግሥት እና የማፊያ ኢኮኖሚ ሥርዓት ዘርግቷል፡፡

[77] ወሳኙ ጉዳይ የኢትዮጵያ ሕዝብ ያገሩን ሕልውና፣ አንድነት እና ነጻነት መጠበቅ ለድርድር የማያቀርብ መሆኑ እና ስለመአዓመ አብዮት እና ስለ 1942-1975 የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት ያወቀ መሆኑ ሲሆን፣ የመወቤካው/ኢሕአዴግ መንግሥት እና ሁሉም ኢተትፈአዎች የሚያደርጉት ደግሞ ሕዝቡ ያ አገር ወዳድነት እና የእውነቱ እውቀት እንዳይኖረውና እነሱ የሚነዱት ሞብ እና በሞራል ፀፀት በሽታ ተጠቂ እንዲሆን ነው፡፡ እነሱ የመንግሥትን ሥልጣን ለመያዝ እና ይዘው ለመቆየት የሚፈልጉት በሞብ እና በሞራል ፀፀት ተጠቂ ሕዝብ ሕዝበ-ምርጫ ነው፡፡

[78] የኃይለማርያም/ኢሕአዴግ መንግሥት በመወቤካው/ኢሕአዴግ መንግሥት ይደረግ የነበረውን የዜሮ ድምር ጨዋታ (ለቅንጅት ተለጣፊ ቅንጅት፣ ለመኢአድ ተለጣፊ መኢአድ ወዘተ እየፈጠረ እተፓዎችን ማጥፋት) ለመድገም ቢሞክር የመአዓመ አብዮት መንግሥታት በፊት እንዳደረጉት "ለምርጫው ተመልካች አንልክም" በማለት አይወስኑም፡፡ ከተፈለገ የተባበሩት መንግሥታትን ስምምነት በመጠየቅ በጅቡቲ የሠፈረውን የኔቶ ጦር ወደ ኢትዮጵያ በማስገባት በተባበሩት መንግሥታት አስፈጻሚነት የሕዝቡ ወኪሎች ምርጫ እንዲካሄድ ያደርጋሉ፡፡ ሕዝቡ የሚመርጣቸው ወኪሎቹ በኢትዮጵያ የግዛት አንድነት እና ኢትዮጵያ በመአዓመ አብዮት መንገድ መሄድ አለባት የሚሉ መሆን አለባቸው፡፡ ማለትም ተመራጭ የምክር ቤት አባላት የኢትዮጵያን በመአዓመ ስምምነት በ1942-1975 የተዘረጋውን የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት መጠናከር እና ቀጣይነት የሚደግፉ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ ከዚህ የተለየ አጀንዳ ያላቸው ቡድኖች ምክር ቤቱ ከተቋቋመ እና በእተፓው አስተባባሪነት ለምክር ቤቱ ቀርቦ በሚጸድቀው ሕገ-መንግሥት መሠረት ሊስተናገዱ ይችላሉ፡፡ ምክር ቤቱ በዚህ ቅድመ ሁኔታ ካልተመሠረተ የተለየ ጥያቄ ያለውን ወገን ማስተናገድ አይቻልም፡፡

[79] የኃይለማርያም/ኢሕአዴግ መንግሥት ካቢኔው የመወቤካው ሹማምንት (ትግሬዎቹ እና ተለጣፊ ባለሥልጣናቱ) በጐሪጥ የሚተያዩበት ቢሆንም በዚህ ጉዳይ ላይ ጠቅላይ ሚ/ር ኃይለማርያም የጋራ አቋም እንዲወስዱ እና የጦር ኃይሉ እና የፖሊሱም ሠራዊት ለጠቅላይ ሚ/ሩ ታዛዥ መሆናቸውን ማረጋገጥ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን የኃይለማርያም/ኢሕአዴግ መንግሥት የመወቤካው/ኢሕአዴግ መንግሥትን (ያለመወቤካው) ልሁን ካለ እንደመንግሥት ግዳጁን ባለመፈጸሙ ተጠያቂ ሲሆን የምርጫውን ሂደት ግን መግታት አይችልም፡፡

[80] የምርጫ ቦርድ አባላት እና ተመራጭ የምክር ቤቱ አባላት የመአዓመ አብዮት እና የ1942-1975 የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓቱ እውቀት ያላቸው፤ ሥርዓቱን ያቋቋሙ እና የገነቡ እንዲሁም ለሥርዓቱ መጠናከር እና ቀጣይነት መስዋእት የከፈሉ መሆን አለባቸው፡፡ እኒህ ሰዎች ያለባቸውን የሕግ፣ የሙያ (የእውቀት)፣ የዜግነት እና የሥነልቡና ግዴታቸውን የተረዱ (የተገነዘቡ) መሆን አለባቸው።

መወሰንና ሕዝቡ ወኪሎቹን ለምክር ቤቱ አባልነት ምርጫ እንዲያካሄድ ማድረግ ነው፡፡[81] ሕገ-መንግሥቱን አርቅቆ በምክር ቤቱ እንዲጸድቅ ማድረግም ለቦርዱ ወይም በሕዝበ-ምርጫ አሸናፊ ለሆነው እውነተኛ ተቃዋሚ ፓርቲ (እተፓ) ሊተው ይችላል፡፡ የምርጫ ቦርዱ ሌላው ተግባር ወኪሎቹን ለምክር ቤቱ መራጩ ሕዝብ ሞብ እና የሞራል ፀፀት በሽታ ተጠቂ አለመሆኑን እና በመአዓመ አብዮት መንገድ እና በ1942-1975 የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት የሚመራ መሆኑን ማረጋገጥ ይሆናል፡፡[82]

በኃይለማርያም/ኢሕአዴግ መንግሥት ወይም በተባበሩት መንግሥታት ሹመኛ ለስብሰባ የሚጠሩት ፓርቲዎች የቶቹ ናቸው? የመወቤካው/ኢሕአዴግ (ወይም ወያኔ/ኢሕአዴግ) መንግሥት (1991-2013) የፈረሰ (እና የሌለ) ስለሆነ ተሳታፊ አይሆንም፡፡ ተብጦፓዎቹም በፈረሰው የመወቤካው/ኢሕአዴግ መንግሥት በአሸባሪነት የተፈረጁ ስለሆኑ እና እራሳቸውን በመአመ ፍርድ ቤት ተጠያቂ ስላላደረጉ በፓርቲዎች ስብሰባ ላይ ተሳታፊዎች መሆን አይችሉም፡፡[83] ታብተፓዎቹም ጥያቄያቸው ከሕገ-መንግሥቱ መጽደቅ በፊት ሊመለስ ስለማይችል ሊስተናገዱ የሚችሉት በሚጸድቀው ሕገ-መንግሥት ነው፡፡ የኃይለማርያም/ኢሕአዴግ መንግሥት (2013-) በፓርቲዎች ስብሰባ ላይ ተካፋይ ሊሆን የሚችለው ካቢኔውን በማስተባበር፣ የትግሬውን ጦር እና የተለጣፊውን ታጣቂ በመንግሥቱ ቁጥጥር ሥር ሲያውል እና የፖለቲካ ፓርቲዎችን ስብሰባ መምራት እና የምርጫ ቦርዱን ማቋቋም ከቻለ ነው፡፡[84]

አሸባሪዎቹና አረመኔዎቹ በመአዓመ አብዮት መንግሥታት ጦርነት የተከፈተባቸው ስለሆኑ በፓርቲዎች ስብሰባ ላይ ተሳታፊዎች ሊሆኑ አይገባም፡፡ ኢትዮጵያውያን የመረጃ ማሰባሰቢያ ማዕከል (masreja.com) አቋቁመው መረጃዎችን ማሰባሰብ ጀምረዋል፡፡ የመአመ ፍርድ ቤቶች ከተቋቋሙ እነኚህ ተጠርጣሪ አሸባሪዎች እና አረመኔዎች ለፍርድ ይቀርባሉ፤ በመአዓመ አብዮት ፍርድ ቤቶችም ዛሬውኑ እንዲቆሙ ማድረግም ይቻላል ፡፡

በኢትዮጵያ ሕዝብና በመአዓመ አብዮት መንግሥታት ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚባ ጉዳዮች፣ (ሀ) የፓርቲዎች ስብሰባ እና የምርጫ ቦርድ መሰየም፣ (ለ) የምክር ቤት አባላትን ስለመአዓመ አብዮት እና ስለ 1942-1975 የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት መጠናከር እና ቀጣይነት አስፈላጊ መሆኑን በተረዳ ሕዝብ ሕዝበ-ምርጫ መምረጥ ናቸው፡፡ እነኚህ ተፈጻሚ ከሆኑ በኋላ (ሐ) የፓርቲዎች ምርጫዎች ይካሄዳሉ፡፡ በሕዝበ-ምርጫው አሸናፊ የሆነው እውነተኛ ተቃዋሚ ፓርቲ (እተፓ) መአመ ይሆናል፡፡

እውነተኛ ተቃዋሚ ፓርቲ (እተፓ) የምንለው፣

> **በመአዓመ ስምምነት በ1942-1975 የተዘረጋው የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ እንዲጠናከር እና ቀጣይነት እንዲኖረው ለማድረግ የማስተባበር ሥራዎችን ፈጻሚ ነው፡፡ የእተፓ አላማው በ1942-1975 የተዘረጋው የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት እንዲጠናከር እና ቀጣይነት እንዲኖረው የሚያስችለውን መርሀ-ግብር ነድፎ የኢትዮጵያ ሕዝበ-ውሳኔውን ሰጪው ሕዝብ እንዲያውቀው አድርጎ እራሱን ለምርጫ ማቅረብ ነው፡፡**

---

[81] ዛሬ ፖለቲከኞች ስለፌደሬሽን፣ የወል መብቶች (የቋንቋ፣ ብሔር፣ወዘተ መብቶች) ሲከራከሩ ይሰማሉ። ይኽ ጋሪውን ከፈረሱ ማስቀደም ነው። ይኽን ሀሳብ አራማጆች በመአዓመ አብዮት መንገድ ካልሆነ በስተቀር የፈለጉትን ማስፈጸም አይችሉም፡፡

[82] የዚህ እውቀት እና ግንዛቤ የሌለውን ሕዝብ ዒላማው ያደረገ የዜግነት ትምህርት ከሕዝበ-ምርጫው በፊት ሊሰጥ ይችላል፡፡

[83] እዚህ ላይ መታወቅ ያለበት ጉዳይ የመወቤካወ/ኢሕአዴግ መንግሥት ተብጦፓዎቹን ተጠያቂዎች ያደረገበት ጥፋት የተፈመ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ተብጦፓዎቹ በጥፋቱ ለተጐዱት ሰዎች ሀዘናቸውን አልገለጡም፤ ጥፋቶቹን የፈጸሙ አለመሆናቸውን አላስተባበሉም፡፡

[84] የኃይለማርያም/ኢሕአዴግ መንግሥት በሕገ-መንግሥት ሥርዓት ሳይሆን በትግሬ አለቃ እና በተለጣፊ ሹማምንት ትእዛዝ የሚሠራ መንግሥት ነው፡፡ ሆኖም በሂደት መወቤካው/ኢሕአዴግ ለጥፋት ሥራ እና ለትግሬው ከለላ እንዲሆን ያሠማራው የጥፋት ሠራዊት ያለበትን የሕግ፣ ሙያ፣ የዜግነት እና የሥነ-ልቡናዊ ግዴታዎች እየተረዳ ሲመጣ በትግሬ አለቃው እና በተለጣፊው ባለሥልጣን ትእዛዝ ሳይሆን በ1942-1975 የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት እና ሕግ መሠረት እንሥራ ባይ ሆኗል፡፡ የተለጣፊው ባለሥልጣንም ተመሳሳይ ግዴታዎቹን ሲገነዘብ ከትግሬ አለቃው ጋር ተስማምቶ መሥራት አቅቶታል፡፡ ለሁሉም የሚበጀው በመአዓመ ስምምነት በመአመ እና በገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓተ መንግሥት ሕግና ደንብ መሥራት መሆኑን እንገነዘባለን፡፡

የመወቤካው/ኢሕአዴግ መንግሥት (1991-2013) ይጠቀም የነበረው የሕግ፣ የሙያ፣ የዜግነት እና የሥነ-ልቡናዊ ግዴታዎቹን ባልተረዳው የጥፋት ሠራዊት ነበር፡፡ ባሁኑ ወቅት መወቤካው የፈረሰ በመሆኑ የጥፋት ሠራዊቱም ግዴታውን እየተገነዘበ በመምጣቱ ለሁሉም ሰው ሰላም እና የኢኮኖሚ እና ማሕበራዊ እድገት ሊገኝ የሚችለው በመአዓመ አብዮት መንገድ ብቻ መሆኑ ግልፅ እየሆነ መጥቷል፡፡ የኃይለማርያም/ኢሕአዴግ መንግሥት በዚህ አኳኋን የፓርቲዎችን ስብሰባ እንዲመራ እና ምርጫ ቦርዱን እንዲያቋቁም የሕግ ግዴታ አለበት፤ የመአዓመ አብዮት መንግሥታት ድጋፍንም ያገኛል፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ በሕዝበ-ምርጫ እተታውን መአመ ማድረግ የሚችለው በመጀመሪያ እተታውንና መርሀ-ግብሮቹን ሲያውቅ ነው፡፡ ስለዚህም እተታው ከሕዝቡ ምርጫ በፊት ዐላማውን፣[85] የአባላቱን ማንነት፣ የመንግሥቱን ወጪ የሚሸፍንበትን ገንዘብ ምንጭ እና መጠን እንዲሁም የኢትዮጵያን የፖለቲካ መድረክ የተቆጣጠሩትን ኢተትፈአዎች እና ከነሱ ጋር ያለውን ግኙኝነት ለሕዝበ-ውሳኔ ሰጪው ሕዝብ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡[86] በአጭሩ እተታው ማንነቱን፣ ዐላማውን፣ መርሀግብሩን እና ወጪዎቹን እና መሸፈኛውን ለመራጩ ሕዝብ ማሳወቅ ይጠበቅበታል፡፡

የእተታው መርሀ-ግብር አራት አብይ ጉዳዮችን ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ አንደኛ፣ በ1942-1975 የተዘረጉት የመአመ መሥሪያ ቤቶች በመአዓመ ስምምነት እና በመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት እና ደንብ እንዲሠሩ ያደርጋል፡፡ የታሳቢ ሹማምንቱን ስም የእውነቱ እውቀት ባለው ሕዝብ (በሞብ እና በሞራል ፀፀት በሽታ ተጠቂ ሕዝብ ሳይሆን) ሕዝበ-ውሳኔ ተመራጭ ለሆነው ምክር ቤት በማቅረብ እንዲጸድቅ ካደረገ በኋላ የመንግሥት ሠራተኞች [የሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ሠራተኞች እና የፍርድ ቤት ሠራተኞች (ዳኞች፣ አቃብያነ ሕግ፣ ጠበቆች እና የአስተዳደር ሠራተኞች)] በ1963/1955 የመንግሥት ሠራተኛ መተዳደርያ ኤጀንሲ (Central Personnel Agency, CPA) አስተዳደር እና ደንብ (Regulations) መሠረት ቅጥራቸው ተፈጻሚ እንዲሆን ያደርጋል፡፡ የግል ኢኮኖሚ ክፍሉ ሠራተኛ ደግሞ በሠራተኛ እና ማኅበራዊ እድገት ሚኒስቴር እና በ1964/1955 የሠራተኛ ሕግ መሠረት ቅጥሩን ተፈጻሚ ያደርጋል፡፡ የጦር ኃይሉ እና የፖሊስ ሠራዊቱን በሚመለከት ለምክር ቤቱ ውሳኔ የሚቀርበው መርሀ-ግብር አመራሩን የሚሰጡት የፖሊስ ኮሌጅ፣ የሐረር አካዳሚ፣ የአየር ኃይል ማሠልጠኛ እና የመርከበኛ ማሰልጠኛ ኮሌጅ ተመራቂዎች እና ባለሙያዎች እንደሚሆኑ ያረጋግጣል፡፡ ማዕከላቱም ተከፍተው ባለሙያዎች አምራቾች እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡

ሁለተኛ፣ የእተታው (ለምክር ቤቱ እንዲያጸድቅ የሚያቀርበው) መርሀ-ግብር አትኩሮቱ የወያኔ/መወቤካው መንግሥት የአፓርታይድ እና የማፊያ ኢኮኖሚ ሥርዓቱን ይመለከታል፡፡ የ1942-1975 የመአመ ሥርዓቱን መመዘኛዎች የማያሟሉ ሠራተኞችን መብቶች የሚያስከብር መርሀ-ግብር ለምክር ቤቱ በማቅረብ እና በማስፈቀድ ተፈጻሚ ያደርጋል፡፡ ይኸ መርሀ-ግብር በዓለም አቀፍ ስምምነቶች (International Labour Organization Convention) ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት፡፡

እንዲሁም የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት ለጥፋት ሥራ እና ለትግሬው ከለላ በመሆን እንዲያገለግሉ የዘረጋቸው ተቋማት (ለምሳሌ ክልሎች፣ ዞን፣ ወረዳ እና ቀበሌ፤ የወያኔ ደህንነት መሥሪያ ቤት፣ ወዘተ) እተታው መርሀ-ግብር ነድፎ እንዲዘጉ ወይም የመአመ ሕገ-መንግሥታዊ የአስተዳደር ሥርዓት እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡ የዚህን መርሀ-ግብር ለምክር ቤቱ ውሳኔ እንደሚያቀርብ ይጠበቃል፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ በመወቤካው/ኢሕአዴግ ዘመነ መንግሥት ፍርድ ቤቶች የካንጋሩ ፍርድ ቤቶች ሆነዋል፤ የሚያስፈጽሙትም የሥርዓቱን ባለሥልጣናት "ትእዛዞች" ሆኗል፡፡ እተታው ለምክር ቤቱ የሚያጸድቀው መርሀ-ግብር ፍርድ ቤቶች (በ1942-1975 እንደነበረው) የመአመ ነጻ አካል በመሆን ምክር ቤቱ ያጸደቃቸውን ሕጐች (ለምሳሌ የ1960/1952 የንግድ ሕግ፣ የ1960/195 የፍትሐ ብሔር ሕግ እና የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉን) መተርጐም ይሆናል፡፡

ሦስተኛ፣ የወያኔ/ኢሕአዴግ የማፊያ ኢኮኖሚውን ይመለከታል፡፡ የመንግሥቱ በዝርፊያ የተገነቡ የኢኮኖሚ ተቋማት በ1942-1975 በተዘረጋው የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት (በ1960/1952 የንግድ ሕግ እና በ1960/1952 የፍትሐብሔር ሕጐቹ እና በአዋጅ በተቋቋሙት ተቆጣጣሪ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ደንቦች መሠረት) ወደ መንግሥት ንብረትነት (public property) ይዞራሉ፡፡ የመንግሥቱ የማፊያ ኢኮኖሚ ተቋማት በዝርፊያ የተገነቡ የትግሬ እና የሌሎች ብሔሮች መንግሥታት ኩባንያዎችን ያካተተ ሲሆን፣ መርሀ-ግብሩ ተቋማቱ የሚዘጉበትን፣ ወደ መንግሥት ንብረትነት (public property) እና የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ ንብረትነት (private property) የሚዛወሩበትን መርሀ-ግብር በምክር ቤቱ ካጸደቀ በኋላ ተፈጻሚ ያደርጋል፡፡ የመወቤካው/ኢሕአዴግ መንግሥት ተጠቃሚ ግለሰብ በእጁ ያለውን ንብረት፣ ሥልጣን፣ አልከሰስም ባይነት (immunity አለኝ ማለት) እና ሁሉም የኔ ነው ባይነት (privilege አለኝ ማለት) በ1942-1975 የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ

[85] ዐላማው በመአዓመ ስምምነት በ1942-1975 የተዘረጋውን የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት እንዲጠናከር እና ቀጣይነት እንዲኖረው ማድረግ ነው፡፡ ይኸ ዐላማ የመአዓመ አብዮት መንግሥታት እና የመወቤካ/ኢሕአዴግ መንግሥት የተስማሙበት ነበር፡፡ ሆኖም የመወቤካ/ኢሕአዴግ መንግሥቱ (1991-2013) የመአዓመ ስምምነቱን በመጣስ የአፓርታይድ እና የማፊያ ኢኮኖሚ ሥርአት ዘርግቷል፡፡

[86] በኢትዮጵያ ሁኔታ ሰማያዊ ፓርቲ፣ ቅንጅት፣ መኢአድ እና የግንቦት 7 ፓርቲዎች ወደ እተፓነት ለመቀየር የቀሯቸው ጉዳዮች ቢኖሩም፣ እተፓ ለመሆን የሚችሉ ይመስላሉ፡፡ የእተፓዎች መፈጠርን በሚመለከት የትግርኛ ተናጋሪው ምሁራን ተሳትፎ የቀዘቀዘ መሆኑ አሳሳቢ ነው፡፡ የመንግሥቱ ሥልጣን በወያኔ እና ሻቢያ እጅ መሆኑ ገለልተኛነትን እንዲመርጡ ያስገደዳቸው ይመስላል፡፡ ገብረመድኅን አርአያ፣ አብርሃም ያየህ እና ሌሎቹም እንደሚያስረዱን የእነህ የጥፋት መንግሥታት ወደሥልጣን መምጣት የብዙ የትግሬ እና ሀማሴን ምሁራንን መስዋእት አስከፍሏል፡፡ የኒህን ሰማዕታት ፈለግ መከተል የሚቻለው እና በህይወት ያሉት እነህ ምሁራን የሕግ፣ የሙያ፣ የዜግነት እና የሥነ-ልቡና ግዴታቸውን መወጣት የሚችሉት እተፓዎችን ሲፈጥሩ፣ ሲቀላቀሉ እና ሲመሩ ነው፡፡

ሥርዓት መሠረት በሕጋዊ፣ ፍትሐዊ እና ሥነ-ልቡናዊ ተቀባይነት ባለው መንገድ ያገኘው መሆኑን እንዲያረጋግጥ ያስገድዳል፡፡

አራተኛ፣ የእተፓው መርሀ-ግብር የሚያተኩረው ከ1975 ወዲህ የተፈጸሙ የወል ግዴያዎች፣ ሰብአዊ መብቶች ገፈፋዎች፣ ንብረት ዝርፊያዎች፣ የሕዝብ ከሥራ እና መኖሪያ ማፈናቀሎች ላይ ነው፡፡ እተፓው ፈጻሚዎቹ የሚታወቁበትን እና ለፍርድ የሚቀርቡበትን መርሀ-ግብር ነድፎ ለሕዝቡ ምክር ቤት ለውሳኔ በማቅረብ እና ፍርድ ቤት እንዲቀርቡ በማድረግ የጥፋት ምዕራፉን እንዲዘጋ ያደርጋል፡፡ የዚህ ሂደት ዐላማው የመንግሥቱን እና የግሉ ኢኮኖሚ የብሔር ማፊያዎቹን ያላቸውን የንብረት ባለቤትነት መብት፣ የሥልጣን ባለቤትነት መብት፣ (authority) ማንም አይነካኝም የማለት (immunity አለኝ) መብት እና እንዲሁም የይገባኛል ባይነት (privilege አለኝ ባይነት) መብት በሕጋዊ፣ ፍትሐዊ እና ሥነ-ልቡናዊ ተቀባይነት ባለው መንገድ ያገኙት መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው፡፡

በመጨረሻም በዚህ ሂደት ሁሉም ተጠቃሚ እንደሚሆን መገንዘብ ይገባናል፡፡ በሥርዓቱ አምባገነንነት የተጐዱ እና መብታቸውን የተገፈፉ ሰዎች ይካሳሉ፣ ፍትህን ያገኛሉ፡፡ በሥርዓቱ ተጠቃሚዎች የሆኑ የንብረት መብታቸው ይከበርላቸዋል፡፡ በአፓርታይድ መንግሥቱ እና የማፊያ ኢኮኖሚው ብልሹ አሠራር ንብረታቸውን የተቀሙ፣ በኪሣራ ኗሪ እንዲሆኑ የተገደዱ እና ሌሎቹም ሠርተው መኖር ያልቻሉ ባለሀብቶች የንብረት መብታቸው ይከበርላቸዋል፣ ሠርተው እና አትሪፊዎች ለመሆን ሁኔታዎች ይመቻቹላቸዋል፡፡

አንዱ የሂደቱ ጠቀሜታ ኢትዮጵያ ለውጭ ማፊያ የማታመች፣ የአገር ማፊያ በቁጥጥር ሥር እንዲወድቅ የሚደረግባት፣ በሕጋዊ፣ ፍትሐዊ እና ሥነልቦናዊ ተቀባይነት ባለው መንገድ ለመኖር እና ለመሥራት ለሚፈልግ የምትሰብ አገር መሆኗ ነው፡፡ የውጭ ባለሀብቶች በመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት መብቶቻቸው የተከበሩ ስለሚሆን ኢትዮጵያ የውጭ ካፒታል የሚፈስባት (የውጭ ካፒታል መሳብ የምትችል) አገር ትሆናለች፡፡

የሶቪየት ኮሚኒስት ፓርቲ እና የስብስብ ኢኮኖሚ ሥርዓቱ ከ100 ዓመታት በኋላ ፈርሷል፡፡ የኮሚኒስት ፓርቲው ወደ መአመ የስብስብ ኢኮኖሚው ደግሞ ወደ ገበያ ኢኮኖሚ አልተለወጠም፡፡ የመአዓመ አብዮት መንግሥታት ይኸን ለውጥ የሚደግፉ እና ርዳታም ለመስጠት ያቀዱ ቢሆኑም መንግሥቱ የተተካው በሆብሶን ምርጫው የሩሲያ ኦሊጋርኪ ሲሆን የስብስብ ኢኮኖሚውም በመለወጥ ላይ ያለው ወደ ውጭ ፈሰስ የማፊያ ኢኮኖሚ ነው፡፡ እንዴት ነው የዛሬዋ ሩሲያ የመአዓመ አብዮት (ማለትም የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት) ወደሰፈነበት ሁኔታ መለወጥ የምትችለው? እንዴት ተደርጐ ነው ኦሊጋርኪው ወደ መአመ፣ ውጭ-ፈሰስ ማፊያ ኢኮኖሚው ደግሞ ወደ ገበያ ኢኮኖሚ የሚለወጠው?[87]

ለኢትዮጵያ ወደ 1942-1975 የመአመ አብዮት (የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት) መመለሱ ቀላል ብቻ ሳይሆን የዓለም ርዳታም የተቸረው ብቸኛው የእድገት መንገድ ሆኖ ይገኛል፡፡ የተገነባ የስብስብ ኢኮኖሚ የለም፤ የመወቤካው/ኢሕአዴግ መንግሥትም (1991-2013) ሊያስፋፋ የሞከረው (የጥፋት) የማፊያ ኢኮኖሚ በምድረ በዳ ላይ የተተከለ ዛፍ ሆኗል፡፡ የኢትዮጵያ ተጋላቢ የትሮይ ፈረሶች፣ አሸባሪዎች እና አረመኔዎች (ኢተትፈአዎች) እና የነሱ ሞቦች እና የሞራል ፀፀት/ዝቅጠት በሽታ ተጠቂዎች የኢትዮጵያን የፖለቲካ ምኅዳር ተቆጣጥረውታል፡፡ ሆኖም የመአዓመ አብዮት መንግሥታት (የተባበሩት መንግሥታት) በእነሱ ላይ ጦርነት ያወጁባቸው ስለሆነ በኢትዮጵያ የመአዓመ አብዮት መስፈኑን እና የ1942-1975 የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት መጠናከሩን እና ቀጣይነቱን ሊገቱት አይችሉም፡፡

እነህ የጥፋት ኃይሎች (ኢተትፈአዎች) የሚፈልጉት የኢትዮጵያውያንን አረመኔነት ዓለም እንዲያውቅላቸው ለማድረግ እና ኢትዮጵያም እንደ አገር እንድትፈርስ ነው፡፡ ኢትዮጵያውያን አሸባሪ እና አረመኔ አለመሆናቸውን ለማረጋገጥ የሚችሉት እንዲሁም

---

[87] በ1975-1991 የሶቪየት ኅብረት የኢትዮጵያን በመገንባት ላይ የነበረውን የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት ግንባታ አፍርሰዋለች፡፡ ለሩሲያ ኦሊጋርኪ የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት ያልተዘረጋባትን ሩሲያ ወደዛ ሥርዓት መቀየር ብዙ የገንዘብ ወጪ፣ የባህል ለውጥ እና የረጅም ጊዜ ትግልን ይጠይቃል፡፡ ሩሲያኖች ያንን ረጂም ጉዞ በይፋ ካልጀመሩት መንግሥቱም የወደቀ መንግሥት (failed government) ኢኮኖሚውም የወደቀ ኢኮኖሚ (failed economy) እንደሚሆን መጸሐፉ ያስረዳል፡፡

ቻይናም ብትሆን ዛሬ የመአዓመ ስምምነቶችን በመቀበሏ እና የግለሰብ የንብረት መብትን አስከብራለሁ በማለቷ ወይም የገበያ ኢኮኖሚ ማሻሻያ በማድረጓ ከፍተኛ የኢኮኖሚ እድገት ልታሳይ ችላለች፡፡ ሆኖም የመንግሥት ማሻሻያዎች (government reform) ባለማድረጓ በገበያ ማሻሻያ ያገኘችውን የኢኮኖሚ እድገት ታጣዋለች የሚል ፍራቻ አለ፡፡ የመአመ ሥርዓት እየዘረጋች አይደለም፡፡ የስብስብ ኢኮኖሚዋም ወደ ማፊያ ኢኮኖሚ እየተቀየረ ነው፡፡ ሙስና እየተስፋፋ ሄዷል አዲሱ የግሉ ማፊያም መጠነ ሠፊ የካፒታል በረራ እያስከተለ መጥቷል፡፡

አገራቸውንም ከማፍረስ የሚያድኑት የመአዓመ አብዮት መንግሥታት በሚሰጡት እርዳታ አንራኮትም ሲሉ እና እንደ አባቶቻቸው ለነጻነት፣ ለኢትዮጵያዊነት እና ለሰብአዊነት በህይወታቸው መስዋእትነት የበለጠ ክፍያ የሚከፍሉ መሆናቸውን ሲያረጋግጡ ነው፡፡[88]

ተሾመ ሙላት ታደሰ
12 መጋቢት 2008
(21 March 2016)

[88] ኢትዮጵያዊነትን እና ሰብአዊነትን በማዳበር ረገድ ወሳኙን ሚና የሚጫወቱት ቤተ እምነቶች/ሀይማኖቶች ናቸው፡፡ እንደሌላው አካባቢ ሁሉ በቤተ እምነቶች/ሀይማኖቶች አካባቢም የመአዓመ አብዮት ወገኖች እና የኢተትፈአዎች ወገኖች ከ20 ዓመታት መፋጠጥ እና ዝምታ በኋላ የመአዓመ አብዮት ወገኖች የሆኑ የሀይማኖት አባቶች የሥነልቡናዊ ትምህርት በመስጠት ላይ ናቸው፡፡ በዚህም ረገድ የመአዓመ አብዮት፣ ማለትም የ1942-197 የመአመ እና የገበያ ኢኮኖሚ ሥርአት መጠናከር እና ቀጣይነት የተረጋገጠ እየሆነ መጥቷል፡፡